# ማኅሌተጽጌ

## ለመጀመሪያ ጊዜ ተተርጕሞ ተሪዘ





ሰላም ኦሽን በመትር ኪሚጸልይ አፍ የጽጌ
አበባን ስትቀበይ ታምርሽን ያየ አደኑተ ዝ 18

እግዚአብሔር ሥራውን የሚገልጽበት ጊዜ አለና፡-
መዝ 118÷126፡

እግዚአብሔርን ሥራህ ግሩም ነው በለ-ት፡
መዝ 65÷3

ተርጓሚና አዘጋጅ ሊቀ ጠበብት አስራደ ባይብል

ፐብያኔ (1998) ዓ.ም
አዲስ አበባ

Scanned by CamScanner



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቀነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት

Scanned by CamScanner



ብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ የጠቅላይ ቤተክህነት ዋና ሥራ
አስኪያጅ የከምባታ ሐድያና ጉራጌ ሀገረስብከት ሊቀ ጳጳስ

Scanned by CamScanner

# መታሰቢያ

ይህ የማኅሌተ ጽጌ ትርጉም መጽሐፍ መታሰቢያነቱ፡-

1. በትዱስ ያሬድ ማኅሌት /ለማያዊ ምስጋና/ ሌት ከቀን ለሚያገለግሉ ሊቃውንት፡-
2. እግዚአብሔር በሰጣቸው ጸጋ በሄዱበት ዓለም ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል ለሚያስተምሩ ሰባክያን መምህራን፡-
3. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች አባላትና መዘምራን፡-
4. በዘመነ ጽጌ ሌሊት በማኅሌት ተገኝተወ ለሚያገለግሉና ለሚነለገሉ ምእመናን፡-
5. የእመቤታችን የድንግል ማርያምን ቃል ኪዳን ለጠበቁ ማለት ስሟን ለሚጠሩ፣ ዝክሯን ለሚዘክሩ ምእመናን በሙሉ ይሁንልን።

አዘጋጅች ለቀጠበብት አስራደ ባያብል

» ተማሪ ይርጋለም ወሰኑ

» ተማሪ ዘውድነሽ አዳነ

በአጋዴን ሀገረ ስብከት ውስጥ ከሚገኘው ከታላቁ ደብር ደብረ መዊዕ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ጅጅጋ።

Scanned by CamScanner

# መግለጫ

ማኅሌት ማለት:- ምስጋና፣ ወረብ፡ ለዘብ፣ ማወደስ ማለት ነው... የመዘመር ሥልጣን የተሰጠው ንጉሥ ዳዊት በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ታቦት ፊት በመንፈስ ወደ ሰማይ ተነጥቆ ልብሱን እስኪጥል ድረስ ዘምሯል አመስግኗል:: 2ኛ ሳሙ 6÷12-8 በገጽ 53 በተራ ቍጥር ፴፫-፴፭ ላይ እስከ መነነቶ ሜልኮል ቅድመ ታቦተ ሕግ ከመዘፈነ ብሎ እንዲያመጣው::

የማኅሌት ትርጉም ምስጋና መሆኑን ከገለጽን ጽጌ የሚለውን ትርጉም ደግሞ እናያለን::

ጽጌ ማለት:- አበባ የፍሬ ምልክት ማለት ሲሆን ማኅሌተ ጽጌ ብሎ ሲናበዝ በአበባና በፍሬ የተመሰሉ ድንግል ማርያምና የማሕጸኗ ፍሬ ክርስቶስ የሚመሰገኑበት የአበባ ምስጋና ማለት ነው::

ይህ ማኅሌተ ጽጌ በትርጉም እንዲቀርብ ያስፈለገበት ዋናው ምክንያትም ትርጉሙ:- ምሥጢሩ:- ታሪኩ የሚታወቅ የማኅሌት ባለሙያና የግእዝ ቋንቋ ባለቤት በሆኑት ሊቃውንት ስለሆነ በዚህ ብቻ ተወስኖ እንዳይቀር በማሰብ ነው:: ሱራፌል፣ ኪሩቤል ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ እያሉ እግዚአብሔርን በማመስገን ቀንና ሌሊት አያርፉም ከአንደበታቸውም ምስጋና አይቋረጥም ብሎ ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚያስረዳን ራእ 4÷5-11 በዘመነ ጽጌ በሌላም ክብረ በዓል (ንግሥ) ጊዜ እንደሊቃውንቱ ምእመናንና ምእመናት:- በተለይ ውጣት የሰንበት ትምህርት ቤት አባላትና መዘምራን የማኅሌቱ አገልግሎት ተሳታፊ በመሆናቸው በዜማው ጣዕም ብቻ እየተገለገሉና እያገለገሉ ይገኛሉ:: ሆኖም በእውኑ የምታነበውን:-

Scanned by CamScanner

ቃል ትርጕሙን፡- ምሥጢሩን ታውቀዋለህን? ብሎ ሐዋርያው ፊልጶስ ለኢትዮጵያዊው ጃንደረባ እንደነገረው፡- ትርጕሙ ፡- ምሥጢሩን፣ ታሪኩን ተረድተዉ የበለጠ ቤተ ክርስቲያንን እንዲያገለግሉ ሃይማኖታቸውንም ጠብቀዉ እንዲያስጠብቁ ነው ከትርጕሙ ከምሥጢሩ ከሐተታው ውጭ ደራሲው በዚህ ማኅሌተ ጽጌ ውስጥ ስም እየጠቅሰ እንዲሁም ስም ሳይጠቅስ በንባብ ምሥጢር ብቻ የተናገራቸው ሁሉ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስማቸውና ታሪካቸው በግልጽ ተጽፎ ይገኛል። የማኅሌተ ጽጌ ደራሲ ኢትዮጵያዊው ሊቅ እመቤታችን ድንግል ማርያምንና ልጇ መድኃኒዓለምን በወይን ሐረግ፡- በጽጌረዳ አበባ፡- ሌላም መመሰል በሚገባቸው በልዩ ልዩ በጎ ምሳሌዎች ሁሉ እየመሰለ የደረሰው ግሩም የጸሎት መጽሐፍ ነው በመሆኑም ከ85 በላይ ታሪኮችን የያዘ ልዩ መጽሐፍ መሆኑን ለአንባቢያን በደስታ እየገለጽን እግዚአብሔር በሊቃውንት ልቡና አድሮ የሚናገረው ምሥጢር እንደውቅያኖስ ባሕር ቢቀዳ ቢቀዳ አያልቅምና አልፎ አልፎ የንባብ መለያየት ቢኖርም ማለት በበዓታ፡- በግምጃ ቤት፡- በተለያዩ ሊቃውንት ሁሉ የሚነገረው ንባብ በትርጕምና በምሥጢር እስካልተለያየ ድረስ አቀራረቡ (ዝግጅቱ) በቅንፍ በቅንፍ ሆኖ ቀርቧል ለምሳሌ ዘኒ /ዘንተ/ ስብሐተ ወዘኒ (ወዘንተ) ማኅሌተ እንደ ማለት ነው። በገጽ 213 በተራ ቍጥር ፻፶፬ 154 ላይ ሁሉን በዚህ ዓይነት ማየት፡- መመርመርና መረዳት ይቻላል።

የማኅሌተ ጽጌ ደራሲ ታሪክ፡- የገጽ ማውጫ በመጨረሻ ከ219-230 ገጽ የተጻፈ መሆኑንም ለአንባቢያን እናሳስባለን።

የእመቤታችንና የልጇ ረድኤት ከሁላችን ጋር ይሁን አሜን።

Scanned by CamScanner

መግቢያ

- ኅሰፈ. ከረምት

ከነኔ ሃያ ስድስት ቀን እስከ መስከረም ሃያ አምስት ቀን ድረስ ያለው የዘናም ወራት አሰፈ ሄደ መጋ 2፥ 11

- ቆመ በረከት

ከመስከረም ሃያ ስድስት ቀን እስከ ኅዳር ስድስት ቀን የልምላሜ፡- የእበባና የፍሬ፡- ወራት የሆነ አርባ ቀን ዘመነ ጽጌ ደረሰ ተባለ።

- ተሠርገወት ምድር በሥነ ጽጌያት።

ምድርም በልምላሜ በእበባና በፍሬ ተሸለመች አጌጠች።

- ለመርዓዊሃ ትብሉ መርዓት፡- ወልድ እጮየ ወረደ ውስተኅሳት።

ሙሽራዋ ሙሽራውን ልጅ ወንድሜ ወደተክል ቦታው ወረደ።

የተክል ቦታውንም ንዝኅ ትለዋለች መጋ 6፥1-3

(ሐተታ) ሙሽራዋ የተባለች ቤተ ክርስቲያን ስትሆን ሙሽራው የተባለ ክርስቶስ ነው ። ወደ ተክል ቦታው ወረደ ማለት የዘወትር ከረምት ምስጋና አልፎ ዘመነ ጽጌ ተተክቶ የመላእክት ጣዕመ ዝማሬ በዘመነ ጽጌ ልምላሜ፡- ጽጌ፡- ፍሬ፡- ወይን፡- መዓዛ በሚል በሊቃውንት ምሥጢር ቅመም የተቀመመና የተጣፈጠ ስብሐተእግዚአብሔር፡- ስብከተ ወንጌል፡- የቅዱስ ሥጋውና የክቡር ደሙ መድኃኒትነት በቤተክርስቲያን ይነገራል ይሰጣል ማለት ነው። ከዚህ በመቀጠል የታሳቁ ሊቅ የአባ ጽጌብርሃን /ጽጌ ድንግል/ ድርሰት ወደሆነው ወደ ማኅሌተጽጌ ትርጉም ገብተን እንሂ ላክታለን. . .



ክፍ ፤ ጽጌ አስተርአየ ሠረፃ አምላዕሙ።

ለዘአምኀክ ጽጌ ለገብርኤል ምስለሰላመ

አበባን ይዞ ያበሠረሽ ገብርኤል፤

ከገብርኤል ሰላምታ /ምስጋና/ ጋር እጅ ከነሳሽ

ሰው ዓፅም ውስጥ የጽጌረዳ አበባ በቅሎ ታየ

መበእንተዝ ማርያም ሶበሐወዘኒ መዓዛጣዕሙ።

ለተአምርኪ አኀሊ አሙ

ማኅሌተጽጌ ዘይሰመይ ስሙ።

ስለዚህም የክርስቶስ እናቱ ድንግል ማርያም ሆይ ደስ የሚያሰኝ የዜማው ድምፅ ባስደሰተኝ ጊዜ ብርቅና ድንቅ ልዩም ሰሆነ ለታምርሽ አመሰግናለሁ /እዘምራለሁ/ ወይም ስሙ ማኅሌተጽጌ ለሚባል ታምርሽ ምስጋናን አቀርባለሁ።

## ከአንድ ሙት ሰው አፍ የጽጌረዳ አበባ ስለመታየቱ ታሪክ

በኢያሪኮ ባሕር ደሴት ውስጥ የሚኖር ስሙ አስቴራስ የሚባል አንድ ዲያቆን እመቤታችን ድንግል ማርያምን የሚወድ ነበር። የውስጥ በደሉን በማሰብ በሚጸልይበት ጊዜ ከኀጢአቱ መጎራት የተነሣ ድምፁን ከፍ አድርጎ /አሰምቶ/ አያጸልያም ነበር።

Scanned by CamScanner

በለሆሳስ (ድምፁን ሳያሰማ) እመቤቱ ድንግል ማርያም ሆይ ሰላም ላንች ይሁን እያለ ይጸልያል።

ከዕለታት አንድ ቀን ከነበረበት ቦታ ወጥቶ ራቅ ወዳለ አገር ሄደ ላለ ርኅራኄ የሌላቸው ሰዎች ድንገት አገኙትና ገደሉት። በድኑንም ትተዉት ሄዱ ሌሎች ሰዎች በዚያ መንገድ ሲያልፉ በድኑን ወድቆ አገኙት በመንገድ ጥግም ቀበሩት።

ከሦስት ቀን በኋላም እመቤታችን ድንግል ማርያም ከፋ ሰዎች ባሉባት በዚያች አገር እሷን ሰሚወድ ሌላ አንድ ዲያቆን በራእይ ተገልጻ ታየችው።

ወዳጄ ሆይ የሚወደኝና ጸሎተ ርኅኔ ዘንድ የተወደደ ዲያቆንን ስለገደሉት በዚያች አገር ውስጥ ባሉ ክፋ ሰዎች እኔ አገኛሃለሁ ስሙ አለችውና ከአሁን ጀምሮ ኀደጭችህ ዲያቆናትን ይዘህ በመንገድ ጥግ ወደ ቀበሩት ዲያቆን ሂድ ብዙ

አንተን አዝዘሃለሁ። መቃብሩን ቆፍሩ በድኑንም ከዚህ አውጥታችሁ በክርስቲያኖች መቃብር መካከል ቅበሩት የገደሉትን ሰዎች ግን ልጄ ይበቀላቸዋል /እንደ ሥራቸው ይከፍላቸዋል/ አለችው።

ዲያቆኑም የእመቤታችን ድንግል ማርያምን ትዛዝ በሰማ ጊዜ ፈጥኖ ተነሣ ኀደጭቹንም ስበሰባቸው ያየውንም ራእይ ሁሉ



ነገራቸው የዚያን የሞተ ዲያቆን መቃብሩን ቆፍረው በድኑን አወጡ ርሄ እንደሚባል ሽቱ መልኩና (ደም ግባቱ) ሽታው ደስ የሚያሰኝ አንድ ጽጌረዳን ከአፉ ውስጥ አገኙ ምንም መለወጥ (ጉስቁልና) አላገኘውም ነበር ይህን ድንቅ ታምር አይተው እጅግ ተደነቁ እመቤታችንንም ፈጽመው አመሰገኑ። ከዚህ በኋላ እንደሕጉ እንደሥርዓቱ ገንዘው በክርስቲያኖች መቃብር መካከል በክብር ቀበሩት ።

ስለዚህ ጽጌ አስተርእየ ሠሪያ እምኅፅሙ ከነፅሙ (ከዘይድኅ የጽጌረዳ አበባ ታየ አለ።

ሰላምኪ ማርያም አብቁለት ዕፀ-አምርት

ማርያም ሰላምታሽ /ምስጋናሽ/ የታምር እንፈኔትን አበቀለች

ወአውጽአት ጽጌ እምአፈሙት/በአፈሙት/

ከሞተ /በሞተ/ ሰው አፍ አበባን አወጣች /አስገኘች/

## በስቅላት ከሞተ ሰው መቃብር ላይ የበቀለች የእንጨት ስምና ታሪክ

አንድ ደሀ የዕለት ምግቡን እየሰረቀ የሚኖር ነበር ነገር ግን እመቤታችን ድንግል ማርያምን ይወዳትና ብዙ ጊዜ ሰላምታዋን ያቀርብላት ነበር።

Scanned by CamScanner

[illegible]



እንዘትብሊ ሊታጉትኪ አንብየተዛቲ ጸሎት
የዚች ጸሎት መድኃኒን /መጺ.ዩን/ አታነቦኩዱ አታጣድፊ
ፈጠሽ ለእንዲት ቤተ ያንቺን በሳምታ /የትዱስ ንብርኤል
ምስጋናን/ አስተግርሻት
እስመ ትኤድመኒ ሊተ እምኩሉ ስቪሐት።
ለኔ ከምስጋናው ሁሉ ይልቅ ይች ምስጋና ደስ ታሰኝለተና።

## የጽጊረዳ አበባን ያበቀለች የእመቤታችን ምስጋና ለእንዲት ቤተ ቃል ኪዳን ስለመሰጠቷ

በእንድ ገዳም ውስጥ የመነኩሰች እንዲት ደህ ቤተ ነበረች እመቤታችንን እጅግ ትወዳት ነበር ሰላምታዋንም ታዝወትር ነበር ብዙ ቤተክርስቲያንንም ትሰክናና የተቻላትን ያህል ለቤተክርስቲያን ትሰጣለች።
በእንዲት ቀንም በእንዲት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰላምታዋን ስትጸልይ እመቤታችን በራእይ ታየቻትና ለኔ እና ለልጀ የምታቀርቢው ክብርና ምስጋና ፈጽሞ ደስ ስላሰኘኝ ባንች ደስ አለን በመልኩም ሥራሽም ሁሉ እመሰገንሽ አለቻት ነገር ግን ቀጋሽ በመንግሥተ ሰማያት ፍጹም (የበለጠ) ይሆን ዘንድ በንብርኤል ሰላምታ ሰላም እልሻለሁ ብለሽ እጅ በምትነሺኝ ጊዜ ተጠንቀቂ አትቸኩዱ ይቺ ጸሎት ደስ ትለኛለች ቃልዳታለውና የሚለውን በጎ ምክር ከነገረቻት በኋላ ከእሷ ተሠወረች ያችም

Scanned by CamScanner

ጸሎተኛ ሴት እመቤታችን ስለተገለጸችላት ደስ ተሰኝቶ ከዚህ
በኋላ ያለችህላ ያለመጣደፍ በዘመኗ ሁሉ የገብርኤልን ሰላምታ
እየጸለየች ኖራለችና እንዲህ አለ።

ኤፉ-3 አሐዱ ብእሲ ገዳመ ዘወፈረ
ጊዜ ያነብብ ሰላመኪ በከመ ያለምድ ወትረ
ወደገዳም የሄደ አንድ ባሕታዊ ዘወትር ሰላምታሽን እንደ
ልማዱ በሚጸልይበት ጊዜ
ንግሥተሰማይ ማርያም ወረደኪ ምድረ።
የሰማይ ንግሥት ማርያም ከሰማይ ወደምድር ወርደሽ
እንዘትነሥኢ እምአፋሁ ጽጌረዳ ስብሐት ሥሙረ
ያማረና የተወደደ ምስጋና ያለበት ጽጌረዳን ከአፉ ስትቀበዪ
ተአምረኪ ዘርእየ አንዝረ።
ድንቅ ታምርሽን ያየ አደነቀ
አሐዱ የተባለ ጻድቁ ዘካርያስ ሲሆን
አደነቀ የተባለ የሽፍቶች አለቃ ነው።



## ከአንድ ባሕታዊ አፍ የጽጌረዳ አበባ ስለ መታየቱ ልዩ ስምና ታሪኩ

ከሮም ነገሥታት ወገን የሚሆን ስሙ ዘካርያስ የተባለ አንድ ጳልማሳ ሰው ነበር ጸሎቱን አንዳለደረሰ አስበና ይጸልይ ዘንድ ከመንገዱ ራቅ ብሎ በመልአኩ በትዱስ ገብርኤል ሰላምታ ሰላም አያለ እመቤታችንን በሚያመሰግንበት ጊዜ በእያንዳንዱ ሰላምታ ከአፉ የጽጌረዳ አበባ ይወጣ ነበር። እመቤታችንም አምሳ የጽጌረዳ አበባ እስኪሞላ ድረስ ከአፉ እየተቀበለች በከንዲ ስትታቀፍ የወንበዴዎች አለቃ አየ ግን የሚሠራውን ታምር በዓይኑ እየተመለከተ አበቦችን ይቁጥራቸው ነበር። እመቤታችንም በዘካርያስ ምክንያት ያደረገችውን ድንቅ መልካም ሥራ አይቶ አደነቀ ሽፍቶቹም የተደረገውን ታምር ቢጠይቁት እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነውና ደስ ይበልሽ በማለት አምላ ጊዜ እመቤታችንን ሰላም አላታለሁ አላቸው። ከዚህ በኋላ የወንበዴዎች አለቃ እና ሽፍቶች ባዩት ድንቅ ሥራ አምነው ንስሓ ገብተው በምንኩስና ተወስነው እመቤታችንን ሲያገለግሉ ኖሩ። ይህ ታሪክ ትውልድ ሁሉ እንዲሰማው እንዲያምንበት ተጻፈ።

Scanned by CamScanner

አእሚርየ ማርያም ከመበልፈ ታፈቅራ
ሰላመ መልአክ ለኪ እንተጽጌረዳ ትፈራ
ዘውትር ላንች ጽጌረዳን የምታስገኝ የቅዱስ ገብርኤል
ሰላምታን እንደምትወጂ አውቂ ተረድቼ
ለለአማኅጽኪ ባቲ ከመገብርኤል አብሣራ።
አዲስ የምሥራችን እንደሚናገር እንደ ቅዱስ ገብርኤል እጅ
አየንሡ ምስጋናን ባቀረብኩልሽ ጊዜ ሁሉ
አፈሞተጽጌ እምልሳንየ ትእርሪ።
እንደ ዘካርያስ የተወደደ አበባን /ምግባር ሃይማኖት/
ከአንደበቱ ትቀበዪ ዘንድ
ትእምርቱ ለሠናይትኪ ምስሌየ ግበሪ።
የርኅራኄሽን ምልክት ከኔ ጋር ኳድርኒ።
ኢየንፍር ቀዊመ ቅድመሥዕልኪ ወርኅጽጌረዳ አመንልቀ።
የጽጌረዳ ወራት ባለፈ ጊዜ በሥዕልሽ ፊት
መቆምን አላፍርም /አልፈራም/ የባሕታዊ ዘካርያስን ታሪክ
ይመስክታል ታሪኩን በተራ ቍጥር ደግ ይመልከቱ።
ዘኢየሐልቅ ስብሐተኪ (ስብሐተ) እንዘ አሴብሐኪ
(እንዘ አሴብሕ) ጥቀ።



ታምርሽ እንደ አስረዳና እንደ አስተማረ መጠን
ጸውያስምኪ ያነሥእ ዘወድቀ
ስምሽን መሥራት የወደቀውን ያነሣል እንደ ቀውስጦስ
መልአክ ያለውን በተራ ቍጥርያፃፃፍ ይመልከቱ
ንጥአኒ ይሬሲ ጻድቀ
ንጥአንም ጻድቅ ያደርጋል እንደ ስምዖን በላዔ ሰብእ ያለውን
ሄ፡ 6 ዕለተፍቅርኪ ማርያም ውስተልብየ አስተንፈሰ
ፍቅርሽን የምትገልጭበት ቀን በልቡናዬ ውስጥ ታሰበ።
ወጽላሎተሥንኪ ጽጌ በኅሊናየ ተሐውሰ
የደም ግባትሽም ማለት የሬድኤትሽ ስፋት ብዛት በልቡናዬ
ወጣ ወረደ።
ተአምረኪ እዜኑ ወስብሐተኪ ሐዲስ።
ታምርሽን እና አዲስ የሆነ ምስጋናሽን እናገራለሁ
/እናገር ዘንድ/
እምከናፍርኪ እለተመልዓ መንፈስ
በከናፍርየ ከዐዊ ሞገስ።
ረቲቅ እውቀትን ከተሞሉ እንደበቶችሽ የተገኘ ባለሟልነትን
በእንደበቴ አሳድራ።

Scanned by CamScanner

ሄ፥7 ከመፍሕሶ ቀይሕ ከናፍርኪ ጽጌ መኃ 4፥3።
ከንፈሮችሽ ፍሕሶ እንደሚባል ቀይ ልም ሐር ናቸው።
ሥውጠ ሥርናይ ከርሥኪ ወሕፁር በጽጌ
ሆድሽ ስንዴን የተሞላ ነው ማለት ማሕፀንሽ የወልደ እግዚአብሔር ማደሪያ ነው በድንግልናም ለዘላለም የከበረ ነው።
ትእምርተሕይወትየ ድንግል ወዘኮንደ መንግሥት ጽጌ።
ድንግል ሆይ የድኅነቴ ምልክትና የመንግሥት ሥር መሠረት አንች ነሽና
በማኅሌተጽጌ እዌድስኪ ለጽጌ
ተቀጺልየ ዘንጽሕኪ ጽጌ
የንጽሕናሽን ክብር ዘውድ ተቀዳጅቼ ጽጌን/አንቺን/ በማኅሌተ ጽጌ አመሰግንሻለሁ።
ሐተታ፦ የመንግሥት ሥር መሠረት የተባለ ከዕሴይ ተወልዶ በእግዚአብሔር ፈቃድ ተመርጦ የነገሠው ንጉሥ ዳዊት ነው እመቤታችንም የዳዊት ልጅ ናትና የመንግሥት ሥር መሠረት አለ።

ሄ፥8 ይውኅዝ ሐሊበትእምርት እምአስናንኪ ፀዓድው።
ነጭ ከሆኑ ጥርሶችሽ ታምር ወተት ይፈስሳል ማለት ወተት ወንዜል ይገኛል።



ወእምከናፍርኪኒ ፀቃውዐ መዓር ቅድው።
ከከንፈሮችሽም ያማረ የተወደደ የማር ወለላ ይፈስሳል ረድኤት በረከት ይገኛል መኃ 4፤11 ።

## ሐተታ

ነጭ ከሆኑ ጥርሶችሽ ማለት ንጽሕናን ቅድስናን የተሞሉ አካሎችሽ ማለት ሲሆን ከከንፈሮችሽ ማለት ደግሞ ከአመቤታችን የሚገኙ ጸጋና በረከት ናቸው።
ማርያም ጽጌ ዘዕብራትኪ መፀው።
አምዕዚ ጺአትየ በዘዚአኪ አፈው
በአበባ ዘመን /ወራት/ የተገኘሽ ጽጌ ማርያም ሆይ በአንቺ መዓዛ የኔን የበደል ሽታ ለውጪ
ወቀስሚ ልስሐትየ በፍቅርኪ ዒው
አልጫነቴንም በፍቅርሽ ጨው አጣፍጪ።

ፀ፥9 ሥነመላትሕኪ ማርያም ከመ ጽጌሮማን አቅየሐይሐ።
ድንግል ማርያም የጉንጮችሽ ደም ግባት እንደ ሮማን አበባ ቀላ /አቅላላ/ ማለት ልጅሽን አብነት በማድረግ የሰማዕታት አካል በደም አቅላላ ደምን መስለ ስደትንና መከራን ገንዘብ አደረጉ።

Scanned by CamScanner

## ሐተታ

የርግማን ዕንጨት ቅርፍቱ ቀይ አበባ ሲሆን ውስጡ ጥቅጥቅ ያለ ፍሬን የተመላ ነው። እንደዚሁ እመቤታችንም ለማዕታት እናት የምእመናን ደናግል መመኪያ ናትና።

ወወደየ ሊተ ውስተልብየ ፍሥሓ።
በልቤ ውስጥም ደስታን ጨመረልኝ
እምፍሬሥርናይ ወወይን ፍሬተአምርኪ በዝን
ከስንዴና ከወይን ፍሬ ይልቅ የታምርሽ ፍሬ በዛ
መዝ 4÷7 ።

## ሐተታ

ምነው ስንዴንና ወይንን ብቻ እነሣ ቢሉ ከአዝርዕት ስንዴ ከለትክልት ወይን ተመርጠዋል። ከነዚህም ይልቅ የታምርሽ ሥራ ይመረጣል ለማለት። ሥንዴ የሥጋው ወይን የደሙ ምሳሌ ነው። ሥንዴ ስብ ሥጋን ሲመስል ወይን ቅዱስ ደምን ይመስላልና ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ በዚህ ፀንቷል

ወጸራቅሊጦስ ማዕነቅ በአፋየ ከልሐ
ጊዜንሚድ እንዘይብል በጽሐ።



መንፈስ ቅዱስ ዋናስም /ሽመላ/ የመከር ጊዜ ደረሰ እያለ በአንደበቱ ጮኸ።

10 ንነተኪ ነፍሐ ነፋሰመዓዛ ዘደቡብ
ሕይወትነት ያለው የደቡብ ነፋስ በተክል ቦታሽ ነፈሰ
አፈወስብሐትኪ የጎዝ በአፈጽጉያን ሕዝብ።
ሽቱ ምስጋናሽ አበባን በመሰሉ ምእመናን አፍ ይፈስስ ዘንድ።
ንዒ ንዒ ድንግለ እስራኤል ጠባብ
ለተአምርኪ ጎበ ይትገበር ክብኅብ።
እዝሥዕለኪ ይጼልል ኪሩብ።
ብልሀ የእስራኤል ድንግል መልእክ ሥዕልሽን ጋርዶ
ለታምርሽ ክብር /የማኅሌት ምስጋና/ ወደ ሚደረግበት ቦታ
ነዱ ነዱ በረድኤትም ጎብኚ።

## ሐተታ

የእስራኤል ብልሀ የተባለችበት ምክንያት ከእስራኤል ነገድ በመወለዷ፤ ከሕፃንነቷ ጀምሮ በቤተ መቅደስ እስከ ስደቷ ድረስ አይሁድ ያደረሱባትን ፈተና ሁሉ በመታገሧና በትሕትናዋ ብልሀ ተብላለች።

11 ናሁ ጸገየ ወወሀበ መዓዛ
ተአምርኪ ናርዶስ ለቤተክርስቲያን ዘይሔውዛ

Scanned by CamScanner

ቤተክርስቲያንን ደስ የሚያሰኛት ናርዶስ የሚባል ሽቱ
ታምርሽ እነሆ አበበ መዓዛውንም ሰጠ።
አዝዘታረውጽኒ ቦቱ (ሊተ)ማርያም ፍናተ ቤዛ
(በፍናተ ሰዛ)
የሕይወት መንገድ የሆንሽ ማርያም ረድኤት ወደሚገኝበት
ወደ ሰዛ መንገድ እኔን እያፋጠንሽኝ ዘፍ 28÷19
አጕዱይኒ ከመወይጠል ወከመጎየል ወራዛ።
እምገጸጋጢአት እጎተአርዌ ዘይቀትል ጎምዛ
የእፉኝት እህት ከሆነች መርሂ ከሚገድል ከጋጢአት ፊት
ዘዳግ 32 ÷ 33 ኢዮ 20 ÷16 እንደ ፌቆና እንደ ጎልማሳ
ዋልያ አሸሺኝ።

## ዕተታ

ፌቆ ፈጣን እንደሆነ ከመከራ ሥጋ ከመከራ ነፍስ ፈጥነሽ
አድኚኝ ማለት ነው።
ገፀ-12 አብውኒ ቤተወይን ንብሩ ላዕሌየ ፍቅረ።
ተአምርኪ ድንግል ወስብሐትኪ ጎቡረ።
ድንግል ሆይ ታምርሽና ምስጋናሽ በእንድነት ወደ
ወይን ቤት አገቡኝ በእኔ ላይም ፍቅር አደረጉ። ማለት
በንስሓ ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን እንድቀበል አስተማሩኝ



አባለጽጌኪ መርዓት እዝዘትንብር ተዝካረ።
የልጅሽ አካል የሆነችው ቤተክርስቲያን ተዝካረ ሞቱን
በምታደርግበት ጊዜ
ትቤ አፅንዑኒ በዕፍረት ምዕረ።
ወሰደቱኒ በአክዋል ድኅረ።
አንድ ጊዜ ሹቱ ቀቡኝ ኋላም በእንኮይ አወዙኝ በሃይማኖ
በምግባር አጸኑኝ አለች መኃ 2÷ 4-5።
ቊ-13ተንሥኢ ወንዒ ያፈንት እምአድባረከርቤ ወልዓው።
የግነት ወፍ ድንግል ሆይ ከሹቱዎች ሁሉ ከሚበልጡ ከርቤና
ዓልው ከአሉባቸው ተራራዎች ተነሥተሽ ነጺ
ወሐውጺ ቤተክርስቲያን እንተመሳክው።
ርግበተነብዮ ማርያም ተአምርኪ ፍትው።
የትንቢት ርግብ ማርያም የብርሃን መስኩት ያለባት
ቤተክርስቲያንን ጎብኚ ታምርሽም ያማረ የተወደደ ነው።
ክንፍኪ ርሡይ በጽጌብሩር ፅዕድው።
ክንፍሽ ነጭ መልክ ባለው ብራማ አበባ ያጌጠ ነው።
ወበጽጌወርቅ ሐመልሚል ገቦኪ ሥርግው።
ጎንሽም ቢጫና አረንጓዴ በመሰለ ወርቅ አበባ የተሸለመ ነው
ለጊዜው የርግብ መልክ ሽልምልም ዝጕርጕር ሲሆን

Scanned by CamScanner

የእመቤታችንም ንጽሕናዋ ቅድስናዋ ክብር ክወርት የጠራ
ነውና።

ምሥጢሩ፦ ናህ የላካት ረግብ የናህን መልክት ግድረሳን
መናገር ሲሆን ታሪኩን በተራ ቍጥር ፱፪ ይመልከቱ

(፪ 14 ከመይትፈሣሕ መርዓዊ ውስተንኑቱ ዘመረደ
ጽጌያተ ይርአይ ብጊዜ ፈቀደ።
አበባዎችን ያይ ዘንድ በወደደ ጊዜ ወደተክል ቦታው
የወረደ ሙሽራ እንደሚደሰት መኃ ፮፣፪ ።
በተአምርኪ ድንግል እትፈሣሕ ፈድፋደ።
ድንግል ሆይ ከዚህ ይልቅ በተምርሽ ፈጽሞ እደሰትለዎ።
ዘያቀልል አምነየአን ያረገዘን ክዕደ
እስመአምኔኪ ፍሥሓ ተወልደ።
ከነየአን ላይ ክዕድ አዘን ሽዘምነ የሚያቀል ደስታ ከአንቺ
ተወልዷልና።
ጌታ በዘመነ ሣቁምስ ታኅሣሥ ፳፱ ሣክሰኖ ቀን መንፈቀ
ሌሊት /ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት/ ተወለደ።

(፪ ጌታ በዘመነ ሣቁምስ ታኅሣሥ ፳፱ ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት ተወለደ



እናንተ ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ እኔም
አሳርፋችኋለሁ ብሎ ክርስቶስ በቃሉ እንደ ተናገረ
ማቴ ፲፩፣፳፰።

ፎፎ፦ 15 እ፡ሰላመ ሰማኅት እንተትሔውጺ /ዘትሔውጺ/ እምርሑት
ሰላም ዘተውህበኪ መዘኪተሰላም ሲል ነው ፍትር እንድነት
የተሰጠሽ ፍትርን አንድነትን የምታሰጪ ድንግል ማርያም
ማኅበረምእመናንን በረድኤት ክሩት የምትሸኚ ነሽ
መኃ ፯፣፲-፪።
ወትትረለዩ ለክሡ በደብረምኵናት።
ደብረምኵናት በምትባል አዝርም ለሀሉ የምትታዩ
(የምትገለጪ)
ተፈሥሒ ድንግል ዘንዳሙ ጽጌ ማዕዝት።
የአበባ በረሃ ሞናስ ድንግል ሆይ ደስ ይበልሽ
አስሙተስምካ በምድርን ቃለ ተአምርኪ ጽድቅ።
ለአድኅንኮነአ ዘይሰቅሎ አምላኩር ወወርቅ።
ከብርና ክወርቅ ይልቅ በደለኛን ለማዳን የሚጠቅም እውነት
ያለበት የታምርሽ ቃል በምድራችን ተሰምቷልና ደስ ይበልሽ

## ሐቲት

ሞ ነ በዘረሀ እንድትኖር እመቤታችንም በማህፀ በረሀ በረሀብ
፡ ጅምኦ ሦስት ቁመት ስድስት ሠር መኖሯን መናገር ነው።

Scanned by CamScanner

[illegible] ሠሌዳ ሣእማ[illegible] ጠሌሞ ነ ሰራፊ ዘአጸሞ።

ኣ ኣሰኒላ ፋኪ(ል ዘበለ በጽ ቅኪ) መነ ለአንቀጸ ገነት ዘሰርጉዋ.
በእ ጽ[illegible] በሌሞ ነ በጾል ምክንያት ሰራፊ **መልአክ የዘጋት**
ነ ሰነ ዘር ነ በ ነገልነ ከወለደቸው **ልጅሽ በቀር** (ያ
ልቦበ የከፈተት ማነው? ዘዳ፣ 3፡24
ቅ. ሥሉስ ድንግል መያዘቱአለም እምዜሞ።
እጅግ ከዚያበለሰ ምርኮ የመለሰሽ በዚያብሉስ ከመገዛትዋ
ነፃ ያወጣሽ ድንግል ማርያም ደስ ይበልሽ።
ስቀለሚኪ ውስተምድረጽጌ አቲሞ።
ኤሎሳነሞ እንፈርዐት ሌሞ።
ሲኖሚርሽ ካነች በተወለደ አምላክ/ አበባ ወደ
እሳት ነት ንጢ ሌሞን እንደ እንቦሳ ዘለሰች(ተደሰተች)።

## ስለእናም ትንቢትና ከገነት መቼ እንደወጣ?

እግዚአብሔር ለሥነ ፍጥረት ስድስተኛ ቀን በሆነው ዓርብ
አዲሶችን አዳምን በምድር መካከል ካለው **ከጎልጎታ** አፈር
እንሥቶ በሦስት ሰዓት ፈጠረው የሕይወት **መንፈስንም**
(ትንፋሽን) አሳድሮ የሚናገር የሚያስተውልና **የሚያውቅ**
አደረገው የብርሃንንም ልብስ አልብሶ ንጉሥ፣ ነቢይ፣ ካህን
አስተዳዳሪ አድርጎ በፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ላይ ሾመው።



ከገነት አጥንትም ሔዋንን ፈጠረለት። ኤዶም በተባለች ገነትም
አናራቸው **ሰባት** ዓመት በተድላ በደስታ ከኖሩ በኋላ አትብሉ
የተባሉትን ዕፀበለስ በልተዉ በዘጠኝ ሰዓት ከገነት ወጡ።

## የአዳም የሥልጣን ይረጃዎች

1ኛ በንጉሥነቱ የፍጥረታት ሁሉ ገዢ ነው
2ኛ በነቢይነቱ የጥፋት ውሃ ይመጣል ፍጥረት ሁሉ
ይሰጥማል ይሞታል ከስምንት ሰው በቀርም የሚቀር
የለም ብሎ ለልጁ ለሴት ትንቢትን ተናግሯል ይህም
ከ1926 ዓመት በኋላ በኖህ ዘመን ተፈጸመ።
3ኛ በክህንነቱ ነጭ ዕጣን ቀንዓተ ሰሊሖት ከሚባል ሽቱ ጋር
እያጠነ እግዚአብሔርን ያገለግል ነበር። 930 ዓመት
ሲሆነው በተፈጠረባት ዓርብ
ቀን በዘጠኝ ሰዓት አረፈ።
አዳም ከሔዋን በሞት ቀድሟል

አዳምና ሔዋንም ከገነት ወጥተው ለ5533 ዓመት በመላእክት
ተዘግታ ስትጠበቅ የነበረች ገነት በዕለተ ስቅለት የደሙን
ማኅተም /ምልክት/ ሰጥቶ በቀኝ በተሰቀለው ጥጦስ ምክንያት
ተከፈተች። ይህ ሁሉ ታምር የተፈጸመው እመቤታችን
አምላክን በመውለዷ ነውና እንዲህ አለ።

Scanned by CamScanner

17፡ 17ተፈሥሒ ድንግል እንተኢተአምሪ (ዘኢተአምሪ) ብእሴ።
ዘጸገይኪ ለነ አሐደ እምነሥላሴ
ወንድን የማታውቂ ከሥላሴ አንዱን ያስገኘሽልን ድንግል ሆይ
ደስ ይበልሽ ::
ኢንዘትዘብኖ ከበሮ ቅድመአዕላፈኢፍራም ወምኒሴ።
በኢፍራምና በምናሴ ወገን ፊት
ለተአምርኪ ትንግር ውዳሴ
ማርያም እጎቱ ለሙሴ።
የሙሴ እህት ማርያም ለታምርሽ /ለፈጣሪ ልጅሽ/ ምስጋና
ትናገራለች ትዘምራለች ዘጸ 15 ፡ 20-22።

## ሐተታ

በኢፍራምና በምናሴ ወገን ፊት ማለቱ ኢፍራምና ምናሴ
ለእኒ እንደ ሮቤልና እንደ ስምዖን ናቸው ብሎ መደበኛ
አድርጎ አስራሔል ያሰቡበ ስለሠሞቻቸው። ዘኁ 48 ፡ 5-1
ማርያምን የጠቀሰ ግን አስራሔል ባሕረ አደርትራን በተሻገ
ጊዜ የሙሴና የአሮን እህት ማርያም ከበሮን ይ
አያቀናቀንችላቸው ንስቲሉ የሚለውን አመስግናለች
የጠቀሰው ያንን ነው።



ፈጅ፡ 18ተፈሥሒ ባሕታዊት እንተጎጣአኪ መምሰለ
እስመተአምርኪ ኮነ ለነፍሰጎጥአን ሣህለ
ታምርሽ ለኃጥአን ነፍስ ምሕረት ሆኗልና በንጽሕና በቅድስና
ብቸኛ የሆንሽ፡- ምላሌ የሌለሽ ድንግል ሆይ ደስ ይበልሽ።
ሰማይ ለኪ ማርያም ይዌድሰኪ ልዑለ።
ሰማይ አንቺን ከፍ ከፍ አድርጎ ያመሰግንሻል
ምድርኒ ትገብር በዓለ
ጽጌፍቅርኪ (ክርሥኪ) ረስያ አክሊለ
ምድርም የፍቅርሽ አበባ የክብር ዘውድን ተቀዳጅታ ወይም
ልጅሽን እንደዘውድ አድርጋ የደስታ ቀንን ታክብራለች።
ሰማይ መላእክት ምድር ደቂቀ አዳም ናቸው። ሰማያት ስሙ
ምድርም አድምጪ ብሎ ነቢዩ ኢሳይያስ እንደተናገረ ኢሳ
1 ፡ 2።
መላእክት ደቂቀ አዳም ያመሰግኑሻል።
19ቀስተደመና ማርያም ትእምርተኪዳኑ ለናህ
ዘእግዚአብሔር ዒመኪ ለተዝካረምሕረት ወፍትሕ
ለምሕረትና ለፍርድ መታሰቢያ አድርጎ ያኖረሽ የናህ
የቃልኪዳኑ ምልክት ቀስተ ደመና ማርያም

Scanned by CamScanner

ህየንተቀሰፋ ለምድር ወእግሰና በእያንኑ።
ምድርን በጥፋት ውሃ ስለመደምሰሳ ስለ አጠፋት ፈንታ።
በእንተእሊ አሠርገዋ በጽጌ ኩሉ አቅማሕ
ከመበዝኃበት አሠርገው ለሰማይ ስፋሕ።
ሰፊ ሰማይን ስላር ቀጥር በሊላቸው ከዋክብት አንደ
አስጌጠው ሁሉ በአንች ምክንያት ልዩ ልዩ በሆኑ
አበባዎች ፍሬዎች ምድርን አስጌጣት ማለት በአንቺ
ምክንያት በምድር ሰን በጎ ታምራት ተደረገ

## የኖህ የትውልድ ዘመን የጥፋት ውሃን የደወል አመጣጥ

ኖህ ከአባቱ ላሜህ ከእናቱ ቤቲኤስ በ2256 ዓመተ ዓለም
ተወለደ።[1] ለአለም አሥራዮ ትውልድ ነው። ከጎናቸ
ዖምር ጎሳዎች አንደሚገበባ ከፋት አንደሚጥሳ ደጋጎችም
አንደሚያንሱ ሥን የለበሰ ሁሉ በውሃ አንደሚደመሰስ
አምላካቸ ምሥጢርን የሚያይ ሆነ ስለዚህም ፈቱ የተቋጠረ
ሆኖ ፈጽሞ ያለቅስ ነበር አምስት መቶ ዓመትም
ደንግልናውን ጠብቆ በአምላክ ትዛዝ የአለምን ሥን
ሊያለማል ከሆረ በኋላ ሴም ካም ያፌትን ወለደ። የጥፋት
ውሃ ይመጣ ዘንድ አለውና ከደብር ቅዱስ ሰንፈኤቸን

[1] ኖህ በ2256 ዓመተ ዓለም ተወለደ።



ቆርጠህ መርከብ ሥራ አለው ሠራ። በተፈጒሮ
ለመንፈሳዊም ሆነ ለሚንሻውም አገልግሉት የምንጠቀምበት
መጦሪያ የሆነውን ደወል ለመጀመሪያ ጊዜ ሥርዓት
የሠራልን ኖህ ነው። ይህም የመገልገያ ደወል ለ4642 ዓመት
ያህል ለሰው ልጅ ሁሉ አያገለግለ ይገኛል።

**የጥፋት ውሃ።** የሰማይ መስኮት ተከፍቶ በምድር ላይ አርባ
ቀን አርባ ሌሊት ዝናም ዘነመ ለአምስት ወር /ለመቶ ሃምሳ
ቀን/ ያህል በምድር ላይ ቀየ የጥፋት ውሃ በ2856[1] ዓመተ
ዓለም ግንቦት አስራ ሰባት ቀን ሆነ አነሆ ይህ የጥፋት ውሃ
ዘመን የዛፈ 4642 ዓመት ነው የኖህ መርከብም በአርመን
አገር በአንድ ሪጅም ተራራ ሜዳ ላይ አረፈች /ተቀመጠች/።
ይህም ተራራ ሰማር /አራራት/ ይባላል። ከእንግዲህ ወዲህም
ምድርን በጥፋት ውሃ አላጠፋም ሲል ሰቃል ኪዳኑ ማጽኛ
የቀስቱ ደመና ምልክትን አሳየው ዘፍ 9፡12።

ኖህ ሰባት ጊዜ ዓለምን አያ፡፡ል
1ኛ ከጥፋት ውሃ በፊት
2ኛ በጥፋት ውሃ ጊዜ
3ኛ ከጥፋት ውሃ በኋላ።

[1] የጥፋት ውሃ በ2856 ዓመተ ዓለም ግንቦት 17 ቀን ሆነ

Scanned by CamScanner

ዘፍ 20 ብኪ (ዘብኪ) ተባረክ ወተቀደሱ አሕዛብ

ትእምርተ ግዝረቱ ወዘርዑ ለአብርሃም አብ።

የአባታችን አብርሃም የዘሩና የግዝረቱ ምልክት ግርዛ አሕዛብ በእንቲ ተባረኩ ተቀደሱ ወይም በእንች የተባረኩ የተቀደሱ ናቸው።

## ስለአብርሃም ዘመንና የግዝረት ሥርዓት እጅግ

አብርሃም ከአባቱ ታራ ከእናቱ ኤድና በ3056 ዓመተ ዓለ ተወለደ[4]

ግዝረት:- በ3155 ዓመተ ዓለም ተጀመረ[5]

አብርሃም ከእግዚአብሔር የግዝረት ሥርዓትን ተቀበ ሥርዓትን ከሠራ እነሆ ዛሬ 4343 ዓመት ሆኖታል።

ነገር ግን ክርስቶስ በግዝረት ፈንታ የክርስትና ጥምቀ ሰጥቶናል ዘፍ 17÷9-15።

አብርሃም 175 ዓመት በዚህ ዓለም ኖሯል።

ጽጌድንግልናኪ በግዕ ለቤዛይስሐቅ ውዕይ

ማርያም ዕፀሳቤቅ

[4] አብርሃም በ3056 ዓመተ ዓለም ተወለደ

[5] ግዝረት:- በ3155 ዓመተ ዓለም ተጀመረ



ዕፀሳቤቅ ማርያም በድንግልና የወለድሽው ልጅሽ ለይስሐቅ ቤዛ /መድኃኒት/ ሆኖ የተሰጠ ነው።

## ስለ ይስሐቅ ዘመንና በስንት ዓመቱ እንደተሠዋ?

ይስሐቅ:- በ3156 ዓመተ ዓለም ተወለደ[6]

አብርሃም ልጅህን ሠዋልኝ በተባለው መሠረት ይስሐቅን ይዞ ለመሠዋት እጁን በዘረጋ ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ ከሰማይ ጠራና አብርሃም አብርሃም አለው እርሱም እነሆኝ አለ በብላቴናው ላይ እጅህን አትዘርጋ አንዳችም አታድርግበት አንድ ልጅህን ስኔ አልከለከልከኝምና እግዚአብሔርን የምትፈራ እንደሆንህ አሁን አውቄአለሁ አለ አብርሃምም ዓይኑን አነሣ በኋላውም አንድ በግ በዳር ውስጥ ቀንዱን ሳቤት በሚባል ሐረግ ተይዞ አየ አብርሃምም በጉን ወስዶ በልጁም ፈንታ መሥዋዕት አድርጎ ሠውቶታልና እንዲህ አለ።

ይስሐቅ በተወለደ በ22 ዓመቱ አስቀድሞ የእግዚአብሔር ወልድ ምሳሌ ሆኖ ተሠዋ

ይስሐቅ 180 ዓመት ኖረ ዘፍ 22÷1-15።

ወምሥራቅ ዘያዕቆብ ወላዲቱ ለሥርግው ኮከብ።

[6] ይስሐቅ:- በ3156 ዓ ተ ዓለም ተወለደ

Scanned by CamScanner

[illegible] ሆይ የሥርግው ክብር እናቱ አንቺ ነሺ
[illegible] አምላክ አምላክን ከሆንሽበ በር ያገለገልሽ ማለት
[illegible] ነው።

## ኢኒ ናኒዶ የትውልድ ዘመንና ወደ ምሥራቅ ጉዞ

[illegible] ዓመተ ዓለም ተወለደ[1] ወደ ምሥራቅ አገር
[illegible] አንቱ ላባን በቅንነት ሲያገለግል ኖረ
[illegible] እግዚአብሔር ባርኮለት ልጅና ሀብትን አግኝ
[illegible] ዮሳቦብ በዚህ ዓለም 140 ዓመት ኖረ

[illegible] መጽሐፍ ማእከለፈጣሪ ወፍጡራን
[illegible] ጽላተ /ትእምርተ/ ኪዳን
[illegible] ዕለተብርሃን
[illegible] እንደተናገረ በፈጣሪ እና በፍጡራን መካከ
[illegible] የቃል ኪዳን ማደሪያ /ምልክት/ የሆንሽ የብርሃን ቀ
[illegible] ማርያም ሆይ

[1] [illegible] 3216 ዓመተ ዓለም ተወለደ



ብኪ ይትፌሥሑ ዘንተጽጌ ጻድቃን
በንጉሥ ያሉ ጻድቃን በአንቺ ደስ ይላቸዋል።
ወብኪ ይወጽኡ ኃጥኣን እምደይን
ኃጥኣንም ከደይን በአንቺ ይወጣሉ

## ሐተታ

ዕለተብርሃን የተባለች ዕለተአሑድ ናት ሰንበተ ሰንበታት የተባለችውም በቀዳሚት ላይ ስለተሠራች። ሰንበተ ሰንበታት ያላትም የደስታ ፍጻሜ ስለሆነች ነው። ይህ ሁሉ በእመቤታችን ስለሆነ ደራሲው ለእመቤታችን ሰጠ።

ኀጽ፡ 22 ሰመዩኪ ነቢያት አለርእዩ ጎበዓተ
ንጉሠ ጽጌ ዕፁበ ወኖኀተምሥራቅ ኀትምተ
ሥውር ምሥጢርን ያዩ ነቢያት የተዘጋች የእዩባ ነገ
የታተመች የተቆለፈች የምሥራቅ በር አሉሽ ነቢያት ሁሉ
እግዚአብሔር በገለጸላቸው ምሳሌ መስለዋታል መኃ 4፡12
ሕዝ 44፡1-3
እግዚአብሔር ወሀበ ለቤተዳዊት ትእምርተ /ትንቢተ/
ከመትጸንሲ ድንግል ወትወልዲ ሕያውተ
ድንግል በድንግልና ሕይወትን እንደምትጸንሺ እንደምትወልጂ
እግዚአብሔር ለዳዊት ቤት ምልክትን ሰጠ ትንቢትን አናገረ።

Scanned by CamScanner

ኢሳይያስን ነገረ ክሙት

ነቢዩ ኢሳይያስም በግልፅ ተናገረ ኢሳ 7፣13-15።

የሮ 23 ተአምኒክ ማርያም ተሰብክ በአሪት

አመ ተሰጽዓኩክ ላዕሰ ምስሙለኮት

ላዕሰ ኮሙለኮት ጎራ አንድ በሆንሽ ጊዜ ድንግሽ በአሪት ተሰበክ

በዚአነኪ ሙሴ ሊቀ ነቢያት

ጸልልኒ በአዕጽቅክ ሐመልማላዊት (ሐመልማል) ዕፀት።

ሊቀ ነቢያት ሙሴ ያየሽ ለምለሚቱ ቁጥቋጦ በትርጓሜዬሽ ጎጥኚኝ ሸፍኚኝ በቃል ኪዳንሽ በአማላጅነትሽ አድኚኝ።

ሦክ ንብአትየ ያውኂ ጽጌክ አሳት

አሳት አዘየሽ አሾህ ንብአቱን ያቃጥል ዘንድ።

## ስለ ሙሴ ዕፅ ምሥጢር

ሙሴ በደብረኮሬብ ሐመልማል (የለመለመ ቅጠል) ከነበልባል ነበልባል ከለመለመ ቅጠል ጎጥ ተሞሐኦ አንዱ አንዱን ሳያጠፋው ሙሴ አያየ ሣጽንቀን መናዝር ነው ነበልባል የጌታ፣ ሐመልማል የእመቤታችን፣ ምሳሌ ዘጸ 3፣1-4።



ጽፀ 24 በትረአሮን ማርያም ዘሥረፅክ አንበሳተክል

መጽሃፍክ ጽጌ (ጽጌ ተአምር) በሕተሰትዮ ማያ ጠጠል

ላይተክሉሽ የበቀልሽ ውሃንና የሰማይ መዝን ሳትጠፈፈ

የታምር አዘዛን ያዝበሽ የአሮን ብትር ማርያም አንች ነሽ

መዘእንተዝ ያፈድ መንገርኒሶል

ምስለ ሱራፊል ያዋድስክ መያብል

ሐውር የኅውጻ መጽኄጸጻ በትአምርተመስቀል

ስለዚህም ድምፁ ደሰ የሚያሰኝ ያፈድ ከሱራፌል ጋራ አንድ ሆኖ ሐውር የኅውጻ መጽኄጸጻ በትአምርተመስቀል አያለ ያመሰግንሻል፡ የማያመረመር ክብር ነው።

## ስለ አሮን ብትር ያለ ውሃ መብቀል ታሪክ

ሙሴ መሰፍን አሮን ካህን ሆነው እግዚአብሔርን በሚያገለግሉ ጊዜ የሮቤል ልጆች በሙሴ ምስፍና /ሥልጣን/ የቀኑት ልጆች በአሮን ክህነት ላይ በምቀኝነት ተነሣሡ በዚህ ምክንያት ሙሴ እግዚአብሔርን ጠየቀ እግዚአብሔርም ከአሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል እየመረጥክ ብትሩን ሰብስበህ ከዚቱ መቅደስ አግባው አለው እንዳለውም አደረገ የአሮን ብትርም ውሃ ሳትጠጣ አብባ ለምልማ ለውዝ ገውዝ አፍርታ ተገኘችለች።

Scanned by CamScanner

ከውዝ መንፈሳት ያለው የሚበላ የተከለ እንጨት ነው።
እንደዚሁም ሁሉ እመቤታችን ንጽሐ ጠባይዕ ሳይጎድልባት
ሊያድፍባት ተገኝተለች በድንግልናም አምላክን ወልዳለችና
የአሮን ብትር አንቺ ነሽ አለ ዘኁ 17፣5-12።

## ቅዱስ ያሬድ ከሰራፌል ጋር በሚጎሌት ስለሚመስጥ

እግዚአብሔር በመላእክት ዜማ ሲመሰገን እንደኖረ ሁሉ
ለሰውም ልጅ እሱ ሊፈቅድ በሶስት የጎንት ወፎች ምክንያት
ቅዱስ ያሬድን ወደ ኢየሩሳሌም ስማያዊት ነጥቆ ሃያ አራቱ
የሰማይ ካህናት የሚያመሰግኑበትን ማኅሌት ገልጾለት
ማኅሌትን ተማረ። ወደምድርም ተመልሶ ከመላእክት
የሰማውን ዜማ ሲያመሰግን የሰሙ ሁሉ አደነቁ። ከዚህ በኋላ
ቅዱስ ያሬድ ወደ ቤተ ክርስቲያን ገብቶ በታቦተ ጽዮን ፊት
ቆሞ ፊጽሞ የከበርሽና የተመሰገንሽ ከፍከፍም ያልሽ የብርሃን
መውጫ የሕይወት መሰላል የሆንሽ የሚለውን ምስጋና
/እንቀጸ ብርሃን/ እስከ መጨረሻው ድረስ ተናገረ።

ዘፀፃ፡- 25ሥንኪ ጸገየ በልብሰአሮን ካህን
ክብርሽ በአሮን ልብስ ላይ ተገለጸ
ወፈረየ ወርቀ እምላለ ሮማን
በሮማን ፍሬ አምላልም የተሠራ ወርቅን አፈራ።



በተአምርኪ ድንግል ዘአገዮቱ መካን።
ወርትስ ጸናጽልኪ አማን
ኮነ መድል ፈቅደ እምወይን።
በታምርሽ መካን የጸነስችው ወርትስ በእውነት መርገፍ ነው።
ማለት ከወይን ይልቅ በገድሉ ዜና ደስ የሚያሰኝ ፈቅደ
ነው።
መካን የተባለች የፈቅደር እናት ናት ታሪኩን በተራ ቁጥር
፹፰ ይመልከቱ።
ታሪኩ፡- አሮን ወደቤተመቅደስ ሲገባ ወርቁን እንደ ኪስ
አሠርቶ ስድስቱን በፊት ስድስቱን በኋላ ከደረቱና ከትከሻው
ያለውን ልብስ ለብሶ ያንን እያሰማ ገብቶ ሲጸልይ ሕዝቡን
ይፈወስ ነበር እመቤታችንም የዓለም መድኃኒት ናትና
ልብስ የእመቤታችን፣ አሥራ ሁለት አዕናቁ የሐዋርያት፣
ድምፅ ማሰማቱ ሐዋርያት ወላዲተአምላክ ብለው
የማስተማራቸው ምሳሌ ዘጸ 28፣29-42።

ዘኍ፣ 26ማዕረረትንዚት ማርያም ዘዘመነ ጽጌ እንግዳ
ወዘመነኖረ ጽጋብ ዘዓመተረሀብ ፍዳ
በአዲሱ የአበባ ዘመን /ወራት/ የረሀብ ዘመን ለውጥ በሆነው
በጽጋብ የፍሬ ዘመን የተገኘሽ የትንቢት አዝመራ /መከር/
ማርያም ሆይ

Scanned by CamScanner

ዘኪ ሶልያ ክርስቶስ እየሱስ ክርሆ ሌልፍ።
ርክሩያ አመንሮኒኮ ርክምአውግረሁ ለይሁዴ።
ሶስኮ ሙሴ ቅድስናነኮም ወየሚብ ወንዳ
ኢያሱ ክርሆ ኢየሱስ ስርዓትና ተራራምችና ኮረብቶች ያሚ
ሳኬሆ ሚር ኑሙ ኮሶት ይፈስክል አራት ወንጌል ይሰክ
ብሎ ሶሎርሆሙ ነንጅ ተፈጸመ። ኢዩ 3፣ 18

## ስለ ክርዩ ኢየሱስ የራብና የጥጋብ ዘመን

ርክሩ ኢየሱስ ዘመን የክሩ ሰምች የእግዚአብሔርን ቃ
በአመጠረቀቅው ምድር የዘሩባትን እንዲታበቅል ክፎ
ሠራም እንደሚሆን እግዚአብሔር ለክርዩ ኢየሱስ ትንቢት
ሥጭንሩ ክርዩችሁ እንደሚመለሱ ድረስ የረዘዘ ዘመን ሆነ
ክር ርክሩ ትምክርትም ክለመኑ በኋላ በረስትን ስለ አገ
እንዲህ አለ። ሐዋርያውን በየቃሉ ለመዘርዝር የትንቢ
እንመራ ማርያም ያለው ጌታ ክሰሳ እንደሚወለድ ትንቢ
ሰመንሩ፤ ዘመን ረዘዘ ፍሬና፤ የሐና የኢያቄም አዘን፤ ዘመ
ፍሬ ደጋብ፤ ሐና ኢያቄም አመቤታችንን እግኝተ
መዲታቸው፤ ዘመነ ጽጌ እንግዳ፤ ለዓለም ሁሉ አዲስ የሆ
ጽጌ ክርስቶስን እመቤታችን ማስገኘቷ ብሎ ይመክላል።



ጌ፡ ርግ ዘክርያስ ርእየ ሰወርኦክባዮ በሠርቁ
ተአምረኪ ለዘይት (ዘዘይት) ማዕከለ ክልኤ አዕሁቱ።
ማርያም ጽጕን ለብርሃን ተትዋመወርቁ።
የብርሃን የወርቅ መቅረዙ ጽጕን ማርያም ክርዩ ዘክርያስ
በሁለቱ የወይራ አዕሁት መካከል በየካቲት ወር ምልክትሽን
እየ።
ዕዝራኒ በጎኖም አመወዐለ ውዱቁ
ዕዝራም በምድረ በዳ ወድቆ በዋለ ጊዜ (ሱባዔ በጾ ጊዜ)።
ለጎብረገጽኪ ጽጌ ጎተወ መብረቁ።
ጽጌ የፊትሽ ደምግባት ብልጭታው በፊቱ ብልጭ አለ
/አንጸባረቀ/

## ስለ ወርቅ መቅረዝ ምሥጢር

ክርዩ ዘክርያስን የእግዚአብሔር መልአክ በሚያነጋግረው ጊዜ
ሁለንተናዋ ወርቅ የሆነ የወርቅ መቅረዝን /ማብራያ ያይ
ክር፡ በዘይት ማሰሮ ራስ ላይም በቀኝና በግራ ሁለት የወይራ
ዛፎችን አይቷል እነዚህም ቤተ መቅደስን የሚሠሩ ካህኑ
ኢያሱ ዮሴፆ እና ዘሩባቤል ክኩ
ዘካ 1፡7፤ ምዕ 4፤1-4 ::

Scanned by CamScanner

## ስለ ዕዝራ ጸሐፊነትና ዕርገት

ዕዝራ ሊቀኤል ክሉዊ ወገን የሆነ የእግዚአብሔርን ቃል
የሚናገር እና እግዚአብሔር ግሩም የሆነ ምሥጢርን
ይገለጽለት ሊሆን በዚህም ጽዮንን በሴት አምሳል አይቶ
ደንግጦ እስኪወድቅ ድረስ ፊቷ ድንገት እንደ መብረቅ
እንዳበረቀ ያችም ሴት ሊየሩሳሌም ናት ዳግመኛም የነቢያት
መጻሕፍትና የአባቶችን ትውልድ የያዙ መጻሕፍት
ተደምስሰው መዮፋታቸውን በአሰበ ጊዜ ስሙ አርፋድ ወደ
ሚባል ጌዳም

ገብቶ የምድረ በዳውን ፍሬ ብቻ እየተመገበ በጾምና በጸሎት
ምሕላ ይዞ በአርባ ቀን ጾም ውስጥ መጻሕፍትን ጻፈ።
በመጨረሻም መላእክት ዕዝራን ደጋግ አባቶች /ሄናኒ
ኤልያስ/ ወዳሉበት ብሔረሕያዋን በሕይወት አላረጉት ዕዝራ
ሱባዔ ገብቶ መጻሕፍትን በ4935 ዓመተ ዓለም ጻፈ።[፰] ዕዝ
ሱቱ 8 ÷23-28 13÷40-49።

ጽጽ÷28 ብውዓን ኃጥአን አለ ተአምረኪ ተወክሉ።

እምጻድቅ አሰጢፋ ዘይትሜነዝ በጽሣ ገድሉ።

[፰] ዕዝራ በ4963 ዓመተ ዓለም መጻሕፍትን ጻፈ



ጻድቅ ነኝ ብሎ በገድሉ ኀሚመካ አስጢፋ ይሉት ኃጥአ ነን
ተስፋ አድርገዉ ያመኑ ኃጥአን የተመሰገኑ ናቸው።
እንበሌኪ ድንግል ለጽጌ መለኮት አባሉ።
የመለኮት ማደሪያ ድንግል ሆይ ያለእንች
ኅድጊሰ አድነኖተዓለም ኮሉ።

አድኅኖ ነፍሶሙ እምኵነኔ ነቢያት ኢነበሉ
ነቢያት ዓለምን ሁሉ ማዳን ይቅርና የራሳቸውን ነፍስ እንኳ
ከኀጥዕ ማዳን አልቻሉም ነገርስቶስም ሊሐዋርያው ቶማስ
ያላመነህ አትሁን ቢለው ጌታዬ አምላኪየ ብሎ በመለሰ
ጊዜ ስለ አየኸኝ አመንሃል ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን
ናቸው ብሎ ተናግሯል ዮሐ 20÷27-30።

ስለ ነቢያት ደም አለማዳን ደግሞ ቅዱስ ኤጲፋንዮስ
እንዲህ አለ ወሰበርእየ ከመኢባቍዕ /ኢበቍዐ/
ለአድኅኖተዓለም ደመነቢያት ቅዱሳን እምደመአቤል ጻድቅ
እስከደመዘካርያስ ወልደበራክዩ ፈነወ ለነ ወልዶ መድኀነ
ወመጌዝወ ከመ ይባልህ ወይቤዙ
ከጻድቁ ከአቤል ደም ጀምሮ እስከ በራክዩ ልጅ እስከ ዘካርያስ
ደም ድረስ የቅዱሳን ነቢያት ደም ዓለምን ለማዳን

እንዳልጠቀመ ባየ ጊዜ ፊጽሞ ያድን ዘንድ መድኃኒት የሚሆን ልጁን ላከልን ብሏል።

## ስለ ትምክህተኛው እስጢፋኖስ

እስጢፋኖስ የሚባል ባሕታዊ ነበር ከዛፍ ላይ ወጥቶ ሲጸልይ በአርሻ ሥራ የሚተዳደሩ ሁለት ሰዎች ለተግባራቸው ወደ ዱር ወርደው ሳለ አንዱ ባሕታዊውን በዛፍ ላይ ተሰቅሎ አየው ዓይኖውን ምንድነው? ብሎ ቢጠይቀው ዓይኖውም ሊጸድቅ ነው የተሰቀለው አለው።

ያ ሰውም መንፈሳዊ ቅናትን ቀንቶ ከጸደቅሁስ ብሎ ከዛፉ ላይ ሊወጣ ሲል የቆመበት ዛፍ ቢንጠል ወድቆ ተሰብሮ ሞተ በጎ ሥራን አስቢልና ነፍሱን መላእክተ ብርሃን ወደገነት ይዘዋት ሲሄዱ እስጢፋኖስ በራእይ አየና እኔ ይህንን ያህል አርባ ዓመት ቅጠል እየበላሁ ተጋድዬ ክብርን ሳላገኝ እርሱ በአንድ ቀን ይጸድቅ! ብሎ ቢመካ እግዚአብሔር ትቢትንና ትምክህትን አይወድምና ከዛፍ ላይ ወድቆ ሞቷል ነፍሱንም መላእክተጽልመት ወደሲኦል ወስደዋታል።

### እንዲህም የሚል ሌላ ታሪክ አለ፦

በገዳም የሚኖር አንድ መነኩሴ በሰንበት ቀን ወደ ሩቅ አገር ሰ' ድ ሰዓት ቢመሸበት ጨለማንና አራዊትን



ፈርቶ ከዛፍ ላይ ወጥቶ ሳለ አንድ ሌባ ከዛፉ ጥግ በራ አርፎ ከበላ በኋላ ከደስታው ብዛት የተነሣ ወደላይ ሲያንጋጥጥ (ሲመለከት) በዛፉ ላይ ያ መነኩሴ ተሰቅሎ አየውና ጌታዬ ማነህ ? ብሎ ቢጠይቀው የሌላ ገንዘብን የማልቀማ ወንበዴ ያልሆንኩ እኔ ጻድቅ መነኩሴ ነኝ ኑሮዬም በጾምና በጸሎት ነው አለው።

ወንበዴውም ለነፍሱ ምን ይሻለኛል ኑሮዬ በክፋትና በበደል ነው አለው። መነኩሴውም ንስሓን አሰኘህ ዘንድ ወደኔ ና ሲለው ያንጊዜም ሌባው ከመነኩሴው አግር በታች ወድቆ አለቀሰ።

ወዲያውኑ አራዊት መጥተው በሉት ንስሓ ገብቷልና ነፍሱን መላእክተ ብርሃን ገነት ሲያስገቧት ያ መነኩሴ በራእይ አያቸው መንግሥተ ሰማያት የሌቦችና የቀማኞች ዋሻ ሆነች እኔ ዘመኔን ሁሉ በከንቱ አጠፋሁ ብሎ ማንኛውንም ኃጢአት ሠርቼ አንድ ቀን ንስሓ እገባለሁ ብሎ ከዛፉ ላይ ወርዶ ወደ ኃጢአት ሥራ እሰማራለሁ ሲል ወዲያውኑ አራዊት ተሸምተው በልተውታል።

ነፍሱንም የጨለማ ሠራዊት የሆኑ አጋንንት ወደ ሲኦል ወስደዋታል። ስለዚህ በገድሉና በጸሎቱ ከሚመካ ይልቅ አማላጅነትሽን ያመኑ ኃጥአን የተመሰገኑ ናቸው አሉ።

Scanned by CamScanner

የኦሪሳዊውንና የቀራፊቱን የጥቦስንና የዳክርስን ታሪክ ይላል

ይላል ሉቃ 18 ÷ 9-15 ፤ 23 ÷33-44

እግዚአብሔርን ከሰማይ የማን ፍቅር ሳበው?

ወእውረዶ ውስተ ምድር እስከነ ለሞት አቅረቦ

ለሞትም እስከ አቀረበው ድረስ ወደ ምድር (ወደዚህ ዓለም) ከሰማይ

ማን አወረደው?

እዝለለ ፍቅርኪ ጽጌ ሥነ አምሳል ዘአልቦ

ጽጌ ምሳሌ የሌለው ፍቅርሽ ነው አንጂ። ወይም ምሳሌ

ከሌለው ፍቅርሽ በቀር ማን ሳበው?

ብውዕ ዘንተ ኀልዮ ወዘንተ ዓቂቦ

ይህን አስቦ ይህንም ጠብቆ

ለተአምርኪ ማርያም ዘየአምር የብቦ

ማርያም ሆይ ዕፁብ ድንቅ ስሆነ ለታምርሽ ምስጋና

የሚያቀርብ የተመሰገነ ነው። ንጉሥ ዳዊትም ምስጋና

የሚያቀርብ ምስጉን ነው ሲል ተናግሯል መዝ 88÷15።

ፀ÷ 30ወይን ውሜኅሌት ያስተፈሥሑ አልባበ

ዘፈንና ወይን ልብን ደስ ያሰኛሉ

ወአምክልዔሆሙሰ ነጊረ ስብሐትኪ ካዕበ።



ከነዚህም ከሁለቱ ይልቅ ምስጋናሽን መናገር በእጥፍ ደስ

ያሰኛል መዝ 103÷15 ሲራ 40÷20-22

ለከናፍርየ ድንግል አንተ አልብኪ ስብሳበ

ይሰብሑ ተአምረኪ አስተጥዒሞን ንባበ

እምጽጌ (ጽጌ) አጥባትኪ እሙ ቅብዒዮን ሐሊበ

ከንፈሮችን የማታውቂ የእምላክ እናቱ ድንግል ሆይ ለታምርሽ

ከንፈሮቼ አነጋገርን አጣፍጠዉ አስማምተዉ ምስጋናን

ያቀርቡ ዘንድ ከንፈሮቼን ከጡቶችሽ አበባ ወተትን (እንደ

ቅቤ አበባን) ቅቢያቸው እንዲጣፍጡም አድርጊልኝ።

## በበረከት ወተት ስለተፈወሰው በሽተኛ

በደሉን መናገር የተሳነው አንድ ካህን ነበር ነገር ግን

እመቤታችንን በጣፈጠ አንደበት ማመስገን ይወድ ነበር።

ከዕለታትም በአንድ ቀን ያ ካህን በጽኑ ደዌ ታመመ

ከበሽታው ብዛት ጋራ ጋኔን ይዞት ነበርና ራሱን ሳተ

ሰውነቱንም እየቆረጠ ይጥል ጀመር ስለዚህም ከንፈሩን ቆረጠ

ምላሱንም አኘከ እየደበደቡ በሠንሰለት ቢያሥሩትም ፈጽሞ

ሊተው አልቻለም ከደዌው ፅናት የተነሣ ይራገጣል

ነሽታውም እንደሞተ ሰው እንዳይንቀሳቀስ ያደርገዋል።

Scanned by CamScanner

ያዩትም ሁሉ እጅግ አዘኑ ያልቁንም በዚህ ከፍተኛ ደዌ ላይ
እንዳለ ሌላ ከባድ ችግር ደረሰበት ከአልጋውም መውረዱ
አቅቶት የአልጋ ቁራኛ የደዌ ዳኛ ሆነ ሰዎችም እነሆ ሞቱ
ደረሰ ይላሉ በአንዲት ቃልም የምሕረት እናት ላምትሆነ
ለእመዛኙትን የሕይወት መገኛ ሆይ የነዳያን ተስፋቸው
ያዘኑትን ሁሉ የምታረጋጊያቸው የሚያመሰግኑሽ እኒህ
ከንፈሮቻቸውን አትመለከቺምን ስላምታሽን እያጣፈጡ ምስጋናሽን
እየተናገሩ በፍቅር የሚናገሩት አንደበቶቻቸውንም ከቶ
አትመለከቺውምን እያሏ ተናገረ ይህንንም እየተናገረ ሳለ
እመቤታችን ቡለጸችለት ጽሑት ከሆኑ ጡቶችዋ የታምር
ወተት ፣ በከንፈሮቹና በምላሱ ላይ ቀቢቸው በዚህም ሊጀዙ
ከሚያሠቃየው የሽታ ተፈወሰ መዳኑን ያዩ ሁሉ እጅግ
አደነቁ በተሰጠውም በምስር አገር የሚኖር ዓይኖቹ
የታወሩ ብዙዎችን የበረከት ጡት የዳነ ስሙ ዮሐንስ
የሚባል መነኩሴ ሰዓቢህም ይሰብሓ ተአምረኪ አስተምኅፂሞን
ንባበ አምላ ኢ አነኳትኪ እሙ ቅብዓዮን ሐሊበ አለ።

31 ሐዋዝ በኢተስዮ መዝሙረማኅሌት ወመሰንቆ
የዘፈንና የመሰንቆ ዜማ በመጠኖ ቤት ያምራል
ወእምኔሁ አንም ሰሚዓው ዳሌኪ ለዘተዐውቆ



ከእሱ ይልቅ ለሚያውቀው ሰው ምስጋናሽን መስማት
ያምራል ይጣፍጣል ሲራ 35 ÷5-7
ማርያም ለኃጥእ ዘጸገይኪ ጽድቆ
ማርያም ለኃጥእ ጽድቅን ያስገኘሽለት
መንክር ተአምርኪ ወነፍስየ ጥቀ ትጤይቆ
ታምርሽ ድንቅ ነው ሰውነቴም /ነፍሴ/ በእጅጉ ትረዳዋለች
መብዝኅቶሰ በጽሑፍ (ለጽሑፍ) ኢይክል ጕልቆ
ብዙውንስ ግን በመጻፍ (ለመጻፍ) መዘርዘርን መፈጸምን
አልችልም
ዮሐ 21÷32 ለዘኢይሰቲ ወይነ ምንትኑ /ምንት ውእቱ/ ሕይወቱ
ሲራክ ይቤ እስመትፍሥሕተልብ ውእቱ
ወይንን ለማይጠጣ ሰው ሕይወቱ (ኑሮው) ለምንድን ነው
ሲራክ ወይን የልብ ደስታ ነው ይላልና መዝ 103÷15
ሲራ 34÷26-28.።
ተአምረኪ ማርያም ዘይጥዕም እምነዝንቱ
ወእብሐተፍቅርኪ ጽጌ ዘያስተፈሥሕ ሥነ ርእየቱ
ለዘያስተሐቅር በመንኖ ሕይወት አልቦቱ
ማርያም ከወይን ይልቅ የሚጣፍጥ ታምርሽንና
መልኩ ለማየት ደስ የሚያሰኝ የፍቅርሽ ምስጋና አበባንም
በመናት የሚያቃልል ካለ ሕይወት የለውም።

Scanned by CamScanner

ምሥጢሩ፡- ወይን ለሰው የሥጋ ሕይወት ሆኖ ደሙ እንዲያሰኝ የሰው የነፍስ ሕይወቱ ደመ ወልደእግዚአብሔር ነው ኃጢአትም ገብቶ ለተቀበለው ሰው ደስታ ነው። ደመወልደእግዚአብሔርን ለማይቀበል ምን ሕይወት አለው? ሥጋው ደሙ ለሰው ደስታ ተሰጥቷልና ይህን መናገር ነው

## ሲራክ ስለተነግበት ዘመን

ሲራክ የተነሣ እስራኤል ከባቢሎን ምርኮ ከተመለሱ በኋላ በዘሩባቤል ዘመነ መንግሥት ነው ማስረጃው በም 49÷11 ላይ ዘሩባቤልን እንዴት እናገነው! አሱስ በቀኝ እጅ እንዳለ ቀለበት ነው ብሎ በክብር አወድሶታል ትውልዱ ከሌዋውያን ነገድ ነው ስለቤተመቅደስም ክብር የተናገረ ጠቢብ ነው ቅዱስ ሥጋው ክቡር ደሙም በንስሓ የሚሰጥ በቤተ መቅደስ ነውና።

ሲራ፡- 33 እስከ መነነቶ ሚልኮል ቅድመታቦተሕግ ከመ ዘፈነ
ንጉሠ እስራኤል ኪያኪ ዘጸገየ ሥነ
ኪያኪ ሥነ አንድ ወገን። እንቺን ያስገኘ የእስራኤል ንጉሥ ዳዊት ሚልኮል እስከናቀችው ድረስ በእግዚአብሔር ሕግ ታቦት ፊት እንዳመሰገነ
ቅድመገጸሥዕልኪ ድንግል እዘፍን እነ



ድንግል ሆይ እኔም በሥዕልሽ ፊት እዘምራለሁ።
ዘይሜንን ተአምረኪ ወስብሐተኪ ሙርሳነ
ድንቅ ታምርሽንና የቀረበ መንፈሳዊ ምስጋናሽን የሚነቅ በአፈ (በጎበ) መላእክት ወሰብአ ለይኩን ምኑነ
በመላእክትና በሰው አንደበት /ዘንድ/ የተረገመ ይሁን

## የንጉሥ ዳዊት ምስጋናና የሚልኮል ትቢት

እግዚአብሔር የአቢዳራን ቤት በታቦተ ጽዮን ምክንያት በባረከ ጊዜ ከአቢዳራ ቤት የእግዚአብሔርን ታቦት ንጉሥ ዳዊት ወደ ከተማው አመጣ በደስታና በሙሉ ኃይሉ በእግዚአብሔር ፊት ያመሰግን ነበር። ያን ጊዜ ሚስቱ ሚልኮል በመስኮት ሆና አየተመለከተች በልቧ ናቀችው ንጉሥ ዳዊት ግን ምስጋናውን አያመሰገነ ታቦተ ሕጉን በክብር ድንኳን አስቀመጠ። የድኅነት መሥዋዕትንም በእግዚአብሔር ፊት ሠዋ 2ኛ ሳሙ 6÷12-18።

ሲራ፡- 34 በኵናተአላት ዘይነድድ ዘየዐቅበኪ ሱራፌ
ወአጼነወ መዓዛኪ ሄኖክ ጸሐፊ
ጽጌዕፀ ገነት ማርያም ዘኢትትነገፊ

Scanned by CamScanner

ስራፊ መልአክ የእሳት ፍላፃ የእሳት ሰገባ ይዞ የሚመጣው፣ መጎዛሽንም ጸሐፊ ሄኖክ ያሸተተልሽ የሚታወቅ የሚተዋ
የገነት ዛፍ አበባ ማርያም
አስቢሕ ተአምረኪ በእደ መልአክ ኃይል ሲያፊ
አርእስተ ፀርየ ከመጽጌ ፍጡነ ንግፊ (ግድፊ)።
ታምርሽን እናገር ዘንድ በሚቆርጥ በኃይል መልአክ አየ
የጠላቶቿን ራሶች እንደ አበባ በቶሎ ቆርጠሽ ጣዪ።
ታሪክ፡ አዳምና ሔዋን ዕፀ በለስን በልተው ከገነት ከወጡ
በኋላ በድፍረት እንዳይዙ መላእክት ገነትን እንዲጠብቁ
እግዚአብሔር ማዘዙን መናገር ነው ሄኖክም በሕያውነት ዐርጎ
ሥጋ ከለበሰ ሁሉ ቀድሞ ገነት የገባ መሆኑና በገነት መልኳም
ሽታ ውስጥ መኖሩን ማስረዳት ነው ዘፍ 3፣23 እስከ ፍጻሜ
ፃሪ፡ 35 ከመይትፈሣሕ ጻድቅ ሶበይራኢ በቀለ
ጻድቅ ሰው ፍርድ ሲመለስ ባየ ጊዜ ደስ እንዲለው
በተበቅሎ ፀር አርእዩ ዘተአምርኪ ኃይለ።
ጠላትን በመበቀል የታምራትሽን ኃይል ግለፊ አሳየ
መዝ 47፣10
እፎ የሐየ እመአምላክ እንተክያክ ጸአለ
የአምላክ እናት ማርያም አንቺን የሰደፀ እንዴት በሕያውነት
ሊኖር ያገባዋል?



ኮኑ በፍትሐጽጌኪ ይሙት ተብሀለ
ዕለ አቡሁ ወእመ ዘአሕሠመ ቃለ
እናት በአባቱ ላይ ክፉ ቃልን የተናገረ በልጅሽ ፍርድ
መት ተብሏልና። ዘዳግ 27፣16።

## ሐተታ

ድቅ ይደሰታል ማለት በንስጥሮስ ሞት ጻድቅ ቂርሎስ
ደሰታል ምስጋና ይግባትና እመቤታችንን ወላዲተአምላክ
ይደለችም ብሎ ነበርና በሊቁ ቂርሎስ መንፈሳዊ ውግዘትና
ሎት ተቀሥፏል ስለዚህ ጻድቅ ቂርሎስ ይደሰታል ማለት
ንስጥሮስን ከሀዲት ለሚከተሉ ሁሉ ይህ ተጻፈ።

## ለእመቤታችን ሥዕል ስላልሰገደ መናፍቅ ሞት

አስክንድርያ አገር ቀልሞን በሚባል ቦታ በእመቤታችን ስም
ተሠራች ቤተክርስቲያን ነበረች የገዳሙ አስተዳዳሪ ሰሎሞን
ባላል። በዚያች ቤተክርስቲያንም ካለች ከእመቤታችን
ሥዕል ብዙ ታምር ይደረግ ነበር።
ገዳሙም አስተዳዳሪ ለሥዕሏ ሦስት ጊዜ ሲሰግድ ከእርሱ
ሩ አራት ሰዎች ነበሩ። እሱን አይተው ሦስቱ ለሥዕሏ
ገዱ እንደኛው ሠይጣን በልቡ አድሮበት ለድንግል ማርያም
ስጋና ይሁንና የሰው እጅ ለሠራው እንዴት እሰግዳለሁ?

Scanned by CamScanner

ብሎ ተጠራጠረና በሥዕሏ ተዘባበተ። በዚያችም ሰዓት ምላ
ተሳልጉሎ ከከንፈሮቹ አንድ ስንዝር ያህል ወጣ
ወደ ላያና ወደታች ወደቀኝና ወደግራ እያለ ጥርሶቹን
ያፋጫ ነበር። ያንጊዜም የገዳሙ አስተዳዳሪ እግዚአብሔ
ይለምንለት ጀመር እመቤታችንም ለገዳሙ አስተዳ
አተጸልይለት በእኔና በልጄ ላይ ስድብን ፈጽሟልና ከሰ
የሞት ፍርድ ተፈርዶበታል አለችው። ወዲያውኑ በክፉ ሞ
ሞታልና ወደ ሲኦልም ወርዷልና አፎ የሐዩ እመአምላ
እንተክያኪ ጸአለ የአምላክ እናት ማርያም ሆይ አንቺን የሰ
እንዴት ይድናል? አለ።

ገጽ፣ 36አርምሞትኪ ማርያም ኀለፈ እምአንክሮ
**እስክንሬኢ** ሕዝብኪ ለተአምርኪ ግብሮ
**ማርያም** የታምርሽን ሥራ እኛ ወገኖችሽ እስክምናይ ድረስ
**ትግሥትሽ** ኮማስደነቅ አለፈ።
**ገነትኪ** ትጽጊ (ትጽገይ) ሰላመ ወተፋቅሮ
ገነትሽ (ቤተ ክርስቲያን) ሰላምንና ፍቅርን ታገኝ ዘንድ/ታ
እለያማስኑ ለአፀደ ወይንነ ወናሮ
ቈናጽለ ኀውሳነ አፍጥኒ አሥግሮ
የወይን ቦታችንን የሚያጠፉ ትናንሽ ቀበሮዎችን ፈጥነሽ አጥፊ
የታምርሽን ሥራና የማኅሌትሽን ምስጋና የሚያቃልሉትን ሁ



አጥፊ የማኅሌትሽ ምስጋና ክብር በመላእክት ዘንድ ይሰማ
መኃ 2፡15።

37 ምሥጢረመንግሥት ሀናይ ለንቢዕ።
የመንግሥትን ምሥጢር መጠበቅ
ወግብረ ጽጌኪ በክብር ለኪሂት
የልጅሽንም ሥራ በክብር መናገር ያማረ የተገባ ነው።
ሩፋኤል መልአክ በስመ ይቤሉ ለጦቢት
መልአኩ ሩፋኤል ለጦቢት እንደ ነገረው።
ተአምረኪ ማርያም ለዘየኀብዕ ስሑት
ታምርሽን የሚክደውን መናፍቅ ሁሉ
ትኅብያ ምድር ኪያም አስመ አኀዘ ቅንዓት
በከመነብዑቶ ለዳታን ትካት
ቅናት ይዞታልና ምድር ቀድሞ ዳታንን እንደዋጠችው
በሕዩጠቴ ኢያለ ምድር ትዋጠው።

## ስለ መልአኩ ሩፋኤልና ስለ ጦቢት ምሥጢር፡-

ጦቢት እውነተኛና መጽዋች ሰው ነው በመልካም ሥራና
ምጽዋትን በመስጠት ፀንቶ ይኖር ነበር መልአኩ ሩፋኤል
ለሱና ለልጁ ጦብያ እግዚአብሔር ያደረገላቸውን መልካም
ሥራ ሁሉ እንደመንግሥት ምሥጢር ሊሸሽጉት አይገባም

Scanned by CamScanner

ርእግዚአብሔርን ሃትሩፋት ሥራ በከብር ሊገልጡት ይገ
ብኑ አስተምኅርቶልና እንዲህ አለ ጣኪ 12፣11-12።

## ምድር በሕይወት እያሉ ያስጠመቃቸው ሰዎች ታሪ

ውትና ማር ከምታፈስሰው ምድር ያወጣሽን አይብቃህም
ርግመህ በእኛ ላይ ራስህን አለቃ ታደርጋለህን ባሉ ጊዜ መ
እድግ ተቆጣ እግዚአብሔርንም ወደ ቍርባናቸ
አትመልከት አኔ ከእነርሱ አንድ አህያ ስንኳ አልወሰድሁ
ከእነርሱ አንድ ሰው አልበደልሁም አለው እግዚአብሔር
ሙሴንና አሮንን ከዚህ ማኅበር መካከል ሽሹ ሁሉን በቅጽ
/እንደ ዓይን ጥቅሻ/ አጠፋቸው ዘንድ አላቸው እነርሱ
በግምባራቸው ወድቀው አምላክ ሆይ
አንድ ሰው ኃጢአት ቢሠራ አንተ በማኅበሩ ሁሉ ላ
ትቆጣለህን አሉ እግዚአብሔርም ሙሴን ለማኅበሩ ከፉ
ከዳታንና ከአቤሮንም ማደሪያ ዙሪያ ሽሹ ብለህ ንገራቸ
አለው። ሙሴም ተነሥቶ ወደ ዳታንና ወደ አቤሮን ሄ
የእስራኤልም ሽማግሌዎች ተከተሉት ማኅበሩንም እባካች
ከእነዚህ ክፋዎች ድንኳን ሽሹ በኃጢአታቸውም ሁ
እንዳትጠፉ ለእነርሱ የሆነውን ሁሉ አትንኩ ብ
ተናገራቸው እነርሱም ሸሹ።



ያሉን ቃል ሁሉ መናገር በፈጸመ ጊዜ ከዙሪያቸው ያለው
መሬት ተሰነጠቀ ምድሪቱም አፍዋን ከፍታ እነርሱንና
ቤተሰቦቻቸውን ለቀሬም የነበሩትን ሰዎች ዕቃዎቻቸውንም
ሁሉ ዋጠች ምድሪቱም ተዘጋችባቸው እነርሱም
በሕያዋኑ ሲኦል ወረዱ ከንባኤውም መካከል ጠፉ
በቀሬም ምክንያት ከሞቱት ሌላ በመቅሰፍቱ የሞቱት አሥራ
አራት ሺህ ሰባት መቶ ነበሩ አሮንም ወደ ሙሴ ወደ መገናኛ
ው ድንኳን ደጃፍ ተመለሰ መቅሰፍቱም ተከለከለ ዘኍ16፣1
እስከመጨረሻው ይመልከቱ ምድር ሰዎችን እስከ
ሕይወታቸው የዋጠችበት ዘመን

በኖህ ጊዜ በ2856 ዓመተ ዓለም በገዘሙት ምክንያት፡-
ከ1013 ዓመት በኋላ በ3843 ዓመተ ዓለም በእስራኤል ነግነት፡-
ምክንያቱ ትቢትና ምድራዊ ሥልጣንን መሻት።
ከሦስት ዓመት በኋላ በሙሴና በአሮን አገልግሎት ጊዜ
በዳታንና በአቤሮን 3845 ዓመተ ዓለም ነው
38 ዘሰ ይብል አፈቅረከ ወኢያፈቅር ተአምረከ ክርስቲያናዊ
እወድሻለሁ የሚል ነገር ግን ታምርሽን አላምንም አልወድም
የሚል ክርስቲያን
ኢክርስቱን ውእቱ አይሁዳዊ ወሠርፀእስጢፋ ሐሳዊ

Scanned by CamScanner

እሱ የከሐዲው አስጢፋ ወገንና አይሁዳዊ ነው፣ ማለት
ከአይሁድ ወገን የሆነ እንጂ የተጠመቀ ክርስቲያን አይደለም
ወይም ክርስቲያን አይደለም የከሐዲ አስጢፋ ወገን ነ
እንጂ።

እንሰ እቤ በማኅሌተ ሰሎሞን ወልደ ሰንቃዊ
አፈቅሮ ለፍግዕኪ ወሰተ ይሁዳ ወሌዊ
ከመመርዓቶ ያፈቅር ጽጌኪ መርዓዊ
ሙሽራ ልጅሽ ክርስቶስ ሙሽራዪቱ ቤተ ክርስቲያንን
እንደሚወድ የይሁዳ የሌዊ ልጅ ሆይ እኔ በዘማሪው ዳዊት ልጅ
በሰሎሞን መኃልይ ፍቅርሽን (ምስጋናሽን) አወደዋለሁ፡

ም ሥጢሩ፡- እመቤታችን ከቤተ ክህነት ከቤተ መንግሥት
መወለዷን መናገር ነው። የበገናና የመለከት የመጀመሪያ
መሠረተ ግኝት በመጀመሪያው ላሜህ ልጅ በዩባል /ኢዮቤል
ዘመን በ300 ዓመተ ዓለም ገደማ ነው[9] ዘፍ 4፡21።

## ስለመናፍቁ አስጢፋ ታሪክ

አስጢፋ የሚባል መናፍቅ ነበር እግዚአብሔር ከዓለሙ ሁሉ
መርጦ ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ ላከበራት
ለድንግል ማርያም ምስጋና ይግባት፡- በእርሱ ተሰቅሶ

[9] በገናና መለከት በ300 ዓመተ ዓለም ተጀመረ



ዓለሙ ሁሉ ለዳነበት ክቡር መስቀሉም ክብር ይሁንና
ለማርያምና ለመስቀል ስግደት አይገባም ብሎ የክህደት
ትምህርትን ሲያስተምርና ብዙዎችን ከዶ ሲያስክድ የነበረ
ሲሆን የኢትዮጵያ ንጉሥ አጼ ዘርዓ ያዕቆብ የኦርቶዶክስ
ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሲቃውንትን ሰብስቦ የመናፍቁ
አስጢፋ ተከታዮች ስግደት አይገባም ያሉበትን ምክንያት
በጉባኤ አስጠይቆ ማስረጃ ባለማቅረባቸው ከክህደት
ትምህርታቸው እንዲመለሱ በንጉሡ ቢመክሩ እንደ አርዮስ
አንመለስም ስላሉ በሲቃውንት ጉባኤ ተወግዘዉ የሞት
ቅጣት ተፈርዶባቸዋል። እነዚህ ደቂቀ አስጢፋ ይባላሉ።

39 እምደቂቀሕዝብኪ አነ እንዘ ነዳይ ወአባሲ
በብዕለዚአኪ ድንግል እት-ሜካህ ከመነጋሢ
ከወገናችሽ ልጅ እኔ በደለኛ ስሆን ድንግል በአንቺ ክብር እንደ
ንጉሥ እመካለሁ።

ወበጽድቅኪ እትፈሣሕ ከመ ጻድቅ ብእሲ
እንደ ጻድቅ ሰውም በጽድቅሽ ደስ ይለኛል።
እስመበየ ተአምርኪ ጌጋየ ኃጥአን ደምሳሲ።
ወመዝገቡበዕል ጽጌኪ ለኵሉ ዘይሴሲ
የኃጥአንን በደል የሚያጠፋ ታምርሽ ሁሉን የሚመግብ
የሀብት ልጅሽም አላችና።

Scanned by CamScanner

፵፡-40 ዜነወኒ ተአምርኪ ሶበ ይነፍሑ ነፋሳት
ከመጼናንነት ይዜኑ (ዘይዜኑ) እምርሑቅ ፍናት
መዓዛ አፈዋት ማርያም ወጽጌ መንግሥት ቡርክት።
የሽቶዎች መዓዛና የተባረከሽ የመንግሥት አበባ ማርያ
ነፋሳት በነፈሱ ጊዜ ከሩቅ መንገድ እንደሚሸት እንደ
መዓዛ ታምርሽ ሸተተኝ ደስ አለኝኝ ሄኖ 7÷7-14 ታሪ
በተራ ቊጥር ፹፫ ይመልከቱ
ጽጌ፡ ጽጌ፡ ዘሰሎሞን ወዳዊት
ጽጌ፡- ጽጌ፡- ድንግል ሆይ የዳዊት የሰሎሞን ነሽ።
ጽጌ፡ ጽጌ፡ ጽጌ አሮን ዘክህነት
ጽጌ፡- ጽጌ፡- ጽጌ፡- ድንግል የአሮን የክህነት ክብር ነሽ

<u>ሐተታ</u>፡- አበባ የደስታ ምልክት ነው ከቤተመንግሥ
አይጠፋም እመቤታችንም ከቤተ ክህነት ከቤተ መንግሥ
ተወልዳ ለዓለም ደስታና መድኃኒት ሆና መንግሥ
ሰማያትን ታወርሳለችና ::
ስለንጽት ቅጠል መዓዛ በተራ ቊጥር ፹፫
እዝይጸውረኪ በሐቂፍ ከሚለው ይመልከቱ::
፵፩-41ተአምረትፍሥሕት ማርያም ጽጌ ተድላ ወፍግዓ
መዓዛ ስብሐትኪ ምድረ ወሰማያተ መልዐ



የፍጹም ደስታ ምልክት እንባ ማርያም የደስታ ታምርሽ
ምስጋናሽ መዓዛ ሰማይንና ምድርን መላ።
በማኅሌተጽጌኪ (ፍቅርኪ) እማዕ አቅንትኒ ፅንዐ
በማኅሌተ ጽጌሽ አሸንፍ ዘንድ ጽናትን ብርታትን ስጪኝ
በመንፈልይኪ ይነሥእ ዘሞዐ
መጽሐፈ ብርሃናዊ ወመና ጎቡስ
በምስጋናሽ አሸናፊ የሆነ ብርሃናዊ መጽሐፍንና የተሠሩ
መናን ያገኛል ራእ 3÷ 4-6።
በምስጋናሽ ያሸንፋል ማለት ያለከንቱ ውዳሴ ያገለግል ሰማያ
ምሥጢር አይከፈልበትም ብሩህ ተስፋን ያገኛል ማለት ነ
42 እንበለትግረር ምድረገነት ወሥነ ጽጌያት ያስተርኢ
ምድር ሳትመሠረትና የአበባዎች መልክ ሳይታይ
በጎሊና ሥሉስ ዘሠሉ ተአምርኪ በቋዒ
ጠቃሚ የሆነ ታምርሽ በሥላሴ ሐሳብ የነበረ ነው
እ፡መዋዒት እመአምላክ መዋዒ
የአሸናፊ አምላክ እናት ሆይ
ንዒንዒ እምርእሰ ሳኔር ወኤርሞን ንዒ ሳኔርን እ
ከመ ትንሥቲዮ ለፀላዒ ሕዝበኪ ገፋዒ

Scanned by CamScanner

ወንኖችሽን የሚገፋ ብላት ሠይጣንን ታጠፈው ዘነ
ከኤርሞን ፣ነዪ ከኤርሞን፤ መኃ 4፣8። ማለት ሄርሞንስ ማ
ከንበል ስደት ነዪ ተመለሽ፣ነዪ ተመለሽ።
ብላት የተባለ ሄሮድስ ወንኖችሽ የተባሉ ሄሮድስ ያስገደላቸ
ሕፃናት፡-ላኔር የኤርሞን ስም ስለሆነ አንድ ወገን ኤርሞ
የተራራና የዕንጨት ስም በመሆኑ ተራራ ለተራራ እየ
በስደቷ ጊዜ መከራ ማየቷን፡- ስደትም እንደተራራ አስ
ነውና፡ ከተራራ ነዪ አለ። ሌላ ምሥጢርም አለው ለማ
ያዕቆብ ወደ ሶርያ ተሰዶ በነበረበት ጊዜ የአጎቱ የላባን ቦ
ሊጠብቅ በሠራው ጥበብ ልብን ገውዝ በሚባሉ ዕንጨቶ
አማካኝነት በጎቹ ሽመልመሌን(ዝጉርጉር) መልክ እንዲወ
ከሚያደርግባቸው ብትሮች አንዱ ኤርሞን የሚባል የዕንጨ
ዘር ነው እመቤታችንም የያዕቆብ ብትር ምሳሌ መሆ
የሚያስረዳ ነው ዘፍ 30፣37።

ማቴ-43 ጸግይየ ሣዕር ዘኪሩቤል ልሳነ
ተአምረኪ በነጊር አመኢፈጸምኩ (ኢፈጸምኩ) አነ
ሳር የሆንኩ እኔ የኪሩቤል እንደበትን ገንዘብ እደ
ታምርሽን በመንገር በማስተማር ባልፈጽምም (አልፈጸምኩ
ባሕቱ አለኩት ማርያም ዘጸረተኪ ማሕፀነ



ነገር ግን ማርያም የተሸከመችሽን ማሕፀን አመሰግናለሁ።
ሰውን ደኅንነት መናገር ነው።
ነዝዘ ሀለወት ጸኒሳ ኪያኪ ርጢነ
መድኃኒት አንችን ጸንሳ ሳለች
ነኢን ዘሠሥዋ ላቲ ትፈውስ ዱያነ
ኢኢን የዳሰሷት ድውያንን ሁሉ ትፈውስ ነበር ወይም
ድውያን በዳሰሷት ጊዜ ሁሉ ትፈውስ ነበርና የተሸከመችሽን
ማሕፀን አመሰግናለሁ።

## አመቤታችን በእናቷ ማሕፀን ስሳደረገችው ታምር

ይህ ታሪክ ከቀጥር ፵፰ ጋራ ተመሳሳይ ነው
ታሪክ፡- ሐምሌ ሠላሳ ቀን ኢያቄምና ሐና ሕልምን አዩ
ክልሙም ልጅ እንደሚያገኙ ነበር።
እግዚአብሔር መልአክ ደግ ልጅን ትወልዳላችሁ ብሏቸው
እግዚአብሔር ፈቃድ በነሐሴ ሰባት ቀን አመቤታችን
ተፀነሰች። በተፀነሰችም ጊዜ ብዙ ታምራት ተደርገዋል በርሱባ
ምትባል አክስት ነበረቻት አንድ ዐይና ናት ሐና
እግዚአብሔር በረድኤት ጎበኘሽ መሰለኝ? ጡትሽ ጠቁሯል
ንፈርሽ ክስሏል ብላ ማሕፀኗን ዳሳ ዓይኑዋን ብታሸው
ድናዳታል ይህን አብነት አድርገው ሕመማን ሁሉ

ማሕፀኑዋን እየዳሰሱ የሚፈጠሱ ሆነዋል ዳግመኛም ሳምን
የሚባል ያኅቲ ልጅ ሞቶ ነበር ትወደው ነበርና ያልጋው
ሽንዙር /እግር/ ይዛ እየሀረች ስታለቅስ ጥላዋ ቢያርፍበት
ተነሥቶ ሰላም ለኪ ኦ እምሐውቱ ለዘንበረ ሰማየ ወምድረ
ሰማያንና ምድርን ለፈጠረ አያቱ የሆንሽ ሐና ሆይ ሰላም
ለአንቺ ይሁን ብሎ አመሰግኗታልና።

ንዑ 44 ሚ።ኩርንኩት ወቅድስት ይእቲ
ሰዓተ ትፍሥሕት ሐና ዘጸገየተኪ ባቲ
ሐና እንቺን የወለደችባት የደስታ ቀን ምን ያህል የተባረከች
የተቀደሰች ናት፣
ወፈረየኪ ለሕይወት ኢያቄም መሞቲ
ሚች ኢያቄምም ለሕይወት አንችን ያፈራባት ቀን ምን ያህል
የተባረከች የተቀደሰች ናት፣
አሴብሕ ተአምረኪ ርግብየ አሐቲ።
አንዲቱ ርግቤ ማርያም ታምርሽን አመሰግናለሁ።

## ሐተታ

ከአመላኪያችን በቀር ወላዲተአምላክ የምትባል እንደ እርሷ
የምትራራ እናት የለችምና አንዲቱ ርግቤ
መድኃኒተ ኵሉ ዓለም እስመ ኮንኪ አንቲ



አንቺ የዓለም ሁሉ መድኃኒት ሆነሻልና ታምርሽን
አመሰግናለሁ።
45 ጽንሰትኪ መርዐአረጊት ወለአረጋዊ ከብክቡ
እንተ ተሐደሰ ብኪ ለእግዚአብሔር ውርዙተሕዝቡ።
መጸነስሽ ለባልቴቷ እና ለሽማግሌውም ሰርግ የሆነ
የእግዚአብሔር የሕዝቡ ሕይወት የታደሰብሽ እመቤቴ ሆይ
አመሰ ለኪ ማርያም ማኅሌተጽጌ ያንብቡ
ዘይቤ ኪያኪ ፍሬ ጸጋ አውያን ሐንበቡ
መፅንኦታት መዓዛ ወሀቡ
ማርያም ወይኖች የጸጋ ፍሬን አፈሩ ትርንጎዎችም መዓዛን
ሰጡ ሲል የተናገረው ሳሎሞን በማኅሌተ ጽጌ
እንዲያመሰግኑሽ አመለከተ መኃ 7 ÷14።
46 ሰንጉሠ ነገሥት ሰሎሞን ከመ ተፈሥሐ ልቡ
በዕለተ ወጸአኪ መርዓት ለእዝላትንቢት እምግቡ
ትንቢት ከተነገረለት ከእንበሳ ጉድንድ ድንግል ሙሽራ
በተነገሸ ጊዜ የንጉሦች ንጉሥ የሰሎሞን ልቡ እንደተደሰተ
መኃ 4 ÷8
ማእከለ ማኅበር ፍሥሓን ተአምረኪ እዝዘ እነቡ (ዘይነቡ)
ደስ ባላቸው በመላእክት አንድነት ፊት ታምርሽን እየተናገርኩ

Scanned by CamScanner

እዜምር ለኪ ጽጌሐና ወፍናተ ነፈርዐፅ አሌቡ
ከመጣዕዋ ሐሊበ ዘይጠቡ

የሐና አበባ ማርያም አዘምርልሻለሁ ውተትን ጣጥቱ እንደሚዘል እንቡላም ዝለል ዝለል ይለኛል፤ መዝለል ወደላይ ወደላይ ማለት ያምረኛል።

## ሐተታ

ከትንቢት አንበሳ ጉድጓድ ወጣሽ ማለት በአንበሳ ከተመሰለ ከይሁዳ ቤት እንድትወለድ ንጉሡ ሰሎሞን አስቀድሞ በትንቢት መናገሩን ሊገልፅ ነው መኃ 4 ÷8-9።

## ስለ ሰሎሞን የምሳሌዎቹና የመኃልዮቹ ብዛት

ሰሎሞን 04311 ዓመተ ዓለም ተወለደ[110]
ሰሎሞን ማለት መስተሳልም ማለት ሲሆን ትርጒሙም የሚያፋቅር የሚያስታርቅና የሚያስማማ ማለት ነው
ዘመኑ የሰላም ዘመን በመሆኑ አባቱ ዳዊት ከእግዚአብሔር እግዚአብሔር ከዳዊት በተራራቁበት ጊዜ ስለተወለደ ዳዊት ንስሐ ገብቶ ሰሎሞንን ወለደ ሰሎሞን በነገሠ ጊዜ አርባ ዘመን ሆኗል እስራኤልም ሥጋዊ ጠላት ጠፍቶላቸው ከበ

[110] ንጉሥ ሰሎሞን 04311 ዓመተ ዓለም ተወለደ



ከወይናቸው ሥር ዳስ ሠርተው ሲበሉ ሲጠጡ በሰላም ኖረዋል።
ሰሎሞን ሶስት ሺህ ምሳሌዎችን አንድ ሺህ አምስት መኃልዮችን /ምስጋናዎችን/ የተናገረ ብልህ መሪ ሲሆን ቤተመቅደስንም የሠራ ንጉሥ ነው።
1ኛ ነገ 4÷25-33 ሲራክ 47÷12።
ስለ እመቤታችንም አስቀድሞ ልጅ ወንድሜ ወደ ገነቱ ወረደ መኃ 6÷11። እቴ ሙሽራዬ ከሊባኖስ ነዪ ብሎ እመቤታችን ገና በእናቷ ማሕጸን እያለች ወደ ሊባኖስ ተሰዳ እንደምትወለድ ትንቢት መናገሩን እሱም መደሰቱን የሚያስረዳ ነው መኃ 4÷8።
ከመጀመሪያው መንግሥት ምሥረታ ከሰባ ዓመት በኋላ በ12 ዓመቱ በ4323 ዓመተ ዓለም ነገሠ። የንግሡ ዘመን 40 ዓመት ሲሆን መላ ዘመኑ 52 ዓመት ነው
47ተፈሥሐት ምድር ወሰማይ አንፈርዐፀ
በዕለተጽገዩኪ አብላስ ወአውጽኡ ሠርፀ
በለሶች /ኢያቄም ሐና/ ቡቃያ አንችን በአስገኙሽ ጊዜ ምድር ደስ አላት ሰማይም ደስ አለው።
ተአምረ ሕይወት ማርያም ዘአልብኪ ቢጸ
ጓደኛ (ምሳሌ) የሌለሽ የድኅነት ምልክት ማርያም፦

(ሐተታ) ከእሷ በቀር በድንግልና የወለደች እናት የለችም
ኀደኖ የሌለሽ አለ።
እስከፈርሐ መልአከሞት ወሰይጣን ደንገጸ
መልአከ ሞት እስከ ፈራና ሰይጣንም እስከ ደነገጠ ድረስ
ዜና ልደትኪ ነጐድጓድ እስከ (ውስተ) ሲኦል ደምፀ።
የመወለድሽ ዜና እስከ ሲኦል ድረስ (በሲኦል) ተሰማ።

## ሐተታ

ምድር ደቂቃ አዳም፣ሰማይ መላእክት፣ሲሆኑ እመቤታችን
ስትወለድ ለመላእክትና ለአዳም ልጆች ደስታ በመ
መላእክትም ለሰው ልጅ ምሕረትን የሚለምኑ ስለሆነ እን
አለ።

ዜና ልደትኪ ጽጌ ዘሰማዕኩ በኤፍራታ
ናሁ ረከብኩ በአእዋመ ገዳም መንታ
እነሆ በኤፍራታ የሰማሁት የልደትሽ ዜና አበባን በመንታ
ሸፍ (በኢያቄምና በሐና) ላይ አገኘሁት መዝ 131፥ 6-7።
ማርያም አብእኒ ለእምኪ ውሳጤ ቤታ
ማርያም ወደ እናትሽ ቤት አስገቢኝ
ትሕጽነኒ ለደክቱምኪ (ለድክታምኪ) በሠሊበ ክልዔ አጥባታ
ችግረኛሽ እኔን በሁለት ጡቶቿ ውተት ታላድገኝ ዘንድ።



ጋበርኄአፈው ተአምርኪ ዘሐሉ ውስቴታ
ከአርሷ ዘንድም ባለው ርኄ በሚባል ሽቱ ታምራትሽ ታላድገኝ
ዘንድ።

## እመቤታችን በአናቷ ማሕፀን ስለመሰደዷ

እመቤታችን ተጸንሳ ከስድስት ወር በኋላ የኢያቄም እና የሐና
ዘመዶች መጽነሷን ተረድተዉ አደነቁ ማሕፀኗን የጻፉት
ሕመ-ማንም ሁሉ ተፈወሱ የእስራኤል ልጆች ይህን ስምተዉ
በፅንሷ እንዲህ ያደረገች ብለው በምቀኝነት በድንጋይ ወግረን
እንግደላቸው በማለት ተማክሩ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልም
ከዚህ ተነሱ ብሏቸው ሊባናስ ወደሚባል ተራራ መራቸው።
በዚያም ከአዳም ጀምሮ እስከ እመቤታችን ልደት ድረስ
ትንቢት ከተነገረለት በስልሳ ስድስተኛው የትውልድ ሐረግ
በአራተኛው ክፍለ ዘመን እመቤታችን ተወለደች። ከሊባናስ
መሸራ ትወጣለች ያሰኘው ይህ ነው። መኃ. 4÷8
እመቤታችን በተወለደች በሰባተኛው ቀን የሐና ዘመዶቿ እና
ጎረቤቶቿ ማርያም ብለው ስም አወጡ። ይህ ታሪክ ከተራ
ቁጥር ፶፫ ጋር ተመሳሳይ ነው።
49 ትመስል እምኪ ማርያም ዕለተ ሣልስተ ወራብዕተ
ዘወለደት ጽጌ ወፀሐየ ዓለም ብርህተ።

ማርያም እናትሽ አበባን ያስገኝች ሶስተኛዪቱ ቀን ማክሰኞ
የምታበራ የዓለም ፀሐይንም ያስገኝች አራተኛዪቱ ቀን ዕ
ትመስላለች።

ካዕበ /ወካዕበ/ ትመስል ሳብዕተ ዕለተ

ዳግመኛም ሰባተኛዪቱ ቀን ቀዳሚትን ትመስላለች

እስመፈረየት ኪያኪ ተአምረ ግእዛን ሰንበተ

ለእለ በሰማይ ወምድር ዘኮንኪ ዕረፍተ

በሰማይና በምድር ላሉ ፍጥረታት ዕረፍት የሆንሽ የነፃነት
ምልክት አንቺን አፍርታለችና አስገኝታለችና

## ሐተታና ምሥጢር

ምሥጢሩ ሥነ ፍጥረትን ይመለከታል ጽጌረዳ ማክ
ፀሐይ ረቡ መፈጠራቸውን ሊገልጽ በጽጌና በፀሐይ የተመ
ክርስቶስ ከእመቤታችን ተወልዶ የሐና የልጅ ልጅ በመ
ለሐና የምሥጢር ክብር መስጠቱን ያስረዳል። በሰማይ ያ
መላእክት በምድር ያሉ የአዳም ልጆች ሰንበ
ማክበራቸውን መናገር ሲሆን ከሲኦልና ከጎሃነም
መውጣትና ዕረፍተመንግሥተሰማያት የሚገኝ በእመቤታች
ነውና እንዲህ አለ።



50 አይኑ ዘተገብረ ፈውስ

እምቅድመ/እንበለ/ትትወለዲ ድንግል እመቤተክህነት ወንግሥ
ድንግል ከቤተ ክህነት ከሌዊ ከቤተ መንግሥት ከይሁዳ
ከመወለድሽ በፊት ምን የተደረገ ድኅነት አለ?

መድኃኒተዓለም /መድኃኔዓለም/ ኮነ ደመጽጌኪ ክርስቶስ።

የልጅሽ የክርስቶስ ደም የዓለም መድኃኒት (ዓለምን
የሚያድን) ሆኗልና።

አስግድ ለተአምርኪ በአብራከ ሥጋ ወነፍስ

በከመሰገደ ሰወልድኪ /ለኪ/ ዮሐንስ በክርሥ

ዮሐንስ በማሕፀን ሳለ ለልጅሽ /ላንቺ/ እንደሰገደ ለታምርሽ

በሥጋና በነፍስ ጉልበት አስግዳለሁ ሉቃ 1፥41።

ምሥጢሩ፡-ክርስቶስ በዕለተ ዓርብ ተሰቅሎ ደሙን አፍስሶ
ዓለሙን ማዳኑን የሚያስረዳ ነው።

የሥጋ ስግደት ጉልበት የተመቸ፣ የነፍስ ስግደት ጾም
ጸሎትና ንስሓ።

## ክፍል አንድ ተፈጸመ

Scanned by CamScanner

## ክፍል ሁለት

ሃሬ፡ 51ከመሰዶም እምነነ ወከመገሞራ እመሰልነ
እግዚአብሔር ኪያኪ እመኢያትረፈ ለነ።
በትረተአምር ማርያም እንተ ጸገይኪ መድኅነ
ዘይቤ ኢመጻእኩ እጸውአ ጻድቃነ
አላ ለንስሓ ኃጥአነ
ጻድቃንን እጠራ ዘንድ አልመጣሁም ኃጥአንን ወደ ንስ
ልመልስ እንጂ ብሎ የተናገረ ማቴ 9፥13።
መድኅን ክርስቶስን የወለድሽልን የታምር ብትር ማርያ
ሆይ እግዚአብሔር አንችን ባያስቀርልን ኖሮ እንደ ሰዶ
በሆን እንደ ገሞራም በመሰልን ነበር። ሰዶምና ገሞራ በ3
ዓመተዓለም በእሳት ተቃጠሉ[1] ዘፍ 13፥10 ኢሳ 1
ሮሜ 9፥22-30።

## ሐተታ

የታምር ብትር ማርያም አንች ነሽ አለ የአርዮን ብት
ያለምንም ውሃ አብባ አፍርታ መገኘቷን የሚያስረዳ ነው።

ሃጂ፡ 52 እመ ተሰቅለ ቍልቍሊተ ወተተክለ በርእሱ።
ወደታች ተዘቅዝቆ ቢሰቀል በራሱም ቢተከል

[1] ሰዶምና ገሞራ በ3152 ዓመተ ዓለም በእሳት ተቃጠሉ



እንበለረድኤትኪ አልቦ ዘይክል አድኅኖ (አድኅኖተ) ነፍሱ
ያለአንቺ እ ዳታ ነፍሱን ማዳን የሚችል የለም
አኮ ድንግል በፈጽሞታላት ስሱ
ድንግል ድስት ታላትን በመፈጸምም አይደለም ማለት ብራብ
አበላችሁኝ ብጠማ አጠጣችሁኝ እንግዳ ብሆን ተቀበላችሁኝ
ብታረዝ አለበሳችሁኝ ብታመም ጠየቃችሁኝ ብታሰር
ጎበኛችሁኝ የሚለውን ትዛዝ መፈጸም ብቻ አይደለም ማቴ
25÷35-37 ክብሯ ከቅዱሳን ክብር ይበልጣል ሲል ነው።
ለተአምርኪ ከመይትነከር ሞገሱ
በገነተጽጌ ሚዳኒ ምስሌኪ አንሶሱ
የታምርሽ ክብር ይገለጽ ዘንድ (እንዲገለጥ)
ልጅሽ ባዘጋጃት ገነት ከአንቺ ጋራ እኖር ዘንድ አድኑኝ
፥-53 ከመታቦት ሥርጉት በወርቀዓረብ ወተርሴስ
በዓረብ እና በተርሴስ ወርቅ እንዳጌጠች ታቦት
በድንግልና ማርያም ሥርጉተሥጋ ወነፍስ
በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ ያጌጥሽ ማርያም።
ተአምረነቢር አርአይኪ በቤተመቅደስ
ኢያቄም ወሐና ቀንሞስ ቀናንሞስ
እምዘጸገዩኪ ለጳጦስ በዓመት ሠላስ

Scanned by CamScanner

ኢያቄምና ሐና ቀንሞስ ቀናንሞስ የሚባሉ ሽቱምች ለ
ምኳሉ የነሥንሽ አንችን በሦስት ዓመት ከአስገኙሽ ዘንድ
በዚተ መቅደስ የመኖር ታምርን አሳየሽ

## ሐተታ

እመቤታችን በተወለደች በሳስት ዓመቷ ኢያቄምና
ለቤተክርስቲያን ስለት መስጠታቸውን መናገር ሲሆን የዓ
ወርችም ጽሩይ ነው።

ንጹሕ በሆነ ምሳሌ ሁሉ እመቤታችንን ይመስላታል ሳ
ልምላሜ እንዳይለየው ኢያቄምና ሐናም ልምላሜ በረ
አልተለያቸውምና እንዲህ አለ።

፪፡-፭ ዎፍኒ ረከበት ላቲ ቤተ ለኑባሬ

አቤቱሕኪ እንዘአብል በመዝሙረዳዊት ወውሉደ
ዘውሉደ ቆራ በዳዊትና በቆራ ልጆች ምስጋና (የቆራ ል
በሚያመሰግኑት በዳዊት ምስጋና) ወፍ እንኳ መኖሪያ ቤ
ለራሷ አገኘች እያልኩ አመሰግንሻለሁ መዝ 83፥3።

ተአምርኪ ማርያም ዘትጸገ ሕገዘማሬ
ትመስል ዕፀ ዘባተ ኀበ ሙሐዘ ማይ ሠራሬ
በበጊዜሃ እንተትሠብ ፍሬ



ማርያም ሕግ ምስጋናን የምታስገኝ ታምርሽ በየጊዜዋ ፍሬን
የምትሰጥ በውሃ ዳር የበቀለች ዛፍን ትመስላለች
ዘፍ 49 ፥22 መዝ 1 ፥3-4።

## ሐተታ

በየጊዜዋ ፍሬዋን የምትሰጥ ዛፍ የተባለች በሀገራቸው ለውዝ
ገውዝ በሀገራችን ሎሚ ትርንጎ ናት እመቤታችንም በዚች
ትመሰላለችና፤ ወፍ ለራሷ ቤትን አገኘች ማለቱ በመጀመሪያ
እመቤታችን በስደቷ ጊዜ ማደሪያ ማጣቷን ሲያመለክት በኋላ
ዮሴፍን ሰሎሜን የምታኖርበት የነትአሞግን ቤት አገኘች
ማለት ነው። በዳዊትና በቆሬ ልጆች ምስጋና ያሰኘው ደግሞ
ለዳዊት ከ288 በላይ መዘምራን ነበሩት የነዚህ አለቆች ቆሬ
ኤማን አሣፍ ኤዶታም ይባላሉ ከአራት ተካፍለው ይጸልዩ
ያመሰግኑ ነበርና።

ከመዘምራን አለቆችም አንዱ ቆሬ ስለነበር ቆራን አነሳ
1ኛ ዜና መዋ 15፥16-19

፭፡-፭ የኀዘነኒ ማርያም ዘረከበኪ ድክትምና።

አመቤተመቅደስ ቦኪ እንዘትጠብዊ ሐሊበሐና
ማርያም የሐናን ወተት እየጠባሽ ወደ ቤተ መቅደስ በገባሽ
ጊዜ ያገኘሽ ድህነት /ብቸኛነት/ ያሳዘነኛል
ወያስተፈሥሐኒ ካዕበ ትእምርተ ልሕቶትኪ በትድስና

Scanned by CamScanner

ምክለአብያጲሁ ከመአብ እዝይሴስየኪ መና
ፋኑኤል ጽጌነድ ዘይከይድ ደመና
ዳግመኛም በደመና የሚመላለስ ደመናን የሚረግጥ የኪ
አበባ ፋኑኤል ከጓደኞቹ መላእክት ጋር መናን እየመ
በንጽሕና የማደግሽ ታምር ደስ ያሰኘኛል።

## ሐተታ

የእሳት አበባ ፋኑኤል ማለቱ የእሳት መልክና የጽጌረዳ መ
አንድ ሲሆን የመልአክ ፋኑኤል ተፈጥሮም ከእሳት ነ
እንዲህ አለ ታሪኩ እመቤታችን በሶስት ዓመቷ ቤተ መቅ
ንብረት መኖሯንና ከወላጆቿ መለየቷን የሚገልጽ ነ
ፋኑኤል ብቻ መናን ቢመግባትም መላእክት አይለይዋ
ነበርና ፋኑኤል ከጓደኞቹ ጋር አለ።

ሂሬ፡- 56 ኢጸመውኪ ወኢፈተልኪ አራዛተ ሠርጉ ለለቢስ።
የጌጥ ልብስን ለመልበስ አልደከምሽም አልፈተልሽምም
እስመ ሥርጋዌ ንጽሕ ብኪ እንተአነሞ መንፈስ
ሠንፈስ ቅዱስ የሠራው የንጽሕና ሽልማት አለሽና።
ማርያም ጽጌ ተአምረ ዘመን ሐዲስ
እምስንኪሰ ከመ ሥነጽጌ ንዑስ
በመዋዕለክብሩ ኢለብሰ ሰሎሞን ንጉሥ



የእዲስ ዘመን ምልክት አበባ ማርያም ሆይ ንጉሥ ሰሎሞን
በመንግሥቱ ዘመን ከመልክሽ ትንሽ የአበባ መልክን
የሚመስል እንኳ አልለበሰም 1ኛ ነገ 10÷1 ማቴ 6፡26-30።
ሂ፡- 57 እምነተመጽሐፍ አቀስም ተአምረኪ ለነቢብ
ለገቢረመዓር ጽጌ በከመ ይቀስም ንህብ
ንብ ማርን ለመሥራት አበባን እንዲቀስም ከተክል ቦታ
መጽሐፍ ታምርሽን ለመናገር አቀስማለሁ
በአሳዕንኪ ማየ ዘአስተይኪዮ ለክልብ
የተጠማ ውሻን በጫማሽ ውሃን ያጠጣሽው
ታስትዩኒ እምሮማንኪ ጊዜ ሰዓተዕምዕ ዕፁብ
በሚያስጨንቅ ውሃ ጥም ጊዜ ከሮማንሽ ታጠጭኝ ዘንድ
ተራጎርጎ ማርያም የዋሂት ርግብ
የዋሂት ርግብ ማርያም ራራልኝ እዘኝልኝ

## ስለተጠማ ውሻ የእመቤታችን ቸርነት ታሪክ

እመቤታችን በዮሴፍ ቤት ሳለች ውሃ ለመቅዳት ወደ ወንዝ
ወረደች የተጠማ ውሻን አይታ በጫማዋ ባጠጣቸው ጊዜ
አበረዋት የነበሩ ብዙ ሴቶች እምላክ ይወሰዳል የሚባል

Scanned by CamScanner

ከእንቺ ያሬያን እናሉ ሊዘክቱላት ከብዙሃችም አንዲት ሲ
ማድ ጋሽን እንስራሽን አንደልሽ አለቾት እመቤታችንን
ውሃስ ከጉድጓድ ኮሚውጣ አደደለም ከላይ ከአግዚአብሔ
እንቺ ስትል ደህን ቃል ምክንያት አድርጎ አካላዊ ቃ
በማሕፀኗ አደረ ስለዚህ የእመቤታችንን ቸርነት ምሕረ
መግለጽ ነው።

ሃጌ፡ 58 ከመጽሔረዳ በምድር ምስለመዓዛ ወቅያሔ
ወከመፀሐይ በሰማይ ምስለሞቅ ወሠራዔ
ከመቅላትና ከመዓዛ ጋር በምድር እንደሚታይ
ከሙቀትና ከብርሃን ጋራ በሰማይ እንደለለ ፀሐይ ሆነሽ
እርአይኪ ማርያም ወእርከብኪ ውስተኩለሄ
እመቤቱ በሁሉ አገኝሽ አይሽ ዘንድ፡-
ይቅጽባኒ አዕይንትኪ አለምሉዓት ርኅራኄ
ፈልፈለረባሕ ተአምርኪ ኅበይትቀዳሕ ርሄ
የክብር ምንጭ ታምርሽ ወደሚቀዳበት ሥፍራ ርኅራኄ
የተመሉ ዓይኖችሽ ይጥቀሱኝ ማለት ያመልክቱኝ።

ሃፀ፡ 59 ኅበ ይቀውም ፀሐይ ለሕልቀተ ወርቅ በማዕከላ
በእርአ ያድንግል ነአስ ማርያም ርግበ ገሊላ
እንዘተሐትፍ /እንዘተሐቅፊ/ ሕፃነ ዘይጸድል እምነአብላ

ፀሐይ ቀጥ በማያበራበት በቀትር ጊዜ በወርቅ ተሰለት
መካከል ከፈኬረታ ይልቅ የሚያበራ ሕፃንን ታቅፋ/ታቅፈሽ
በምትታይ ታናሽ ድንግል ሕፃን አምሳል የገሊላ ርግብ
ማርያም ሆይ
መንገለ ሰማይ አዕይንቲሃ አልዓላ
ተአምረኪ ነጸረት ሳቤላ
ሳቤላ ወደ ሰማይ ዓይኖቿን አቅንታ ታምርሽን አየች።
ሐተታ የገሊላ ርግብ ማርያም ማለቱ ገሊላ ማለት ገለልተኛ
አየመንደር ዙሪያ ማለት ሲሆን ሐገሊላ ሕፃናት ምክንያት ከገሊላ
ተነሥታበረሃ ለበረሃ በስደት መንገላቷቷን ያመለክታል።

## ቁሰበት በሰማይ ስለመታየቱ ታሪክና ምሥጢሩ

በሮሜ አገር የነገሠ ብልህ ንጉሥ ነበር ሰዎችም አሱን
ከመውደዳቸው የተነሳ ልንሰግድልህ እንወዳለን አሉት አሱም
ፈራሽ በስባሽ ሰው ነኝና ይህ ለኔ አይገባም ብሎ
መለሰላቸውና በልቡናውም አዝኖ የሚሠራውን አጣ ከዚህ
በኋላ በዚያው በሮሜ የምትኖር ሳቤላ የምትባል ብልህ ሴት
ነበረች ሄዶ ሰዎች ልንሰግድልህ ይገባል ያሉትን ሁሉ ነገራት
ሳቤላም እስከ ሶስት ቀን ድረስ ታገሠኝና የሚደረገውን ሁሉ
ኣኔ እነግርሃለሁ አለችው ስለሚያደርገው ነገር ሁሉ
ኣግዚአብሔርን በጸሎት ለምና

Scanned by CamScanner

በነጋተኛው ቀን በኒድነት ሰዓት ፀሐይ በሰማይ መካከል
ራእይን አየች። ራእዩም የወርቅ ቀሰበት በንጉሡ እጅ
በወርቅ ቀሰበቱም ላይ እንደ ፀሐይ የምታበራ ድንግል
ሴት ተሥላለት። በክንድዋም ሬቱ ኩብርሃናት ሁሉ የሚ
ሕፃንን አየች።

ንጉሡን ና ወደሰማይ ተመልከት አለችው ንጉሡና
ወደ ሰማይ በተመለከተ ጊዜ ሳቤላ እንዳየችው ሬ
ተገነዘለት ሕፃኗ ምንድን ናት? ሕፃኑስ ምንድን ነው? ብ
ወየቃት ክቢያት ሳቤላም ሕፃኗ እመቤታችን ናት ሕ
የሰማይ ንጉሥ ጌታችን ነው አለችው።

ለዚህ ሰማያዊ ንጉሥ ሰማደት ይገባል ብላ ተረጉመችለት ንጉ
በዚህ ራእይ ተደንቆ መሠዊያ አሠርቶ መሥዋዕትን ሠዋ
ሆናንም አቀረበ ንጉሡም ከሰደት ዳነ ስለዚህ ታምርሽን
አሰኝ አለ።

ጽ፡ ና፡ እግዚአብሔር ንሮ ኑሩ ዓለመ
እግዚአብሔር ዓለምን ሁሉ አየ ተመለከተ
ወአረጋገጠ ማርያም ዘኮነች እመ
ማርያም እንዳንች ያለች እናትንም አላየንም።
ለለሥራ ከያሁለ ሽጌ ዘአምነዘሥላ ተቀበመ
አሉስ ኮሚአሸንሽ የተገኘ አዘነ ነው።



ዳዊትኒ አመረከ እንዘይብል ቅድመ
ስምዒ ወለትየ ወርአዩ ዳግመ
ዳዊትም ልጀ ሆይ ስሚ ዳግመኛም እዩ
እስመ ፈተወ ንጉሥ ሥነኪ አዳመ
ያማረ ደም ሞባትሽን ንጉሥ ወዲልና ሲል አመለከተሽ ማለ
ከሥጋሽ ሥጋን ከነፍስሽ ነፍስን ነሥቶ ከእንቺ ተዋሕዲልና ዘሰ
አስቀድሞ ትንቢትን ተናገረልሽ።

ኪያሁስን ከዚህ ተርጉም ከማሕፀንሽ የተገኘ አሱን እንድትወልጂ
ዳዊት አስቀድሞ አመለከተሽ ትንቢትን ተናገረልሽ
መዝ 44፡10-11።

## የንጉሥ ዳዊት የትውልድና የነገሠበት ዘመን

ዳዊት ከአባቱ ዕሴይ ከእናቱ ሀብሲ በ4253 ዓመተዓለም ተወለደ[12] ዳዊት ማለት የተወደደ የተመረጠ ልበ አምላክ ማለት ሲሆን ትውልዱ ከነገደ ይሁዳ ነው ንጉሥ ዳዊት በ4283 ዓመተ ዓለም በኢየሩሳሌም በሰላሳ ዓመቱ ነገሠ ክቢያ ነውና ከእሱ እመቤታችን እንደምትወለድና ክርስቶስ ከእመቤታችን እንዲወለድ በትንቢት አስቀድሞ መናገሩን የሚያስረዳ ነው መላ ዘመኑም 70 ዓመት ነው።

[12] ዳዊት በ4253 ዓመተዓለም ተወለደ

Scanned by CamScanner

ሳዱ፡ ፩ ስብሐተፍጥረኪ ማርያም ኵሉ አሚረ
በልብነስኵላ ያጸንኒ ወአያፈርሕ አባረ
ማርያም የፍጥረሽ ምስጋና ሁል ጊዜ በሁሉ አንደበት ያ
ያንንፈል ድርቅንም አያፈራም
ዘያረጥብ የብስ ወያየብስ ባሕረ
የብሱን ርጥብ የሚያደርግ ባሕሩንም የሚያደርቅ ነው
እስመ ብኪ ጠለተአምር እንተ ርደቦ ነጸረ
ጌዴዎን ጎበ ስፍሐ አምላስኪ ፀምረ
ጌዴዎን የእንቺ ምሳሌ የሆነውን ፀምር /ነጭ ባ
በዘረጋበት ሥርዓት መውረዱን ያየው የታምራት
አለሽና /በአንች አለና/

## ሐተታ

ድርቅ እህሉን ተክሉን ቅጠሉን ቆርጦ ያስቀራል
የእመቤታችንን ምስጋና ግን ድርቅ ውዳሴ ከንቱ
አይቀላቀለውም፤ ባሕርም አይገድበውም አይወስነውምና።
የጌዴዎንን ታሪክ በመጽሐፈ መሳፍንት በምዕ 6፣37 ቁ
ያመልክቱ።

፪፡ ፫ ፈትለጠርቅ ወፈትለሜላት አመ በአጽባዕትኪ ተባየጹ
አምላለመለኩት ወትስብእት እንዘ ኢየሐፀ



ተአምረ ብርሃን ማርያም ሰፀሐየ ጽድት አንተጹ
የእውነት ፀሐይ መውጫ የብርሃን ምልክት ማርያ
የትስብእትና የመለኮትን ተዋሕዶ ሳያጓድሉ የሐርና የወር
ፈትሎች በጣቶችሽ በሚፈተሉበት ጊዜ
ጸገይኪዮ እንበለአብ በሰሚዓቃሉ ወድምፁ
ለገብርኤል መልአክኪ ዘፍሥሕ ገጹ
ፊቱን ደስ ያለው የተላከልሽ የገብርኤል ድምፁን በመስማት
ያለአባት ጸነስሽው

ታሪኩ፡- እመቤታችን በቤተ መቅደስ ሐርና ወርቅን
እያስማማች ስትፈትል ቅዱስ ገብርኤል ትጸንሻለሽ ብሎ
ያበሠራትን አዲስ ብሥራት የሚተርክ ነው።

## ሐተታ

የቃልና የድምፅ ልዩነት፤ ቃል የነገሩን ፍሬነት ሲያመለክት
ድምፅ ከቃል የሚወጣውና በጆሮ የሚሰማው ነው።

፮፫፡ 63 ዐቢይ ውእቱ ተአምር ጸገዮትኪ በድንጋሌ
ወፈርዮትኪ በንጽሕ ቍርባነ አምልኮ መጥለሌ
በድንግልና መጽነስሽ በንጽሕናም የሚያለመልም የአምልኮ
ቍርባንን መውለድሽ ታላቅ ድንቅ ታምር ነው።



Scanned by CamScanner

ማዕጠንተ ሱራፌ ዘወርቅ ወፅዋዓ ኪሩብ ዕንቁ ቢረሌ
አልቦ ጸሎት ወአልቦ ትንባሌ
እንበሌኪ ማርያም ዘየዐርግ ሉዓሌ
የሱራፌል የወርቅ ማዕጠንት ቢረሌ የሚባል የኪሩቤል
የዕንቁ ፅዋ ማርያም ያለአንች ወደላይ ወደ ፈጣሪ የሚያርግ
ልመናም ምልጃም የለም።

ቁጥር 64 አ፡ዝ መንክር በዘዚአኪ አምሳል
ኮከበ ትንቢት ዘቦቱ መልክአሕዛን ሥዑል
ሠረቀ ያርኢ ተአምረኪ ድንግል
ድንግል ምን አይነት ድንቅ ነገር ነው! በአንቺ አምሳል የተሳለ
የሕዛን መልክ ያለበት ኮከብ ታምራትሽን ይገልጥ ዘንድ ታየ።

ወመርሆሙ ለሰብአሰገል አምርሐት ደወል
ጽጌኪ ኀበሀሎ ሰኪቦ /ይስክብ/ በጎል
ልጅሽም ተኝቶ ወዳለበት በረት ሰብአሰገልን ከሩቅ አገር
መራቸው ማቴ 2፥9-12

## የሰብአሰገል ቁጥርና የ1534 ዓመት የኮከብ ታሪክ

አመቤታችን ከመወለዷ ከ1520 ዓመት በፊት በለዓም የሚባል
ፈላስፋ /ተመራማሪ/ ነበር ከዕለታት አንድ ቀን ከአዳም እስከ



ሙሴ ዘመን ያሉትን ሰዎች የትውልድ ቁጥርንና ትንቢትን
የያዘ መጽሐፍ አቅርቦ መረመረ አመቤታችንን አየ ባያትም
ጊዜ አርስዋ ድንግል ስትሆን ልጅዋ ክርስቶስን ታቅፋ ነበር
በዐጠገቧም ታላቅና ብሩህ የሆነ ኮከብ ነበረ
በዚያን ጊዜ ከሱ በታች ያሉትን ፈላስፎችና ደቀመዝሙሩ
የሆነ ዘረደሽትንም ሰበሰባቸው ከዚያም በተዳመጹ ብራና ላይ
የተሣለውን የጌታችንና የአመቤታችንን ሥዕል እንዲሁም
በዐጠገቧ ያለውን የኮከብ ሥዕል አሳያቸው ፈላስፋውም በሱ
ዘንድ ለተሰበሰቡት ይህ ኮከብ በእናንተ ዘመን ወይም
በልጆቻችሁ ዘመን ምልክትን ቢያሳይና ቢገለጥ የዚያን ጊዜ
ድንግል ከነልጅዋ ወዳለችበት ቤት መርቶ ያደርሳችሁ ዘንድ
አሱን ተከተሉት እጅ መንሻንም አቅርቡለት አላቸው
ይህንንም ምልክት ከነገራቸው በኋላ ፈላስፋው በለዓምና
ተከታዮቹ ሁሉ ሞቱ። ነገር ግን በሕይወት ያሉት ወይም
ከነሱ በኋላ የተነሱት ሰዎች ያቺን ሥዕል በቤተ መዛግብት
/ዕቃ ቤት/ አኖሯት። ያችን ሥዕል ለሚነበሷት ሁሉ በኋላ
ዘመን የሚደረገውን አባቶቻቸው የተናገሩትን ትንቢት
ይነግሯቸው ነበር። ከ1534 ዓመት በኋላም ጌታችን ኢየሱስ
ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሊወለድ ሁለት ዓመት
ሲቀረው ያ ኮከብ በሀገራቸው ላይ በግልጽ ታየ በዚያን ጊዜ

Scanned by CamScanner

ያንን ሥዕል ከቤተ መዛግብት (ዕቃ ቤት) አወጡና በሥዕሉ ላይ ከተገለጸላቸው ኮከብ ጋራ አንድ መልክ /ትክክል/ መሆኑን አረጋገጡ። በዚያን ጊዜ አባታቸው ዘረደሽት እንደ ነገራቸውና እንዳነረዳቸው የሀገሩ ፈላስፎችና መኳንንቶችም ሁሉ ከሠራዊቶቻቸው ጋር እጅ መንሻውን ይዘው ሥዕሉን ተሸክመው ለመሄድ ተነሡ።

ኮከቡም ርቀቱ ከሰው ቁመት ሰባ አምስት ሜትር በሆነ ከፍታ ላይ ሆኖ በፊት በፊታቸው እየሄደ መንገዱን ይመራቸው ነበር። በመሸም ጊዜ በመልካም ማደሪያ ቦታ ያደርሳቸውና ከነሱ ይሠወር ነበር እነሱም በሰላም ያድራሉ። በዚህ ዓይነት ጉዞ እየተጓዙ ጌታ ከተወለደበት ቦታ በሁለት ዓመት ደረሱ ሕፃኑን ድንግል እናቱ በክንዷ እንዳቀፈችው አይተው ተደሰቱና እጅ ነሱት ሰገዱለትም የሰብአሰገል ብዛታቸው ሰላሳ ሺህ ሦስት ሲሆን ሶስቱ ለእያንዳንዳቸው አሥር አሥር ሺህ ሠራዊትን ይመሩ ነበር የአንድ ሺህ አምስት መቶ ሀላሳ አራት ዓመት የትንቢት ኮከብ ታሪክ በዚህ ተፈጸመ።



65 እንዘተሐቅፌዮ ለሕፃንኪ ጽጌ ፀዳዳ ውዮይሕ
እመ ቤተመቅደስ ቦእኪ በዕለተተአምር ወንጽሕ
ንዒ ርግብየ ትናዝዝኒ እምላህ
ነጭና ቀይ መልክ ያለው አበባ ልጅሽን ታቅፈሽ በአርባ ቀን ወደቤተመቅደስ በገባሽ ጊዜ /እንደገባሽ/ ርግቤ ኮዝዘን ታረጋጊኝ ዘንድ ነዪ።

**ወንዲ ሠናይትየ ምስለ ገብርኤል ፍሥሕ**
**ወሚካኤል ኅማኪ ርኅሩኅ**
**የእኔ አዛኝ ደስ ካለው ከገብርኤል እንደ አንቺ ርኅሩኅ ከሚሆን ከሚካኤል ጋር ነዪ።**

ነጭ በመለኮቱ ቀይ በሰውነቱ ነው መኃ 5÷10

ምሥጢሩ፡- እመቤታችን ጌታን በወለደች በአርባ ቀን ከርግብ ወገን ዋናስ ጋራ ቤተመቅደስ መግባቷን ይመለከታል። የኦሪቱን ሥርዓት ለመፈጸም በግዕዘኢሳናት /በእሳናት ልማድ/ እንጅ ልማደ አንስት ኖሮባት አይደለም። ቅዱስ ገብርኤልም በዕለተ አሑድ በያለንበት እንዕና ብሎ መላእክትን በማረጋጋቱና ማርያምን ሂድ አብሥራት ሲለው ደስ እያለው አብሥሯታልና ገብርኤል ፍሥሕ አለ።

ቸዳብ ሚካኤልም አስራኤልን አርባ ዘመን ሙሉ በፈጣሪ
ትዛዝ መና መመገቡን እንደአንች ርኅሩኅ አለ። በባቢሎ
ምርኮ ጊዜም አቤቱ ሕዝብህን ማራቸው ይቅርም በሳቸ
እያለ ከሰባው የምርኮ ዘመን ውስጥ በአምስት በአምስ
ዓመት አሥራ አራት ጊዜ ለአስራኤል ምሕረት
ይለምንላቸው ነበርና።

አስተምህሮ ለነ ለአልናከ ሚካኤል በአሠርቱ መአርባዕ
ትንበልናከ

በአሥራ አራቱ ልመናዎችህ ማልድልን ያሰኘውም ይህ አንጻ
ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በዓመት አስራሁለት ጊዜ በወር
በወር በዓሉ ሲከበር፣ በአሥራሦስት ከአእላፍ መላእክት
በታኅሣሥ አሥራ ዘጠኝ ከቅዱስ ገብርኤል በዓል ጋራ በዓሉ
በመከበሩ፣ ለሰውም ሁሉ ታዛኝና ምሕረትን የሚለምን
ነውና እንዲህ አለ ሄኖ 6፡ 5-6 ::

ሄ፡ 66 ሶበያዒንኪ አርዌ በሊኃሕሣንኪ ዘንለየ
በዘትሠርረ ገዳመ ወታፈጥኒ ጕዩየ
ልጅሽን ለመብላት(ለመግደል) ያሰበ አውሬ ሄሮድስ በተከተለሽ
ጊዜ ወደበረሀ እንድትበሪ ፈጥነሽም እንድትሸሺ
ማቴ2÷13-18::
እንተ(አመ)ጸገይኪ አክናፈ ከመዮሐኒ /ዮሐንስ/ ጸገየ



ለዮሐኒ እንደተሰጠ ክንፍ ተሰጠሽ ወይም ዮሐኒ ክንፍን
እንዳወጣ ክንፍን ባወጣሽ ጊዜ
ብእሊተሰማይ ማርያም ዘትሰብሲ ፀሐየ
ተአምረኪ ጸሐፈ ዮሐንስ ዘርእየ።
ፀሐይን የምትለብሺ የሰማይ እመቤት ማርያም አንችን ያየ
ዮሐንስ ታምርሽን ጻፈ።

## አባ ዮሐኒ በሕይወት ገነት ስለመግባቱ ታሪክ

አባ ዮሐኒ ከመወለዱ በፊት የእናቱ ባል የተገዜን ሹም
ነበር። ለዘመቻም ለንግድም ይላሉ ናባ ወደሚባል አገር ሄዶ
ለሰባት ወር ያህል ዘገየ።
ከሰባት ወር በኋላም ሚስቱን የሱ ትንሽ ወንድም የሆነ
ወንድሜ ዘገየ ከእንግዲህ ወዲህ አይመለስም ሞቷልም
ይላሉ።
ስለዚህ ሚስት ትሆኚኝ ዘንድ ነጺ ቃልኪዳን እንግባ አላት።
እሷም የባሏ ትንሽ ወንድምና በቤቷ ውስጥ ያሳደገችው
ነበረና እንዴት ደፈርክኝ ብላ ተቆጣች። እሱም ወንድ ነውና
አሸንፎ ደረሰባት ጸንሳ ወንድ ልጅን ወለደች።
በወለደችበት ቀን ከብዙ ምርኮ ጋር ባሏ ወደ አገሩ ተመለሰ
ወደቤቱም በገባ ጊዜ ሚስቱ ከቤት የለችም ነበርና ሚስቱ
ወዴት ሄደች ብሎ ጠየቀ።

Scanned by CamScanner

በቤት ውስጥ ያለ አንድ ሕፃን ባለቤትህ ታማለች አለው። ባለቤቷም በሽታዋ ምንድነው አለው ያም ሕፃን ዛሬ ልጅ ወለደች ብሎ መለሰለት

ከሕፃኑ አንደበት ይህንን ነገር በሰማ ጊዜ ፈጽሞ ተቆጣ ያ ሕፃን እየመራው ሚስቱ ወዳለችበት ገባ ይደበድባትም ጀመር ደብረ ዓሣይ በሚባል ገዳም ስሙ አባ አሞኒ የተባለ ገዳማዊ ነበር በዚያ ገዳምም ለሃያ ዓመታት ያህል የቆየ ነው።

የእግዚአብሔር መልአክም አባ አሞኒን ተነስተህ የተንቤን ሹም ወደ ሆነው ሰው ቤት ሂድ ከዚያም እግዚአብሔር የወደደውን ነገር ታገኛለህ አለው አባ አሞኒም የእግዚአብሔር መልአክ እንዳዘዘው ከተራራው (ከገዳሙ) ወርዶ ወደ ተንቤን ሹም ቤት ደረሰ ሚስቱም በቤታ በር ፊት ለፊት አባ አሞኒን ባየችው ጊዜ ውስጡ ጥበበ እግዚአብሔር ነውና ከዚህ መነኩሴ ጸንስኩ አለችው።

ያን ጊዜ ባሏ በቁጣ ወጥቶ አባ አሞኒን መታው ልጅህን ያዝህ ሂድ ብሎ ሕፃኑን ለአባ አሞኒ ሰጠው።

አባ አሞኒም ሕፃኑ በተወለደበት ቀን በልብሱ አቀፈው ስለዚህም ዮሐኒ ተባለ።



ወደ ገዳሙ ወስዶ እኔ ጡት የለኝ! ብሎ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ ከገደሉ ጀርባ በመቃብር አምላያ (እንደ መቃብር አጠመሰሉ) ምድርን ቆፈረና ለሕፃኑ የሰሌን ቅጠልን አንጥፍ በዚያ አስቀመጠው ድንጋይንም ከደነው እግዚአብሔር ከወደደ ያድንህ ይቺ ጉድጓድ እናትህ ትሁን ብሎ ከዚያ ትቶት ወደ ገዳሙ ሄደ።

በነጋውም ማልዶ ወደዚያ ሕፃን ገሠገሠ ፈቆዋ(ሚዳቷዋ) ከጉድጓዱ ድንጋዩን አስወግዳ ተንበርክካ ስታጠባው አያት ፈቆዋም አባ አሞኒን ባየችው ጊዜ ከጉድጓዱ ውስጥ ሸሸች አባ አሞኒም ያን ሕፃን ጸስተኛ ሆኖ ዓይናቹን ባየ ጊዜ ያህን ዕፁብ ድንቅ ሥራ ያሳየኸኝ እግዚአብሔር ስምህ ይመስገን አለና ወደ ገዳሙ ተመለሰ አባ አሞኒም ጠዋትና ማታ እየጎበኘው ሕፃኑ እንዲህ ሆኖ ፈቆ እንደ እናቱ እያጠባችው ሦስት ዓመት ኖረ። እንዳይበርደውም ዝንጀሮ ያቅፈው ነበር። ሕፃኑም ከሦስት ዓመት በኋላ የፈቆዋን ጡት መጥባት ተወ አባ አሞኒም ወደ ገዳሙ ወስዶ እስከ ሰባት ዓመት ድረስ በዚያ አሳደገው ከሰባት ዓመቱ ጀምሮ የዳዊትን መዝሙር፣ የነቢያትንና የሐዋርያትን መጻሕፍት እስከ ትርጓሜያቸው

አስተማረው ሕፃኑም አስራ ሁለት ዓመት በሆነው ጊዜ አባ አሞኒ ይህ ልጄ ትምህርትን ጨረሰ ዲያቆን ይሆን ዘንድ ወደ ጳጳስ ልውሰደው ብሎ አሰበ።

የስድስት ሰዓት መንገድንም ያህል ሄደ አባ ዮሐኒ ውሃን በእንስራ ተሸክመው የራሳቸው ጸጉር ረጅም ጡቶቻቸውም ታላላቅ ሆነው ከልብስ ተራቁተው አሥር ሴቶችን አየ።

አባ ዮሐኒ ከዚህ አስቀድሞ የሴት መልክን አይቶ አያውቅም ነበረና አባ አሞኒን እነዚህ የረከሱ ሠይጣናት ናቸውን አለው። አባ አሞኒም ልጁ ዮሐኒ ሴትንና ወንድን ይለይ ዘንድ ልጁ ዮሐኒን ልጄ አምን ሰውን የሚያስቱ ናቸው። ሁለተኛ እንደነዚህ ያለ ባየህ ጊዜ ተወርውረህ ወደ ገደል ግባ አለው። ከዚህ በኋላ ወደገዳሙ መለሰው በገዳሙ ውስጥም አባ አበይዶ የሚባል መነኩሴ ነበር የተጋድሎ ዜናቸውን ሰምቶ ረድዕ (አገልጋይ) ለመሆን አብሯቸው ተጨመረ አባ አሞኒና ልጁ አባ ዮሐኒ መጽሐፍን እየጻፉ ለምግባቸውና ለልብሳቸው አባ አበይዶ እየሸጠ እንዳህ ሆነው በብሕትውና ሲኖሩ አባ አሞኒ አርባ ዓመት በገዳም ኖሮ አባ ዮሐኒ በተወለደ በሃያ ዓመቱ አባ አሞኒ አረፈ በገዳማቸውም ቀበሩት።



ከዚህ በኋላ አባ ዮሐኒ 12 ዓመት ኖሮ ጎደሬ አምነት [illegible] ኩዕ ሦስት ሰዓት እንደ ልማዱ ከተራራ ላይ ወጣ ወላጅ እናቱ መኖታ እንደምን አደራችሁ አለች አባ አንቱ ማነህ? አለ እናቱ በክርስትና ስሟ እኔ መንፈስቅዱስ ነኝ አለች።

አባቱ አሞኒ የነገረውን አስታውሶ እንዝቱን አትንካ አያት በዚያን ጊዜ መጽሐፉንና የቁለም መጻፊያ ብዕሩ ወደ ገደሉ ተወረወረ (ወደቀ)።

አባ አበይዶ እያየው በክንዶቹ ግራና ቀኝ ክንፍን አውጥቶ ቅዱስ ገብርኤል ከአርሱ ጋር ሆኖ መንፈስ ቅዱስ እየመራው ሄኖክና ኤልያስ ወዳሉበት ብሔረ ሕያዋን ገባ።

ወደገደል መወርወሩ እንደ ሞት እና እንደመቃብር ክንፍ አውጥቶ ብሔረ ሕያዋን መግባቱ እንደ [illegible] ሙታን ተቆጥሮለት ሁለተኛ ሞት የለበትም። በተወለደ በሃያ ዓመቱ ሞትንና መቃብርን ሳያይ ብሔረ ሕያዋን ገባ ይህ ሁሉ ዕፁብ ድንቅ የተጋድሎ ታምር የሚገኝም አመቤታችንን በወለደችው ጽጌ ክርስቶስ ነው።

## ስለ አመቤታችን የክንፍ ምሥጢር፡-

የሐንክ ወልደ ነጕድጓድ ምሥጢር ያልተከፈለበት

የክርስቶስ ባለሟል ነው በመስቀል ላይም እመቤታችን እና
እንደሆነች እሷም ልጅዋ እንደሆነ ክርስቶስ አደራን ሰጥቷል
ዘዕለታት አንድ ቀን ፀሐይን የለበሰች ሕፃን አየ ይች ሕፃ
ፀሐይ መልበሷን ሲተረጉም እንዲህ አለ፡- ሕፃኗ እመቤታች
ናት ፀሐዩ ልጅዋ ክርስቶስ ነው በፍጥረት ሁሉ አንደበ
ስሟ ከሚጠራበት የልጅዋም ምስጋና ከሚነገርበት ቦታ ሁ
በረድኤት ፈጥና የምትደርስባቸው ረቂቃን ክንፎች አሏ
አለ። በለበሰችው የፀሐይ ብርሃን ሙቀትም በኃጢአት ቁር
ውስጥ ላሉት መቀትን /ንስሓን/ ሰጣቸው ብሎ ዮሐኝ
ያየውን ራእይ ስለጻፈ ክንፍን ያወጣሽ ፀሐይን የለበስሽ አለ።

ጀ፡67 ተአምረ ማርያምኪ ለአርእዮ እምገጸሄሮድስ መስቴማ
አመጕየይኪ ማርያም በሐዊረፍናት አለደክማ
ማርያም የግፍሽን ታምር ለመግለጽ ከጠላት ሄሮድስ ፊት
በሸሸሽ ጊዜ
ምስለአግረ ጽጌኪ ልምሉም ኀበ አኢጋርኪ ቆማ
ለምጽረገጻምኪ ቅድስት ቍስቋም ስማ
እምፈተውኩ በጺሐየ በሰጊድ እስዓማ
ካለመለመ ከልጅሽ እግር ጋር መንገድን በመሄድ የደከመ
ለግሮችሽ የቆመባት የተቀደሰች ገዳምሽ (ቦታሽ) ስሟ
ቍስቋም ነው።



እኔም ደርሼ ብላለማት እመኛለሁ ወያም ብላለማት
በወደድኩ ነበር።

ኖ፡68 አፈ አሮን ማርያም ጽጌያናንም ወአበሚ
ቍናንም አበሜ ከሚባሉ ሽቱዎች(በነቢያት ትንቢት) የተዘጋጀሽ
የአሮን የክህነቱ ክብር ማርያም
እስከ ተጸምሐየየ በጸም ዘመልክዕኪ ልምላሚ
የመልክሽ ልምላሜ በጸም እስከ ጠወለገ ድረስ
ተአምረብካይ ወስደት ዘበጽሐኪ (ዘበጽሐኪ)ጊዜ ድክመ
እምተመነይኩ ተሳትፎ ከመእሥትኪ ስለሚ
በድህነትና በጭንቀት ጊዜ የደረሰብሽ (የደረሰብሽ) የስደትና
የልቅሶ ታምርን እንደ እህትሽ እንደ ሰሎሜ በተሰጠኸኝ ነበር
ወፍሥሓኪ (ወፍሥሓየ) ዘአልቦ ፍጻሜ
ደስታሽም (ደስታዬም) ፍጻሜ የሌለው ነበር።

ኗ፡69 የበስኩ አንሰ ( እንክ) ተክለ ቤትኪ በነፋስ ሐሩር ዘንጣውስ
ከመ ጽጌ መንግሥት የበስኪ በዋዕየ ረሀብ ወዕምዕ
የመንግሥት አበባ አንቺ በራብና በዕም ሐሩር እንደተቃጠልኝ
እኔ የቤትሽ ተክል እንግዲህ በኃጢአት ሐሩር ነፋስ ደረቅሁ
ማርያም ንዝኅኒ በዘዚአክ አንብዕ
ወአጽግዩኒ ጽድቀ በተአምርክ ቀውዕ
እንተቡቱ ይጸገ ወይፈሪ ቀዕ

Scanned by CamScanner

ለፍጥረቱ ሁሉ ርኅርኅት ነሽና።

## የበረከት ቅባትን ስለተቀቡ እንስሶች ታሪክ

በዓመት በዓመት ደብረ ቍስቋምን ሊያከብሩ የሚሄዱ ምእመናን በፊረስ በበቅሉ ተጭነው ሲሄዱ እንስሶች ሲደክሙባቸው በአለንጋ ይገርፏቸው ነበር እንዳይደክሙ ኃይልን እንዲያገኙ እመቤታችን የበረከት ሽቱን ትቀባቸው ነበርና መራራትሽ ለሰው ብቻ አይደለም ለእንስሶችም ጥምር እንጅ አለ።

ቍ፡- 71 አመአተውኪ ውስተታቦት ምስለ ቆጽለዘይት ሐመልማል

ከለመለመ የ[illegible] ቅጠሉ [illegible] ሞርክብ በገባሽ

/በተመለከተ። [illegible]

ከመ አ[illegible]

ለኖኅ የታየኸው [illegible] ምሳሌ ነሽና/ዘርዝሩ

አብሥርኒ ጽድቁ ዘአዊረጽኄ ጽዱል

ነአኩሕ አበባን በመያዝ ጽድቅን አብሥሪኝ

ማርያም ርግበ ቍስቋም ዘአክናፍኪ መስቀል

ከንፎትሽ መስቀል የሆኑ የቍስቋም ርግብ ማርያም

ሃሌ ሉያ ፋሲካየ ማዕዶት እምነጥል

ከጦፋት የደስታ መሸጋገሪያዬ ነሽ።

ሃሌ ሉያ ምስጋና ይገባሻል።



ማርያም እንዘሸን እርጪኝ

ቡቀያ አብዮ በሚያፈራበት በመጸው ዘመን በታምርሽ ጽድቅ

እንዳብብ እንዳፈራ አድርጊኝ።

## ሐተታ

በእኩሳ ከዘረሌ በለሚሳላድንትሽ ልንጸ ነፋስ የበላው /የመታው

እህል ፍሬ እንደሌለው ንጣውአም ሰውን ከፍሬ እ

ይሊየሱና። ጽጌመንግሥት የሚለውም ንባብ ምሥጢሩ

ኩኖዊት ከሰሎሞን መገኘቷን የሚያስረዳ ነው

ቍ፡- 70 ነጋድያንቍስቋም ለእንስሳ አለተፅዕንሙ በፍናት

የቍስቋም ነጋዴዎች በመንገድ የተጫነባቸው እንስሶች

/ፈረስ በቅሎ/

ዘኢያስተትኪ እግሮሙ ከመትቅብዒ /ከመትቅብዒሙ/

ቅብዓ በረከት

የበረከት ቅባትን አግራቸውን ትቀቢ ዘንድ ያልናቅሽ እመቤቴ

ቅብዓጽጌኪ ቅብዕኒ ተአምረምሕረት መርዓት

የምሕረት /የቸርነት/ ምልክት ማርያም ሆይ

የልጅሽ ሽቱን ቀቢኝ

እኩ ለሰብኢ ባሕቲቱ ማርያም ሠናይት

ግርያም ደኃንትሽ ለሰው ብቻ አይደለም

እለሙ ርኅርኅተ ልብ አንቲ ለኵሉ ፍጥረት

Scanned by CamScanner

**ማርያም እንባሽን እርጪኝ**

ቡቃያ አብቦ በሚያፈራበት በመጸው ዘመን በታምርሽ ጽድቅ እንጸብብ እንዳፈራ አድርጊኝ።

## ሐተታ

በንስሓ ከበደሌ በአማላጅነትሽ ልንጻ ነፋስ የበላው /የመታው እህል ፍሬ እንደሌለው ኃጣውኣም ሰውን ከፍሬ ጸ ይለያሉና። ጽጌመንግሥት የሚለውም ንባብ ምሥጢሩ ከዳዊት ከሰሎሞን መገኘቷን የሚያስረዳ ነው

ቍ፦70 ነጋድያንቀሳቋም ለእንስሳ አለተፅዕንዎሙ በፍኖት

የቀሳቋም ነጋዴዎች በመንገድ የተጫኑባቸው እንስሶች /ፈረስ በቅሎ/

ዘኢያስተትኪ እግሮሙ ከመትቅብዒ /ከመትቅብዒዮሙ/

ቅብዓ በረከት

የበረከት ቅባትን እግራቸውን ትቀቢ ዘንድ ያልናቅሽ እመቤቴ

ቅብዓጽጌኪ ቅብዕኒ ተአምረምሕረት መርዓት

የምሕረት /የቸርነት/ ምልክት ማርያም ሆይ

የልጅሽ ሽቱን ቀቢኝ

እኮ ለሰብእ ባሕቲቱ ማርያም ሠናይት

ማርያም ደግነትሽ ለሰው ብቻ አይደለም

እስመ ርኅርኅተ ልብ አንቲ ለኵሉ ፍጥረት



ለፍጥረቱ ሁሉ ርኅርኅት ነሽና።

## የበረከት ቅባትን ስለተቀቡ እንስሶች ታሪክ

በዓመት በዓመት ደብረ ቍስቋምን ሊያከብሩ የሚሄዱ ምእመናን በፈረስ ለበቅሉ ተጭነው ሊሄዱ እንስሶች ሊደክሙባቸው በአለንጋ ይገርፏቸው ነበር እንዳይደክሙ ኃይልን እንዲያገኙ እመቤታችን የበረከት ሽቱን ትቀባቸው ነበርና መራራትሽ ለሰው ብቻ አይደለም ለእንስሶችም ቸርነሽ እንጅ አለ።

ቍ፩፦71 አመአተውኪ ውስተታቦት ምስለ ቆጽለዘይት ሐመልሚል

ከለመለመ የ[illegible] ቅጠል [illegible] ርክብ በገባሽ

/በተመለሰሽ/ ጊዜ

ከመ አ[illegible]

ለኖኅ የያቀርባ ጊዜው ምሳሌነት አንደነገርሽው

አብሥርኒ ጽድቀ ዘአዊረጽጌ ጽዱል

ንጹሕ አበባን በመያዝ ጽድቅን አብሥሪኝ

ማርያም ርግበ ቍስቋም ዘአክናፍኪ መስቀል

ከንፎችሽ መስቀል የሆኑ የቍስቋም ርግብ ማርያም

ሃሌ ሉያ ፋሲካየ ማዕዶት እምነጕል

ከጥፋት የደስታ መሸጋገሪያዬ ነሽ።

ሃሌ ሉያ ምስጋና ይገባሻል።

Scanned by CamScanner

ታሪኩና ምሥጢሩ፡- ናህ በመርከብ ውስጥ እያለ ርግብን ልኮ የወይራ ቅጠልን ይዛ ወደ ናህ ስትመለስ የጥፋት ውሃ መጥደሱን ናህ ተረዳ በእመቤታችንም ምክንያት የዓለም ሁሉ ኃጢአት በንስሓ መንጻቱን የሚገልጽ ሲሆን የርግብ ክንፍ አራት መዓዝን /አቅጣጫ/ እንደመሆኑ የእመቤታችንም ንጽሕናዋ ቅድስናዋ በመላው ዓለም መነገሩን የሚያስረዳ ነው። የክንፍ የአራት አቅጣጫነት ደግሞ ግራና ቀኝ ሁለት ክንፍ እንዳለ ሆኖ ወደፊትና ወደኋላ ያለውን የአካል ክፍል እንደመስቀል ቅርፅ ቆጥሮ ነው መርከብ ርግብ የእመቤታችን ቆጽለዘይት የዘመነ ጽጌ ምሳሌ።

ሮቮ፦72 እስመ ብዙኃን ድንግል ተአምረወልድኪ ዘኀሠሡ
ድንግል ሆይ የልጅሽን ታምር የፈለጉ ብዙዎች ናቸው እኮ!
ኢፈጸሙ ኵሉ እንዘ ይዌድሱ
ነገር ግን ሁሉን አመስግነው አልጨረሱም እመ ብዙኃን ቢል ድንግል ሆይ የልጅሽን ታምር የፈለጉ ብዙዎች ቢሆኑም አመስግነው አልጨረሱም
ትቤ በሜሮን ዘተኀትመት ቤተመቅደሱ
በሜሮን የተቀደሰች (ሜሮንን የተቀባች) የልጅሽ ቤተ መቅደሱ ለሰች ምን አለች?
ኅቡተከለ ወአጽገየ አብትረ ዮሴፍ ዘየብሱ



(ኅቡተከለ ወአገዩ አብትረ ዮሴፍ ዘየብሱ)
ወልድ እጕየ ወራዶ በጊዜ ናእሱ
ልጅ ወንድሜ በታናሽነቱ የደረቱና የጡቱና የዮሴፍ ብትሮችን ወደተከለበትና ወደ አሳበበበት (አዘዘ ወደ አስመሰለበት) /የደረቱና የተሰበሩ የዮሴፍ ብትሮች ወደ ተተከሉበትና ወደ አበበበት/ ቦታ ወርዶ
አፈዋተ (አፈወ መዓዛ) አውጎዘ እምልብሱ
መዓዛ ያለው ሽቱን ከልብሱ አፈሰሰ አመነጨ አሰተ

## ስለ ዮሴፍ ብትር መሰበርና የሜሮን አመጣጥ

እመቤታችን ዮሴፍ እና ሰሎሜ ጌታ በተወለደ በሦስተኛ ሥመቱ ወደግብጽ በተሰደዱ ጊዜ ዮሴፍ የሚመረዘዘው ብትሮን በእጁ ይዞ ነበር ጌታችን የዮሴፍን ብትር እንሥቶ ስዘረ ተአትን ማለት ስባት ስብርባሪዎችን አድርጎ በዚያ ቦታ ተከሳችው በከበሩ እጆቹም ጉድጓድን ቆፈረ መዓዛው የሚዛኩት ውሃ ፈልቆ ፈሰሰ ከዚያም ውሃውን በመሐል እጁ አነዝንን የተከላቸውን ስባት የብትር ስብርባሪዎች አዘዛቸው ወዲያውኑ በቀሉ አድገውም ታላላት ዛፎች ሆኑ ከእነርሱም ደስ የሚል መዓዛ ሽተተ እርሱም ከሽቱዎች ሁሉ እጅግ ይበልጣል በለሳንም ብሎ ጠራቸው።

Scanned by CamScanner

እናቱ ድንግል እመቤታችንንም እናቴ ሆይ የተከልኩት በሰ
እስከ ዓለም ፍጻሜ ከዚህ ይኖራል የክርስትና ጥምቀትን
በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ለሚጠመቁ ክርስ
ቅብዕ ቅዱስ ይገኛል አላት ከዚያም ጌታችን የመሠረተ
የክርስትና ጥምቀት የሚፈጸም ከበለሳን በሚገኘው ቅ
ቅዱስ ነው። በእርሱም ደግሞ አብያተክርስቲያናት ንፁ
ቅድሳትና ታቦተ ሕግ የሚከብሩበት ሕይወትም የሚገኝበ
ለክርስቲያኖች ሁሉ መመኪያቸው ነው። በለሳን ማለት የሽ
ዕንጨት ስም ሲሆን መገኛውም ገሊላና ይሁዳ ነ
ይልቁንም በኢያሪኮ ይበዛል ከዕጣን እንጨቶችም አንዱ ነው
ቁ፲፫፡-73 ስፍነ ድንግል ለጽጌኪ ተአምራቲሁ /ተአምሪሁ/እ
ወትሕትናሁ እኄሊ ሶበረፈቀ ለስምዖን በውስተ ሕፅኑ
ድንግል የልጅሽን ታምራቱን ስንት ጊዜ እናገራለሁ
አደንቃለሁ? ትሕትናውንስ አስባለሁ?
በስምዖን እቅፍ ውስጥም በተያዘ ጊዜ ነውን? ሉቃ 2÷27-29
ከመቆመኑ ቅድመ ዮሐንስ ድኑኑ
በዮሐንስ ፊት አንገቱን ዘንበል አድርጎ እንደቆመ ሳስብ
ነውን?
ወሚመ ከመበረቀ በደብረ ታቦር ብርሃኑ
ወይስ በደብረታቦር ብርሃነ መለኮቱን እንደገለጸ፡-



ወከደነ ሰማያተ ሥኑ ማቴ 3÷13-17 ፣ 17÷1-3 ።።
ጌትነቱም ለማያትን እንደመላ ሥልጣ ነውን? ስንት ጊዜ ምን
ያህል/ እናገራለሁ! ይህ ቃለ አንክሮ ነው።
**ታሪክና ምሥጢር**፡- ጌታ ከተጸነሰ ጀምሮ ብዙ ታምራትን
ይሠራ ነበር በተወለደ በአርባ ቀኑም በነዚህ ስምዖን እትፍ
መያዙ በሠላሳ ዘመኑ በዮሐንስ እጅ መጠመቁ እና ደብረ
ታቦር በተባለ ተራራ ላይ ብርሃነ መለኮቱን በመግለጹ ድንቅ
ሥራንና ትሕትናን ገንዘብ ማድረጉን የሚያስረዳ ነው።
፻፬፡-74 በላዕሌኪ ወበዮርዳኖስ ወበታቦር ሥልሰ ጊዜያተ
በእንቺ ላይ በዮርዳኖስ በደብረታቦር ሦስት ጊዜ
ዘአልቦ ተውላከ ወአልቦ ሕፀተ /ተውላክ ወኢ ሕፀት/
ለውሉደ ሰብእ ያርኢ ዘሥላሴሁ ገጸተ።።
ጭማሪ ጉድለት ላይኖርበት ለሰው ልጆች ሦስትነቱን በአነ
ይገልጽ ዘንድ
ጽጌኪ ድንግል ተአምሪሁ ከሠተ
ወበፀዳሉ አብርሀ ጽልሙተ
ድንግል ልጅሽ ብርሃኑን ገለጠ በብርሃኑም ጨለማን አራቀ።።

Scanned by CamScanner

ቍ፭፡ 75 እምትእምርተሞቱ ለጽጌኪ ዓለም ጽልመተ ድኅረተከደነ
ከልጅሽ ሞት ድንቅ ታምር የተነሣ ዓለም ጨለማን ከለበሰ
በኋላ

ገይሠኪ በአስቆቅም ኀበሥጋሁ ተደፍን
ሥጋው ወደ ተቀበረበት መቃብር በልቅሶ ገስግሰሽ
አመርኪኮ ድንግል እንዘይትአጸፍ ብርሃነ
ወልድየ ብህልኪዮ ተንሣእስኑ እሙነ
ድንግል ሆይ ብርሃንን ተጐናጽፎ ባየሽው ጊዜ ልጁ በእውነት
ተነሣህን አልሽው
ወሰዐምኪ በአፉኪ እፁሁ ቍርባነ
ቍርባን አፉንም በአፍሽ ሳምሽ

**ታሪክና ምሥጢር**፡-ጌታ በዕለተዓርብ በተሰቀለ ጊዜ የፀሐይን መጨለም የጨረቃን ደም መልበስ የከዋክብትን መውደቅ ሲያመለክት እመቤታችንም ብርሃንን ለበሶ ልጅዋን አይታ ልጁ ተነሣህን ብላ አስቀድማ ትንሣኤውን አመልክታለችና እንዲህ አለ።

ቍ፮፡ 76 እስኮንተ ነፍሳተሰብእ ኃይለተአምርኪ ዘመሠጠ
እምአፈሊኦል ወሞት አለ ለመዱ ውኂጠ



መዋጥን ከለመዱ ክሞትና ከሲኦል አፍ ስጉቶችን የሰው
ነፍሳት ወይም ምን ያህሉትን ነፍሳት የታምርሽ ኃይል
የነጠቀ (ያወጣ) ነው?
እንዘይብል አቡኪ አሜሃ መሰንቆትንሣኤ ዘበጠ
አስመሰበረኖኃተ ብርት ወመንሠግሐሢን ቀጥቀጠ
ጽጌኪ ማርያም ዜዋነ ዘሜጠ
ማርያም ምርኪትንን የመሰሰ ልጅሽ የብረቱን በር ሰብረ
የነሐሱንም በር ቀጠቀጠ ብሎ ያን ጊዜ በትንቢት አባትሽ
ዳዊት የትንሣኤ መሰንቆን መታ መዝ 106÷15 - 17።

ቍ፯፡ 77 ለጽጌኪ ማርያም ከመይጠይቅ ትእምርቶ
በድንግልና ልደቶ ወውስተ ሰማያት ዕርገቶ
እመሊእምነ ሰሚያ እሙታን ተንሥኦቶ
ኀበ መቃብሩ ለለዓሙ ለብርሃነ ሰማይ ርደቶ
ይባዕ ወይርአይ ዘይነብብ ከንቶ
ማርያም የልጅሽን ታምራቱን ሊረዳ የሚፈልግ በድንግልና
መወለዱን፣ ወደሰማይ ማረጉን፣ ከሙታን መነሣቱን ሰምቶ
ከንቱ ነገርን የሚናገር ሐሜተኛ ካላመነ በየዓመቱ ከመቃብሩ
ላይ ብርሃን መውረዱን ይግባ ይይ።

ቍ፰፡ 78 ጽጌደመና ማርያም ሥጋኪ ዘንብረ ግልባቤ
ትእምርተመዊዕ ምሕርካ ነሢእ እምድረምንዳቤ

Scanned by CamScanner

አመ ዐርገ ወልድ ውስተ ወግረስዂን (ውስተ ደብረ ስዂን ወደብረከርቤ

የደመና አበባ ማርያም ሥጋሽን የለበሰ ወልድ የድል መንሣት ምልክት የሆነ ምርኮን ማርኮ ከዚህ ዓለም መዓዛዎች ወደ አሉባቸው ኮረብታና ተራራ (ወደ ሰማያት) ባረገ ጊዜ

አርኅዉ ኖኃተ መኳንንት ለንጉሠ ስብሐት ዘይቤ

ተሰምዐ ቃለ ቀርን ወደምፀ ይባቤ

መኳንንት ሆይ ለክብር ባለቤት በሩን ክፈቱ የሚል የመለከት የዕልልታ ድምፅ ተሰማ መዝ 23፥7-10 ::

ታሪኩ ክርስቶስ ባረገ ጊዜ መላእክት ለፈጣሪያቸው ምስጋና ማቅረባቸውን መናገር ሲሆን ሱራፌል ኪሩቤል ለፈጣሪያቸው ምስጋናን ወደሚያቋርጡበትና ሰጣንን በማጠን ወደ ሚያገለግሉበት ሰማየሰማያት በክብር ማረጉን የሚገልፅ ነው

## ሐተታ

የደመና አበባ ማርያም ማለት አበባ በደመና ጊዜ ፈክቶ/ ጎልቶ/ ይታያል በደመና ከተመሰለች እመቤታችን በአበባ የተመሰለ ልጇ መወለዱን የሚያስረዳ ነው::

ቁ፡- 79 መዓዛ ጥዑም ዘኤርምያስ ጽጌክርሥኪ ጽርስፎራ

ኤርምያስ ደስ የሚያሰኝ መዓዛ ብሎ የተናገረለት ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙን ያደለን ልጅሽ



አመመሠጠኪ ድንግል በዚናተአምር ዘክሩ

ድንግል በሚያስደንቅ የታምራት ኃይል በአሳረገሽ ጊዜ

ተተበሡኪ በአብሐት ሥርግዋነ መብረቅ ሐራ

መብረቅን የለበሱ በመብረቅ ያጌጡ መላእክት በክብር በምስጋና ተተበሡሽ

ቦ ዘይዘብጥ ክበሮ ወቦ ዘይነፍሕ እዝራ

እስከ አብዑኪ ለንግሥት ዘብርሃን ደብተራ

ንግሥት አንችን ወደ ብርሃን ድንኳን እስከ አስዝዑሽ ድረስ ክሮን የሚመታ እዝራንም የሚነፉ ነበር::

ምሥጢሩ እግዚአብሔር ለነቢዩ ኤርምያስ የለውዝ ብትርን አሳይቶ ምን ታያለህ ቢለው ኤርምያስም የለውዝ ብትር ማየቱን ሲናገር መልካም አይተሃል ብሎታል ለውዝ /ሎሚ/ የእመቤታችን ምሳሌ እንደሆነች አስቀድሞ በትንቢት ገልጸለታል ኤር 1፥11-13 ፤ 24፥2-7 ተረ ኤር 11፥35-38

ቁ፡- 80 እግዚአብሔር ጽጌትንቢት ለቢሶ ሥጋኪ ሥጋዚአነ

የትንቢት አበባ እግዚአብሔር የእኛ ሥጋ የሆነ

ሥጋሽን ለብሶ

አመ አስተርአየ በምድር ውስአምረ ሰነ

በምድር /በዚህ ዓለም/ በታየና በተገለጸልን ጊዜ

ንዌድሰኪ እንዘንብል ምክሐ ዘመድነ

Scanned by CamScanner

የባሕርያችን የነገዳችን መመኪያ እመቤታችን
ዮም በፍሥሐ ለማርያም እምነ
አስተርአዮ በሰማይ ኮነ
ዛሬ ለእናታችን ለማርያም በሰማይ በደስታ የክብር መገ
ሆነ እያልን እናመሰግንሻለን

## ሐተታ

የትንቢት አበባ እግዚአብሔር ማለት ነቢዩ ኢሳይያ
በተናገረው ትንቢት ከዕሴይ ግንድ ብትር ይወጣል ከሥሩ
ቍጥቋጦ ያፈራል ብሎ ብትር እመቤታችን፣ ጽጌ፡ ክርስቶ
መሆኑን አስቀድሞ ስለተናገረ እግዚአብሔር ጽጌ ትንቢት አ
ኢሳ 11፥1-2።

ቍ፡-81 በብሔር በንበ ፈለስኩ ጎዲግየ ብሔረ
ስብሐተአርብዓኪ ድንግል ኮነኒ መዝሙረ
አገርን ትቼ በተሰደድኩበት አገር የአርባ ቀን ምስጋና
መዝሙር ሆነኝ ማለት ከመስከረም ሃያ ስድስት ቀን እስ
ጎዳር ስድስት ቀን ድረስ ያለውን።
ተአምርኪ ድንግል በከመነገረ
ጌቴ ሴማኒ መቃብርኪ አመትከውን ሐመረ
ድንግል ታምርሽ እንደተናገረ፣ መቃብርሽ ጌቴሴማኒ
መርከብን በምትሆን ጊዜ



ሥመሪ ታዕድውኒ ዘእሳት ባሕረ
የእሳት ባሕር ገሀነምን ታሻግሪኝ ዘንድ ውደጂ

## ሐተታ

የአርባ ቀን ምስጋናሽ ምስጋናን ሆነኝ ማለት በዘመነ ጽጌ
ለአርባ ቀን ያህል ደራሲው ጽጌ ብርሃን (ጽጌ ድንግል) ካለበት
ቦታ ወደ ኀደኖው ወደ አባ ገብረማርያም አገር ሄዶ ለአርባ
ቀን ያህል የማኅሌተ ጽጌ አገልግሎትን ሲያገለግል ቆይቶ ወደ
አገሩ ይመለሳል እንደዚሁም አባ ገብረማርያም ከአለበት አገር
ወደ ኀደኖው ጽጌ ብርሃን (ጽጌ ድንግል) አገር ሄዶ ለአርባ
ቀን ያህል አገልግሎ ይመለስ ነበርና እንዲህ አለ።

ቍ፡-82 አመነሥኡኪ እምኤዶም አዕላፈማኅሌት ጸታ /በበጸታ/
እንዘይጼልሉኪ ድንግል በአክናፈመባርቅት ከመወልታ
ድንግል ወገኖች መላእክት በየነገድ በየነገድ ሆነው በብርሃን
ክንፎች እንደ ጋሻ ጋርደው ከኤዶም ገነት በተቀበሉሽ ጊዜ
ሠራዊተ ሰማይ ይቤሉ ለክብረፍልሰትኪ ግርማ ትእምርታ
/ትርጒታ/
መኑ ይእቲ ዛቲ እምገዳመጽጌ (ዘገዳመ ጽጌ) ዕርገታ
ወከመ ሠርፀ ጢስ ዘስሂን ይምዕዝ ዕጥንታ
የሚያስደንቅ ክብር ለተገለጸባት ለዕርገትሽ የሰማይ ሠራዊት

Scanned by CamScanner

አበባ ካለበት በረሃ የምትወጣ መዓዛዋም ከነጭ ዕጣን ይልቅ
የሚሸት ይች ማናት? ይላሉ መኃ 3÷6።

ቁ፡- 83 እንዘይጸውረኪ በሐቂፍ ወይስዕመኪ በእፍ
አመአፍለሰኪ ወልድ (አመ ወልድኪ አፍለሰኪ) ውስተየማኑ
ለዐረፍ
ጽጌ ዕፀ ገነት (ጽጌ ተአምር) ማርያም ዘትጸንዊ ለአንፍ
ለአፍንጫ መዓዛን የምትሰጪ የገነት ዛፍ (የታምር) አበባ
ማርያም ሆይ ልጅሽ በክንዱ አትፎ በአፉ እየሳመ በቀኙ
ሊያስቀምጥሽ ባሳረገሽ ጊዜ
እንዘይትጎድኡ አክናፈ በክንፍ
ለቀበላኪ ወረዱ አእላፍ
አንቺን ለመቀበል ክንፍ ለክንፍ እየተጋጨ (እየተማቱ) አልፍ
አእላፋት መላእክት ወረዱ። አባታ ዳዊት በመዝሙሩ
ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቀመጣለች፡- በሰጠሃት ክብርም ጸንታ
ትኖራለች ብሎ የተናገረው ትንቢት ተፈጸመ መዝ 44÷9።

## ስለ ገነት ቅጠል መዓዛ ታሪክ

የገነት ዛፍ ቅጠሉ ለፋፊ ነው አሥራሁለት አሥራ አምስት
ክንድ ይሆናል ቢያንስ ቢያንስ ከስምንት ክንድ አያንሰም
ሽታው የዓመት የመንፈቅ ጎዳና ያህል ርቀት ሄዶ ይሸታል
ፍሬው የጋን መክደኛ ያህላል ቆርጠው እስኪመለሱ ድረስ



አፍርቶ ይገኛል ጥራቱ እንደመስተዋት ነው መልክንም
ያሳያል።

ቁ፡- 84 ትእምርተ ፍልሰትኪ እምድረጽጌ ኦ ድንግል በክልዔ
በደመና ሰማይ አርአየ ዘሐዋርያት ጉባኤ
በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ ድንግል የሆንሽ ማርያም ሆይ
አበባ ካለበት ምድር ወደ ሰማይ የማረግሽ ታምር በሰማይ
ደመና የሐዋርያት ጉባኤን አሳየ።
እምድረጽጌን ዘርዝር፡- ፍልሰትኪ እምድረጽጌ።
ከሚያልፈው ዓለም ወደማያልፈው ዓለም ማረግሽ በሰማይ
ደመና የሐዋርያት ጉባኤን አሳየ።
ፍልሰትኪ እምድኅረጽጌ
ከልጅሽ ዕርገት በኋላ የሆነ እርገትሽ በሰማይ ደመና
የሐዋርያት ጉባኤን አሳየ።
ወእለሞቱ እንቅሐ/አንሥአ/ እምክርሠመቃብር በቀርነፅዋዔ/
የሞቱትንም ከመቃብር ውስጥ በታምር ነጋሪት ድምፅ
አስነሣ።
ሰነሰ እስከ ይብሉ ሶበሰማዕነ ውዋዔ
መሰለነ ዘበጽሐ ትንሣኤ
ለኛስ የምስጋና ጩኸትን በሰማን ጊዜ የዳግም ምጽአት
/የሙታን መነሣት/ የደረሰ መሰለን እስኪሉ ድረስ።

Scanned by CamScanner

## ሐዋርያት በአንድነት ወደሰማይ ስለማረጋቸው

በደመና ሰማይ አርአየ ዘሐዋርያት ጉባኤ የሚለውን ለመግለጽ እመቤታችን ባረገች ባመቱ ሁለት ሱባዔ ማለት ከነሐሴ አንድ እስከ አሥራ አራት ያለው ቀን ከተፈጸመ በኋላ እመቤታችንን ስታርግ ባለማየታቸው ዓመት ሙሉ ሲያዝኑ የነበረውን በጎ የጸሎት መልስን ለመስጠት በነሐሴ አሥራ ስድስት ቀን ጌታ ሐዋርያትን ወደ ሰማይ አሳርጎ ነፍሷን ከሥጋዋ አዋሕዶ በክብር በልጅዋ ቀኝ ተቀምጣ አላይቷቸዋልና እንዲህ አለ አነሱም ወደ ደብረ ዘይት ተመልሰው መጥተዋል::

ቸ፡ቁ፡-85 ሠዊተሥርናዩ ለታዴምስ ወለበርተሎሜምስ ወይኑ

የታዴምስ የስንዴው እሸት:-

እንተጸገይኪ አስካለ በዕለተተከለኪ እደየማኑ

በቀኝ እጁ በተከለሽ ጊዜ ፍሬን ያፈራሽ የበርተሎሜምስም ወይኑ:-

ማርያም ለጴጥሮስ ጽላሎቱ ወለጳውሎስ ሰበኑ

የጴጥሮስ ጥላው የጳውሎስም ልብሱ ማርያም ሆይ

ብኪ ምዉታን ሕያዋነ ኮኑ

ሞተው የነበሩ በእንቺ ሕያዋን ሆኑ



ወሐዋርያት መላእክተ በሰማይ ኮኑ

ሐዋርያትም መላእክትን በሰማይ ዳኙ 1ኛ ቆሮ 6÷3::

## ስለ ሐዋርያው ታዴምስ የታምር ስንዴ ታሪክ

የሐዋርያው ታዴምስ /ልብድዮስ/ ሀገረ ስብከቱ ሶርያ ነው:: ቅዱስ ጴጥሮስ ታዴምስን ወደሀገረ ስብከቱ ለማድረስ አብሮ ሲሄድ በከተማ አካባቢ ሲደርሱ በአርሻ ሥራ የተሠማራ አንድ ሽማግሌ ሰውን ኦግኝተው የምንበላው ስጠን ቢሉት ከቤት ሄዶ እንዲያመጣላቸው ነግሯቸው ሲመጡ ችን ይጠብቁ ዘንድ አሳሰባቸው ታዴምስ በሬዎችን ጠምዶ ሲያርስ ቅዱስ ጴጥሮስ ዘርን ይዘራ ጀመር ገበሬው ምግባቸውን ይዞ እስኪመለስ ድረስ የተዘራው ዘር በአንድ ቀን በቅሎ አፈራ ይህን ታላቅ ታምር ያየ ገበሬም አደነቀ ስለዚህ እንዲህ አለ::

## ስለ በርተሎሜምስ ወይን ታሪክ

በርተሎሜምስ አልዋህ ወደ ሚባል አገር ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋር አብረው በሚሄዱ ጊዜ በመንገድ አንድ ነጋዴን አግኝተው ይህን አገልጋዩን (በርተሎሜምስን) ልሸጠው ነበር ብሎ ቅዱስ ጴጥሮስ ለነጋዴው አማከረው

ነጋዴውም የበርተሎሜምስ ሙያ ምን እንደሆነ ጴጥሮስን ጠየቀው ወይን ጠባቂ ነው አለው ነጋዴውም ይህን ከተረዳ

Scanned by CamScanner

በኋላ ቅዱስ ጴጥሮስ በሠላሳ አስታቴር(በሠላሳብር
በርተሎሜዎስን ሸጠው።
ነጋዴውም በርተሎሜዎስን የወይን ጠባቂዎች አለቃ አድርጎ
ሾመው ወይን እየጠበቀና እየተንከባከበ ለአርባ ቀን ያህል
ከቆየ በኋላ የወይኑ ባለቤት ሞቶ ጸልዮ አስነሥቶታል
በዚህም ብዙዎች አምነዋል የበርተሎሜዎስ ወይን ያሰኘው
ይህ ነው።

## በቅዱስ ጴጥሮስ ጥላ ሕሙማን የመዳናቸው ታሪክ

ማርያም ለጴጥሮስ ጽላሎቱ /የጴጥሮስ ጥላ/ ያሰኘው ደግሞ
ክርስቶስ ለሐዋርያት ሕሙማንን እንዲፈውሱ በሰጣቸው
ሥልጣን መሠረት ቅዱስ ጴጥሮስ በመንገድ ሲያልፍ በጥላው
ሕሙማን ይፈወሱ ነበርና ማቴ 10፣1-2 የሐዋ 5፣15-17።

## በቅዱስ ጳውሎስ ልብስ ሕሙማን የመዳናቸው ታሪክ

ወሰጳውሎስ ለበኑ የሚለውም ደግሞ ቅዱስ ጳውሎስ ጌታችን
ኢየሱስ ክርስቶስ ከዐረገ ከሰሙንት ዓመት በኋላ ያመነ
ሐዋርያ ሲሆን በልብሱ ጫፍ ብዙ ድውዮች ይፈወሱ ነበርና
ይህን ያስረዳል የሐዋ 19፣11-13።



## ወንድማማቾች ከሞት ስለመነሣታቸው ታሪክ

ብኪ ምዉታን ሕያዋነ ኮኑ ያሰኘው የሚከተለው ነው
ቅዱስ ጴጥሮስ ወደ ሮሜ ከተማ ሄዶ የሚራሩ ብዙዓን
ናቸው ለእነርሱም ይራሩላቸዓ[illegible] የሚለውን የወንጌል ቃል
ሲያስተምር የሰሙና በዚያ ያሉ የድንጋይ ምሰሶዎች እሜን
ይሉ ነበር ይህን ታምር በመጠኑ ከገለጽን ወዳዋናው ታሪክ
እንመለስና የተመረዘ ውሃ ጠጥተው የሞቱ ሁለት ልጆች
/ወንድማማቾች/ ነበሩ እናታቸው አክሮስያ አባታቸው
ቀውስጦስ ይባላሉ። እናታቸው አክሮስያ የልጆቻቸውን ሞት
ለአባታቸው ለቀውስጦስ መናገር ፈርታ ብዙ ምሳሌዎችን
ከመስለችለት በኋላ ነገረችው እጅግ አዝኖ አለቀሰ
ሚስቱም እንዲህ አለችው ጌታዬ ሆይ ልባችን የሚጽናናበትን
እርሱ ያደርግልናልና የጴጥሮስን ፈጣሪ እግዚአብሔርን
እንለምነው አለችው ጸሎትንም በጀመሩ ጊዜ ቀውስጦስና
አክሮስያ ሆይ የደቀመዝሙሬ የጴጥሮስን ቃል ስለሰማችሁና
ስለተቀበላችሁ ልጆቻችሁን በሕይወት አሰጣችኋለሁ የሚል
ቃልን ከሰማይ ሰሙ። ያን ጊዜም ልጆቻቸው ከሞት ድነው
ተነሡ እሊህም ከሞት የተነሡ ልጆች ለቅዱስ ጴጥሮስ ደቀ
መዛሙርት ሆኑ።

Scanned by CamScanner

## መላእክት በሐዋርያት ሥልጣን ስለመጻኢታቸው ታስ

በሐዋርያት መላእክተ በአማይ ኮነኑ ስለሚለው ገጸ
ስሎሐክ አፈወረት ሀሳት ወዲኛች ክሰሩት እነሱም ንጉ
አርቆሮኖክና ንግሥቲቱ አውደክሰሮ ናችው። ልጅ አየወለ
ይምትባችው ክሰር በምን ምክንያት ልጅ ይምትብናል ብሎ
ራሳችውንና መክሥቶችውን ጠየቁ ያማክሯችሁም ሲወ
ልጆችኑን ደግ ሰው በክርስትና ሊኮነሳችሁ ይህንኔ
አሊችው ክሰሀ የተነገ ክሎሐክ አፈወረት የክሰለ ደግ ሰው
አለን ብሎው ቤት ልጅን በሀሳቱ ጊዜ መሆተህ አጥምቅህ
ብሎው ላክሰት ሎሐክ አፈወረትም መልክታችውን ተቀብሉ
ሊሄድ መልእክኑን በመንገድ አገኘው ወዲት ትሄዳለህ አሉው
እሱን አንተ የምትሄድባት ሕዛንን ነፍሲን ከሥጋዋ ልለ
እሄዳለሁ አሉው አዲስ የሆነ ልደትን፣ ጥምቀትን ጽና አላን
ችምና ቶናን ላጠምቃት ብሎት ሄደ ሕዛኒን አጥምቆ በለ
መንገድ ተመላለስ የክሰናት ማክርንችው ሥልጣናችው ደግ
አንደሆነ ሊታወቅ ወደላይም ወዲቱችም ላይል አሥር ዓመት
ክዚያው ካለበት ቤታ ቆም ናረ።

ሕፃኒ አሥር ዓመት ሲሆናት ለባል ታጨቺች ያቺ ሕፃን
ሀብትን አግኝታለችና መጥተህ መርቀት ብለው ላክሰት እሺ
ብሎ በዚያ መንገድ ሲሄድ መልእክኑን ቆም አገኘው ምክሮ



ክዚህ ቆመሀል? አለው አንተ ቆይ ካልክኝ ወዲህ ወዲያና
ወዲህ ብዙ አላውትም አሰው ዮሐንስም አጥፍቻለሁ ብሎ
ሄድ የታዘዝክውን አድርግ አለው። ቢሄድ ነፍሲን ከሥጋዋ
ለይቶ ሞታ ሲያለቅሱ አገኛችው ተውት ነገሩ ከእግዚአብሔር
ክው ብሎ አስረድቶ ለጽናንቲቸዋል። በተጨማሪም በምድር
የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል በምድርም
የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል የሚል
ሥልጣንን ሰጥቷቸዋልና። ማቴ 18፣18-19 በሰላተምጽአት
ጊዜም ሐዋርያት በአስራሁለቱ ነገደአስራኤል ላይ
ስለሚፈርዱ የሐዋርያት ሥልጣን ለመላእክት አልተሰጠምና
ሐዋርያት የምድር መኪንንትን ዳኑ አለ ማቴ 19 ፥ 28።

ቁ፡ 86 ጽጌኪ ማርያም ኮነኒ ሲላየ ወለፊዘ
ማርያም ልጅሽ ምንብንና ልብስን ሆንኝ
ወጸገወኒ እምትካዝ ተለምረኪ መናገዘ
ከጭንት ከችግር የሚየረጋጋ ታምርሽንም ሰጠኝ
ቶማስ ሱቱ አመገዛሁ አንዘ
አንዘ /አስአ/ ይብል ክርቤ አምአዴየ ውሕዘ
ረክበ ውስተ (በውስተ ቁኑሱ) አፈወ ምዑዘ
ቶማስ ንኑን በዳሰለ ጊዜ ሸቱ ከእደ ፈሰለ እስኪል ድረ
ከቁኑሱ ውስጥ አስደናቂ መዓዛን አገኙ።

Scanned by CamScanner

ከዚህ ቆመህል? አለው እንተ ቆይ ካልከኝ ወዲህ ወዲያና ወዲህ ብዬ አላውቅም አለው ዮሐንስም አጥፍቻለሁ ብሎ ሂድ የታዘዝከውን አድርግ አለው። ቢሄድ ነፍሷን ከሥጋዋ ለይቶ ሞታ ሲያለቅሱ አገኛቸው ተውት ነገሩ ከእግዚአብሔር ነው ብሎ አስረድቶ አጽናንቷቸዋል። በተጨማሪም በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል የሚል ሥልጣንን ሰጥቷቸዋልና። ማቴ 18፥18-19 በዕለተምጽአት ጊዜም ሐዋርያት በአስራሁለቱ ነገደእስራኤል ላይ ስለሚፈርዱ የሐዋርያት ሥልጣን ለመላእክት አልተሰጠምና ሐዋርያት የምድር መኳንንትን ዳኑ አለ ማቴ 19 ፥ 28።

ቸ፮- 86 ጽጌኪ ማርያም ኮነኒ ሊላየ ወአራዘ
ማርያም ልጅሽ ምግብንና ልብስን ሆነኝ
ወጸገወኒ እምትካዝ ተአምረኪ መናገዘ
ከጭንቅ ከችግር የሚያረጋጋ ታምርሽንም ሰጠኝ
ቶማስ ሎቱ አመገቦሁ አጎዘ
እንዘ /እስከ/ ይብል ከርቤ እምእዴየ ውሕዘ
ረከበ ውስተ (በውስተ ቀኍስ) አፈወ ምዑዘ
ቶማስ ጎኑን በዳሰሰ ጊዜ ሽቱ ከእጁ ፈሰሰ እስኪል ድረ
ከቀኍሱ ውስጥ አስደናቂ መዓዛን አገኘ።



## መላእክት በሐዋርያት ሥልጣን ስለመዳኘታቸው ታሪክ

ሐዋርያት መላእክት በሰማይ ኮነኑ ስለሚለው ገጸንባ
ለዮሐንስ አፈወርቅ ሁለት ወዲያች ነበሩት እነሱም ንጉሠ
ለርዮድናስና ንግሥቲቱ አውዶክስያ ናቸው። ልጅ እየወለዱ
ይሞትባቸው ነበር በምን ምክንያት ልጅ ይሞት ብናል ብለው
ፊላቸውንና መለሎቻቸውን ጠየቁ ያማከሯቸውም ሰዎች
ልጆችሁን ደግ ሰው በክርስትና ባያነሣላችሁ ይሆናል
አሏቸው ከዚህ ዮተነሣ ከዮሐንስ አፈወርቅ የበለጠ ደግ ሰው
አለን? ብለው ሴት ልጅን በወለዱ ጊዜ መጥተህ አጥምቅልን
ብለው ላኩበት ዮሐንስ አፈወርቅም መልክታቸውን ተቀብሎ
ሲሄድ መልአኩን በመንገድ አገኘው ወዴት ትሄዳለህ አለው
እሱን አንተ የምትሄድባት ሕፃንን ነፍሷን ከሥጋዋ ልለይ
እሄዳለሁ አለው አዲስ የሆነ ልደትን፣ ጥምቀትን ገና አላገኘ
ችምና ቆየኝ ላጥምቃት ብሎት ሄደ ሕፃኗን አጥምቆ በለለ
መንገድ ተመለሰ የካህናት ማዓርጋቸው/ሥልጣናቸው/ ደግ
እንደሆነ ሊታወቅ ወደላይም ወደታችም ላይል አሥር ዓመት
ከዚያው ካለበት ቦታ ቆሞ ኖረ።

ሕፃኗ አሥር ዓመት ሲሆናት ለባል ታጨች ያቺ ሕፃን
ሀብትን አግኝታለችና መጥተህ መርቃት ብለው ላኩበት እሺ
ብሎ በዚያ መንገድ ሲሄድ መልአኩን ቆሞ አገኘው ምነው

## ስለ ሐዋርያው ቶማስ ጥርጥርና አምነት

የክርስቶስ ትንሣኤ በሆነ በስምንተኛው ቀን ለቶማስ ሐዋርያት ጌታን አየነው ቢሉት ቶማስ የችንካሩን ምልክት በእጁ ካላየሁ አላምንም ብሎ ለሐዋርያት ባላቸው ጊዜ ይማጸቱ ክርስቶስ በመካከላቸው ተገኝቶ ሰላም ለእናንተ ይሁን ብሎ ቶማስ ያላመንክ አትሁን አለው። ቶማስም ጌታዬ አምላኬ አንተ አሰገ እጅቼንም አይ ብሎ ቶማስም አይተ አምኗልና እንዲህ አለ ከዚህ የተነሣም ክርስቶስ ሳያዩን የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው የሚለውን ታላ በሐዋርያት ፊት አብነት አደርጎ ተናገረ ዮሐ 20፡19-8።

ቁጥር 87 ከበበ ጌራወርቅ ጽሩይ እምዕንቁ ባሕርይ ዘየኑ፡
ዘተጽሕፈ ብዚ ትእምርተሰሙ ወተዝካረሞቱ
አክሊለጽጌ ማርያም ለጊዮርጊስ ቀጸላ መንግሥቱ
የሰማዕትነቱ ምልክት የሞቱ መታሰቢያ የተጻፈብሽ ከሚያበራ ዕንቁ ይልቅ የጠራ የወርቅ ጌጥ ጊዮርጊስ በክብር የነገሠብሽ የእበባ አክሊል ማርያም።
አንቲ ኩሉ ታሰግዲ ሎቱ
አንች ሁሉን ታሰግጅለታለሽ
ወለኪኒ(ሰ) ይሰግድ ውእቱ።
እሱ ግን ለአንች ይሰግዳል።



## የጊዮርጊስ ስመና የሞቱ ምልክት ታሪክና ምሥጢር

ቅዱስ ጊዮርጊስ የርም ዕዓ ከምትሆን ቀአዶቅያ በርም ቋንቋ ዘርንቶስ በትብጥ ቋንቋ አንስጣዘዮስ ከተባለው አባቱ እና በዕርዕ ቋንቋ አትሊስያ በትብጥ ቋንቋ ቲዎባስታ /ቴዎባስጥያ/ በግእዝ ቋንቋ ቤተ ክርስቲያን ከተባለችው እናቱ ተወለደ።
በአሥር ዓመቱም አባቱ አረፈ።
በአምስት ሽህ ወታደሮች ላይ የበላይ ሥልጣን ነበረው።
ጊዮርጊስም በቤተመንግሥት አሥር ዓመት በዙሙት ከአንስጣስ በኋላ እስከ ሃያ ዓመት ድረስ ለአሥር ዓመታት ያህል ቅዱሳት መጻሕፍትን ተማረ።
ፊሪስ መጋለብን ቀስት መወርወርን አውሬ ማደንንም ጭምር አወቀ ከሃያ ዓመት በኋላ በቅዱስ ጋብቻ እንዲመሰን ሴትን አጨለት።
ጊዮርጊስ ግን የምድር ሙሽራነትን በመናቅ በአግዚአብሔር ፈቃድ በሰማይ የክርስቶስ ሙሽራ ለመሆን መርጦ የርም ነገሥታት ጣያትን የሚያመልኩ ጋላስንና ጋሪስን አሸንፎ ሥልጣን የያዘው ዱድያኖስ ክርስቲያኖችን ሁሉ የሚያሠቃይበትና የሚያላድድበት ጊዜ ነበርና የሃይማኖት ሰማዕት ለመሆን ንጉሥ ዱድያኖስ ጣያት አቁሞ ለምኝ

ሁሉ ለጣዖት ሲያሰግዳቸው አየና ገንዘቡን ሁሉ ለደሀ
መጽውቶ ከዚች ቀን ጀምሮ ተጋድሎውን ተጠለ
ዱድያናስም ጊዮርጊስን በተለያዩ ሥቃዮች ማሠቃየቱን ጀ
ክርስቶስ ግን ጊዮርጊስ ሦስት ጊዜ እንደሚሞትና እር
ሦስት ጊዜ እንደሚያስነሣው በአራተኛውም የምስክር
አክሊል እንደሚቀበል ነገረውና ቅዱስ ጊዮርጊስ ሰባት ዓመ
በተጋድሎ ከኖረ በኋላ በተወለደ በሃያ ሰባት ዓመቱ ሚያ
ሃያ ሦስት ቀን በክብር አርፎ የክብር አክሊልን ተቀዳጀ
ይህ ታሪክ ሲሆን ሐተታው ደግሞ ከዚህ ይከተላል።

## ሐተታና ምሥጢር

፩ ዘተጽሕፈ ብኪ ትእምርተስሙ

የስሙ ምልክት የተጻፈብሽ ማርያም የሚለው ምሥጢ
ማር ኤፍሬም ማር ይስሐቅ እንደሚል ሁሉ ማር ጊዮርጊ
የሚል የመዓርግ ስም ቅጽል አለው ማርያም ከሚለው ስ
ከአራቱ ፊደሎች ማር የሚለውን ሁለት ፊደሎችን መያ
ሲሆን

፪ ወተገዝኣረሞቱ

የስሙ መታሰቢያ ማርያም የሚለው ምሥጢር ደግሞ ከላይ
በታሪኩ ላይ እንደተገለጸው ሦስት ጊዜ ሞቶ ተነሥ



በአራተኛው ጊዜ የክብር አክሊልን ተቀዳጅቶ መንግሥተ
ሰማያት መውረሱን ሲገልጽ ማርያም አራት ፊደል ሆኖ
የአራት ጊዜ መሞት ምሥጢርን በእመቤታችን ስም
የመታሰቢያ ምሳሌ ተመስሏል።

፫ እንቲ ኵሉ ታሰግዲ ሎቱ

አንች ሁሉን ታሰግጅለታለሽ ማለት መኳንንቱ መሳፍንቱ
ሁሉ ይሰግዱላት የነበረች የንጉሡ ሚስት እለእስክንድርያ
በቅዱስ ጊዮርጊስ
ተጋድሎና ትምህርት አምና ለቅዱስ ጊዮርጊስ የጸጋ
ስግደትን ለክርስቶስ የአምልኮ ስግደትን ስግዳ በንጉሡ
ዱድያናስ አዛዥነት አንገቷን በሰይፍ እንድትቆረጥ መደረጉ፡-
በሰማዕትነት አርፋ የክብር አክሊልን በመቀዳጀቷ ነው።
በቅዱስ ጊዮርጊስ የገድል መጽሐፍም እንደተገለጸው በአንድ
ጊዜ ሠላሳ ሺህ አሕዛብን በክርስቶስ አሳምኗል በጣዖቱ
አጽሎን ያደረውን ርኩስ መንፈስም ከጣዖቱ ወጥቶ ምድር
ተከፍታ እንድትውጠው አድርጓል ይህ ሁሉ ድንቅ ታምር
የሚፈጸም እመቤታችን በንጽሕና በቅድስና በወለደችው ጽገ
ክርስቶስ ኃይሩና እንዲህ አለ።

Scanned by CamScanner

የድንጋጌ ጽሕፈት ለእስጢፋኖስ እምነአጽሮት ዘተጸድሊ

ለእመ አመነ ለእንቲ ማርያም መሓዘነ ናብሊስ ተጸንጸሊ

እነዚህም መልክ ይልቅ የምታበራ የእስጢፋኖስ ጽጌረዳ

ሥጋዋም የጸናጽል ድምጽም ያለው የመድኃኒት ታቦት

ድንግል ናብሊስ ማርያም እንች ነሽ።

መአምንከሰ ኦሪኦሎት ማኅበራነልትጣር መአቦሊ

ስለርስ ጽር የሰቡ የፈትህርና የእቦሊ ማኅበር ስማዕታትም

ደናንፈቅትርጊ እሙ በእሚትሰት መዮስሊ

ኢረአመርም ለአማም ቀታሊ

መርስሉ እናቱ ሥጊያለመልም የቅትርሽ ናጽል ድምፂ

በመአምት ጸናይ የሆነ አማንን አላወቁትም።

## ስለ እንቲኦኪው የመጀመሪያ ሰማዕት እስጢፋኖስ

ቤኒሎልፕያኖስ ዘመነ መንግሥት በ296 ዓ.ም. ገደማ

የእንቲኦ የመጀመሪያ ሰማዕት እስጢፋኖስ ነው።

ፍሎልፕያኖስ በሱ ግዛት ውስጥ ያሉት አብያተ

ክርስቲያናት እንዲወድሙ አብያተ ጣዖታት እንዲከፈቱና

እንዲመልኳቸው ሕዝቡን በብዛት የአዋጁን ደብዳቤ

በተላከው ፊት አገዙ ሲያስገብብ ቅዱስ እስጢፋኖስ ሰምቶ

በቀ ክርስቶስ ሃይማኖት ልው በክርስቶስ ፍቅር እሳት ነደደና



ያችን የረከሰች ደብዳቤ ከእንባቢው ወታደር ነጥቆ ቀደዳት።

በዚህ ምክንያት ወዲያውኑ ዲዮቅልጥያኖስ ሰይፉን መገዘ

እስጢፋኖስን መታው ለሁለትም ከፈለው የቅዱስ እስጢፋኖስ

ራስ ወደ ፊት በንጉሡ ላይ የሚደርሰውን መከራ ማለት

ሓይኖቹ እንደሚጠፉና ምጽዋትንም እንደሚለምን እየጮኸች

ትዘልፈው ነበር። እንደ ዮሐንስ ራስ እንደሄሮድስ ተግሣፅ

ማለት ነው።

ከዚህ በኋላ ንጉሡ ራሱን በምድር ውስጥ እንዲቀብሯት

አዘዘ በምድርውስጥ ቀበሯት እንደገና ለሦስት ቀን ያህል

ንጉሡን ስትዘልፍ በብረት ላጥን ውስጥ ጨምረው ከባሕር

እንዲጥሏት አዘዘ እንደታዘዙ አደረጉ ከእግዚአብሔር የታዘዘ

መልአክም ከባሕር ውስጥ ላጥኑን አውጥቶ ከባሕር ዳር

አኖረው የቅዱስ እስጢፋኖስ እናት መጥታ ሣጥኑን ወደ ቤቷ

ወስዳ የመከራው ዘመን እስኪያልፍ ድረስ በሥውር ቦታ

አኖረችው።

መብራትንም ታበራለት ነበር የመከራው ዘመን ሲያልፍ ቤተ

ክርስቲያን ተሠርቶለት ብዙ ታምር ተደርጓል ስለዚህ

ከአበቦች መልክ ይልቅ የምታበራ የእስጢፋኖስ ጽጌረዳ ነሽ

አለ።

Scanned by CamScanner

## ናብሊስ ስለሚባል ድንጋይ ታሪክና ምሥጢር

ናብሊስ የሚባል እንደብረት የሚጮህ እንደመስታውት ሰቱ ያለ ድንጋይ አለ። መልኩ ዕብነበረድን ይመስላል። ሞኝ ለበዛበት ሰው ይበጃል በደከመም ሰው ላይ ሲበዛበት በጀሮው አጠገብ የመቱለት እንደሆነ በቶሎ ያሳጭንቅ ያርፋል ሴትም ምጥ በፀናባት ጊዜ አሱን ስትነካ በፍጥነት ትወልዳለች ወፍም ምጥ ሲፀናባት በአግሯ ትቆምበታለች ወዲያውኑ በፍጥነት ትወልዳለች የምሕረት ድንጋይ ነው። አመቤታችንም በሥጋ ፍስ መድኃኒት ናትና ተአምረ ፈውስ አንቲ ዕብነ ናብሊስ አለ።

## ስለ ፊቅጦር የተጋድሎ ዘመንና ልዩ ታምር

ሰማዕቱ ቅዱስ ፊቅጦር እንደ አንያኪያዊው አስጢፋኖስ በዲዮቅልጥያኖስ ዘመነ መንግሥት በ296 ዓ.ም ገደማ የተነሣ /የተጋደለ/ ሰማዕት ነው አባቱ ጠርማኖስ እናቱ ማርታ ይባላሉ። በሃያ ዓመቱ በዲዮቅልጥያኖስ ቤተመንግሥት የሦስተኛ የሽመት ደረጃ የነበረው ከሃዲ ሥጋን አይበላም ወይንንም አይጠጣም ነበር ንጉሡ የሚያመልከውን ጣዖት አላመልክም ብሎ ለሰማዕትነት ከዘጋጀ በእሳት በዲኝ ተጋድሎ የተጋደለ ነው።



ላሚዳዎችን /የአውድማ እህል የሚዘራባቸው መሣሪያዎችን/ እየሸጠ ራሱንና ነዳያንን ይረዳ ነበር ዘቅዝቀው ሰቀሉት ይህን ሥቃይ ያየች አንዲት የአስራ አምስት ዓመት ሕፃን መላእክት አክሊሎችን በፊቅጦር ራስ ላይ ሲያስቀምጡ አይታ ለአሕዛብ ነገረቻቸው ሰምተውም አደነቁ ብዙዎቹ በክርስቶስ አምነው እነርሱም በሰማዕትነት አርፈዋልና።

ወእለምቱ ምስሌሁ ማኅበራነ ፊቅጦር ወአቦሊ አለ።

## ስለ አቦሊ መታን ማስነሣት ታሪክ

አባቱ ዮስጦስ እናቱ ታውክልያ ይባላሉ። ከመንግሥት ልጆች ውስጥ ነበር ዓላውያንን ወግቶ ሲመለስ ዲዮቅልጥያኖስ ክርስቶስን ክዶ አገኘው ከሌሎች የመንግሥት ልጆች ጋር የዲዮቅልጥያኖስን የመንግሥት ሥልጣን ለመቀማት አስበው ከዚህ ከሚያልፈው ዓለምስ የማታልፈው ሰማያዊት መንግሥትን መውረስ ይሻላል ብሎ መርጠው በሰማዕትነት ለመጋደል ወሰኑ በዚህ መሠረት አቦሊ እንደ ሐዋርያው ቶማስ ቆዳው እስኪገፈፍ ድረስ ተጋድሏል ከዚህም ይልቅ ልዩ ታምርን ሠርቷል ማለት የአንድ ባዕለ ጸጋ ቤት ሚሠራ የቤቱ ግድግዳ ፈርሶ የባዕለ ጸጋው ሁለት ልጆችና በቤቱ ሥራ የተሠማሩ አሥራ ስድስት ሰዎች ሞቱ አቦሊ የተገፈፈ

Scanned by CamScanner

ቆሻውን ወስዶ በሞቱ ሰዎች ላይ ዘርግቶ በሕያ
እግዚአብሔር ስም ተነሡ አላቸውና አሥራ ስምንት ሰዎ
ተነሡ ክርስቶስም የገድልህን መጽሐፍ የሚጽፈውን
የሚያነበውን፣ የሚሰማውንም ሁሉ እኔ በኪሩቤል ክንፍ ላ
ስሙን እጽፈዋለሁ ብሎ ቃል ኪዳን የሰጠህ ሰማዕት ነው።

ቁ፡89 ተአምረ ፍቅርኪ ማርያም ይገብር መንክረ.
እንዘ ዓዕረሞት ያረስዕ ወያስተጥዕም ምረረ /መራረ/
የሞት ጣርን እያስረሳ መራራውንም እያጣፈጠ የፍቅርህ
ታምር ድንቅ ሥራን ይሠራል።

አመዓዛጽጌኪሰ /በመዓዛ ጽጌኪስ/ ለዘበዓውዱስምዕ ለክረ
ከልጅሽ መዓዛ የተነሣ ወይም በልጅሽ መዓዛ በሰማዕትነት
አደባባይ ለለከረ ግን
ውግረተአዕባን ይመስሎ ሐሠረ
እሳትኒ ማየባሕር ቆረረ
በድንጋይ /የድንጋይ/ መወገር ገለባን መሸከም ይመስለዋል
እሳትም የባሕር ቀዝቃዛ ውሃን ይመስለዋል።

ምሥጢሩ ሰማዕቱ እስጢፋኖስን አይሁድ በምቀኝነት
ተነሥተዉ በድንጋይ ሲወግሩት በድንጋይ መወገሩ ምንም
አልመሰለውም ነበር እንዲያውም ጌታ ሆይ ይህን በደል



አትቊጠርባቸው እያለ ለሥጋ ገዳዮቹ ለነፍሳቸው
ይጸልይላቸው ነበር። መከራውን ባለመሰቀቱ ይህ
ተነግሮለታል የክርስቶስም የመጀመሪያው ሰማዕት ነው።
ምክንያቱም ከጌታ ቀጥሎ ከሐዋርያት በፊት መከራን
የተቀበለ እሱ ነውና የሐዋ 7፡54-60
በድንጋይ የተወገሩትንና በእሳት የተቃጠሉትን ሰማዕታት
ሁሉ ያስተርካል።

ቁ፡90 አንብርኒ ማርያም ውስተልብኪ ከመሕልቀት
ወከመማዕሎብ ዘትአምርት (ውርኒ) በመዝራዕትኪ ልዕልት
ማርያም ምልክት አንዳለው ቀለበት በልብሽ፣ እንደማኅተምም
ከፍ ባለች ክንድሽ ያዢኝ መኃ 8፡6፡
በእንተ ርስሐትየስ ኢትመንንኒ ንግሥት
ንግሥት ማርያም ሆይ ስለ ኃጢአቴ አትናቂኝ
እስመወሀብኩ ንብረትየ ለፍቅርኪ ሞት
ዘአሠርገምሙ ለሰማዕት በጽጌሁ ሕይወት
ሰማዕታትን በሕይወት አበባው ለለዝጣቸው ለፍቅርሽ ሞት
ሕይወቴን ሰጥቻለሁና።

ቁ፡91 ተአምረ ፍቅርኪ ማርያም በማኅበረአድቃን ተወደሰ
ማርያም የፍቅርሽ ታምር በጸድቃን ማኅበር ተመሰገነ
ወፈድፋደሰ በላዕለኃጥአን ነግሠ

Scanned by CamScanner

ይልቁንም በታቦአን ላይ ከፍ ከፍ አለ።
አስመአሕየወ /እንሥአ/ ሙታነ ወሕሙማነ ፈወሰ
ሙታንን አሥነሥቷልና ሕሙማንንም ፈውሷልና።
ቦ ዘይቤ አጽገየ ዘየብሰ
የደረቀውን አለመለመ አሳበበ (አበባ አስመሰለ) ያለ አለ።
ወቦ ዘይቤ አድባረ አፍለሰ
ተራራን አፈለሰ ያለም አለ።

## ሐተታ

በታቦአን ላይ ታምርሽ ከፍ ከፍ አለ ማለቱ ጻድቃነ በመልካም ሥራቸው ዋጋ ያገኛሉ ታቦአን ግን በጎ ሥራ ስለሌላቸው ለአመቤታችን በተሰጣት ቃል ኪዳን የመጻ ተኑ ስላላቸው የዳኑትም ብዙ ነመሆናቸው እንዲህ አለ። እንደእንጢላርዮስ እንደ ስምዖን በላዔሰብእ ያሉትን።
የደረቀውን አለመለመ የሚለው የቅዱስ ጊዮርጊስን ታሪክ ያስተርካል።
ተራራን አፈለሰ የሚለው ደግሞ እንደሚከተለው ነው።

## ተራራውን ስላፈለሰ አብርሃም ታሪክ

የሃጓለት አለቃ በሆነ በአባ አብርሃም ዘመን በምሥር የነገሠ ስሙ ሰዎፕ የሚባል ንጉሥ ነበር የንጉሡ የጭፍሮች አለቃ ወደ ንጉሡ ገብቶ እኒህ ክርስቲያኖች ሃይማኖት የላቸውም



እኮን አለው። በወንጌላችሁ የሰናፍጭ ቅንጣት ያህል ሃይማኖት ቢኖራችሁ ይህን ተራራ ተነሥተህ ሂድ ወደባሕር ግባ ብትሉት ይደረግላችኋል ይላልና እንዲት ያህሎል ብሎ ንጉሡ አባ አብርሃምን ቢጠይቀው ቃሉ ትክክል ነው አለው ማቴ 17፥20-21። ይህ ከሆነስ ምልክትን አላዩኝ አለ አባ አብርሃምም ንጉሡን ሦስት ቀን እንዲሰጠው ለመነው ንጉሡም እንዳልህ ይሁን አለው አባ አብርሃምም መነኩሳትንና ኤጲስቆጶሳትን ሰብስቦ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንዲጸልዩ ነገራቸው ከጸለዩ በኋላ በሦስተኛው ቀን አመቤታችን እርግ ጊዜ ኪርያላይሶን (አቤቱ ጌታ ሆይ ይቅር በል) እያላችሁ አድርሱ አለቻቸው እንዳለቻቸውም አደረጉ ንጉሡ ሕዝቡ በተሰበሰበበት ሦስት ጊዜ ሰግደው ተራራውን በመስቀል ምልክት አባ አብርሃም ቢባርከው ተራራው በሰው ሁሉ ፊት ተነሥቶ ወደ ሰማይ ከፍ ከፍ አለ ሊቀጳጳሱና ምእመናኑ ሲሰግዱ ያ ተራራ ሦስት ጊዜ ወደ ቦታው ወረደ እስላምችና ንጉሡ ይህን አይተው አደነቁ
ወቦ ዘይቤ አድባረ አፍለሰ ያሰኘው ምክንያት ይህ ነው።
ጀ፥92 ሃይማኖትየ ማርያም ዘአጥረይኩኪ እምኬፋ
አፍለስኪ ደብረ ወሣረርኪ ለኢያሪኮ በፅንሱ

Scanned by CamScanner

ከጴጥሮስ የተማርኩሽ ሃይማኖቴ ማርያም ተራራን ነትሰሽ
በኢያሪኮ ዳርቻ ላይ ተክልሽ/ ሠራሽ/
ሶበ ያቴክዘኒ ሊተ ዘጌጋይየ ዘለፋ
በበደሌ የሚመጣብኝ ወቀሳ እኔን ባሳዘነኝ ጊዜ
ለእምየ መርዓተጽጌ ተአምርኪ መጽሐፉ
የጽጌ ሙሽራ የአንች የእናቴ ታምርሽ
ያብሥረኒ ሊተ ኑዛዜ ወተስፋ
መጽናናትን ተስፋን ያብሥረኝ ያምጣልኝ

## ሐተታ

ከጴጥሮስ የተማርኩሽ ሃይማኖቴ ማርያም ማለቱ ክርስቶስ የሰውን ልጅ ማን ይሉታል ብሎ ደቀ መዛሙርቱን በጠየቀ ጊዜ ቅዱስ ጴጥሮስ አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ ብሎ ሲናገር ክርስቶስም ብፁዕ (የተመሰገንህ) ነህ በዚች ዓለት ላይ ቤተክርስቲያኔን እሠራለሁ ብሎ የቅዱስ ጴጥሮስ ሃይማኖቱን ያጸናለትና ቅዱስ ጴጥሮስም ሥልጣነ ክህነትን ከክርስቶስ መቀበሉን ያስረዳል ማቴ 16÷15-21።

(1) ሃይማኖት እንዲት ብቻ ናት ኤፌ 4 ÷ 4-5



## ከጽርዕ ወደ ኢያሪኮ ስለፈለሰው ተራራ ታሪክ

በጽርዕ አገር አንድ ተራራ ነበር ርቀቱም ከኢያሪኮ ግማሽ ኪሎ ሜትር ያህል ነው። በዚያም በአመቤታችን ስም የተሠራች ቤተ ክርስቲያን ነበረች እመቤታችንም ለአንድ ቄስ በኢያሪኮ ዳርቻ ቤተ ክርስቲያን ሥራልኝ ስትል በሕልሙ ነገረችው እንደዚህም እየነገረችው ለብዙ ዓመታት ሣያሠራ ቆየ የቤተክርስቲያኒቱንም ሥራ ችላ ባለ ጊዜ የመነኰሳቱ ቤት ከነአጥሩ ወደኢያሪኮ ዳርቻ ፈልሶ ወረደ ነገር ግን በእመቤታችን የጸሎት ኃይል በተራራው ላይ የሚኖሩ ብዙ ሰዎችና የመነኰሳቱ ቤት ያችም ቤተክርስቲያን በፈለሰችበት በዚያ ሌሊት ምንም ጉዳት አላገኛቸውም በማግሥቱ ከየደጃቸው ሲወጡ ከአዩት ታምር በቀር አንዳችም የሚያውቁት ነገር አልነበረምና በዚህ ምክንያት እንዲህ አሉ።

ገጽ 93 ተአምረ ፍቅርኪ ማርያም ውስተአጽናፈ ምድር ያደ
እንዘ ሞገደ ባሕር ያዝነን ወያጠፍዕ ኀደ
ማርያም የፍቅርሽ ታምር በምድር ዳርቻ ሁሉ የባሕር ሞገዱን
ፀጥ እያደረገና እሳትንም እያጠፋ ተገለጸ ታወቀ
እምፍርሐተ ሚመት ዘከህነት /በፍርሐተ ሚመት
ዘምሥጢር/ ተመሊያመ ሪዓደ

Scanned by CamScanner

ከክህነት ሹመት መፍራት የተነሣ ወይም በክህነት ምሥጢር መፍራት ድንጋጼ ደርሶባቸው

ካህናት ክልዔቱ ድኅረ መተሩ ገሀደ

ጸገዩ እምኔኪ ልሳነ ወአደ

ሁለቱ ካህናት በገሀድ ከቆረጡ በኋላ ከአንች ታምር የተነሣ ምላስንና እጅን አገኙ።

## አባቱ አሳት ውስጥ የጣለው ሕፃን ያሰመዳኑ

አንድ የእስላም ወገን ሕፃን ልጅ ከክርስቲያን ልጆች ጋር ላሞችን ሲጠብቅ አረኞች ተሰብስበው ምሳቸውን ሲበሉ ያልተጠመቀው ሕፃን አብሯቸው በቀረበ ጊዜ የክርስትና ጥምቀትን እስከምትጠመቅ ከኛ ጋራ አትበላም አሉት ከእናንተ ጋራ እንድሆን ወደ ክርስትና ሃይማኖት አስገቡኝ አላቸው ካልተጠመቀው ልጅ ይህን ቃል ከሰሙት ከአረኞች አንዱ ተነሥቶ ከሚጠጡበት ምንጭ ውሃ ጠልቆ በሕፃኑ ላይ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጠምቅሃለሁ ስምህም ገሪዛን ይሁን ብሎ አጠመቀው ከተጠመቀ በኋላም በመካከላቸው ገብቶ በላ አባቱም በፊቱ ብርሃንን የተሞላ ሆኖ አየው የልጁም መዓዛ ከሹቱ ሁሉ በለጠ አባቱም ይህን በሰ መዓዛ ከየት አገኘኸው? ንገረኝ አለው።



የክርስቲያን ልጆች የክርስትና ጥምቀትን እንዳጠመቁት ነገረው አባቱ ከዚህ የተነሣ ልጁን በእሳት እንዲቃጠል አደረገ ነገር ግን እመቤታችን በታምር እሳቱን አጥፍታለት ሕፃኑ ድኗል። እናት አባቱም የልጃቸውን ከእሳት መዳን ከተረዱ በኋላ በክርስቲያን ሃይማኖት አምነው ተጠምቀዋል።

## እጆቻቸውን ስለቆረጡ ሁለት ካህናት ታሪክ

በአንጾኪያ አገር አንድ ኢስላም ነቢር ወደቤተክርስቲያን እየሄደ በእመቤታችን ሥዕል ፊት ይቆም ጀመር ከዕለታት አንድ ቀን በሥዕል አድራ አንተ ካላመኑ ወገን ስትሆን ዘወትር ለምን እጅ ትነሣኛለህ አለችው አንቺ የእግዚአብሔር እናት ነሽና እኔን ካሲኦል ማዳን እንደሚቻልሽ አውቃለሁ አላት እመቤታችንም ወደ አባ አትናቴዎስ ሂድ አለችው ያም እስላም ሄዶ ወደክርስትና ሃይማኖት ትመልሰኝ ዘንድ እወዳለሁ አለው አባ አትናቴዎስም አጥምቆ በእርሱ ስም አትናቴዎስ ብሎ ሠየመው።

የቤተክርስቲያን ትምህርትን አስተምሮ የዲቁና የቅስና ሥልጣንን እንዲቀበል አደረገ አባ አትናቴዎስም ከአረፈ በኋላ ምእመናኑ መርጠዉ ሾሙት ከተሾመ በኋላም ቀድሶ ምእመናን በሚሳለሙበት ጊዜ ከክርስትና ጥምቀት በፊት

Scanned by CamScanner

በሕፃንነቱ ወቅት ወዳጅ ነበረችውና ከምእመናን ጋር ወደ እ
ቀርባ እጁን ነክሰችው እጅግ ተቆጣትና ሥርዓተ ቅዳሴውን
ፈጽሞ ወደ ቤቱ ሄዶ ይች እጅ እኮ አደፈች ረከሰች ብሎ
በስይፍ ቆረጣት በልብስም ጠቅልሎ ከመኝታው በታች
እኖራትና ተኛ።

በነጋውም ምእመናን መጥተው ቀድስ አሉት እንግዳ መምህር
በተሾመ ጊዜ ስምንት ቀን ይቀድስ ዘንድ ልማድ ነበረና።
ከዚህ በኋላ ቀድሞ ይሰምናት ወደ ነበረችው ወደ እመቤታችን
ሥዕል ሄዶ ጸለየ እመቤታችንም እንደ ፀሐይ የምታበራ እጅን
በታምር ቀጠሉችለትና እንዲቀድስ ነግራው ቀደሰ አሱም
በሚቀድስበት ጊዜ እጁ እንደ ፀሐይ ስታበራ ያዩ ሁሉ
ተደነቁ። አንዱ ይህ ሲሆን፦

ሁለተኛው ደግሞ ከሮሜ ጳጳሳት ውስጥ እግዚአብሔርን
የሚፈራ ስሙ አባስ የሚባል አንድ ካህን ነበር ሰውነቱንም
ከክፉ ሐሳብና ከዝሙት ሁሉ የጠበቀ ነው።

ከታላላቅ በዓላት ውስጥ አንድ ቀን ሥርዓተ ቅዳሴን ፈጽሞ
ቅዱስ ሥጋውን ከቡር ደሙን ለምእመናን ከአቀበለ በኋላ
እንደሥርዓታቸው ወንዶችም ሴቶችም ከመሳለማቸው በፊት
ላካህኑ ለማደሙ ሰላም ይላሉ በዚህ ልማድ አንዲት ቤት



የካህኑን እጅ ስትሳለም በልቡናው ውስጥ የረከሰ የሥጋ
ፍትወት አደረበትና ልቡናው በዝሙት ጦር ተወጋ
ሥርዓተ ቍርባንንም ከፈጸመ በኋላ ወደ ቤቱ ሄዶ ስይፍ
አንሥቶ እጁን ቆረጠ እመቤቱ ድንግል ማርያም ኃጢአቱን
ይቅር በዪኝ እያለ አስቀሰ በእመቤታችን ታምር የተቆረጠች
እጁ እንደ ቀድሞ ሆነችለት።

ካህናት ክልኤቱ ሁለቱ ካህናት በተምርሽ ምላስንና እጅን አገኙ
አለ

(ሐተታ) እጁን ምላስ ማለቱ አንዱ አካል ከታመመ ከተቆረጠ
ሁሉም አካል ታማሚ ነውና እጅን ምላስ አለ ኖ ቆሮ
12÷14-27።

ገፅ 94 ተአምርኪ ጽጌሐና በገጸ ከሊፋ አመተዐውሎ

የሐና አበባ ማርያም ሆይ ታምርሽ በከሊፋ ፊት በተገለጸ
በታወቀ ጊዜ
ሠረረ ዖፍ ነሚአ ዘመጽሐፈ መልእክት ረቀ
በትእዛዘ ዚአኪ (ጽጌኪ) ያብጽሕ ብሔረ ርሑቀ
በአንቺ (በልጅሽ) ትዛዝ መልክት የተጻፈበት ደብዳቤን ይዞ
ወፍ ወደሩቅ አገር ያደርስ ዘንድ በበረ
ዓሣ ባሕርኒ እንዘይጸውር ወርቀ
የባሕር ዓሣም ወርቅን ተሸክሞ

Scanned by CamScanner

ያጸብት ቀላያተ መየሀርግ ሐይቀ
በባሕር ላይ ሞኝቶ ከየልቱ ይወጣል።

## ወፍ (ርግብ) ደብዳቤን ስንጉሥ ስለመስጠቱ ታሪክ

በመቂዶንያ አገር የነገሠ ክሊፋ የሚባል ንጉሥ ነበር ትርጉሙ ክፉ ሰው ማለት ነው ክርስቲያኖችን የሚቃወሙና ቤተ ክርስቲያንን የሚዘርፍ ነው አትራብ በምትባል አገር በአመቢታችን ስም የተሠራች ቤተክርስቲያንም ነበረች።

ይችን ቤተክርስቲያን አፍርሶ ብሎ ብዙ ሠራዊትን ላክ ሠራዊቱም ቤተክርስቲያኒቱን ሊያቃጥሉ ሲሉ አበምኔቱ ቀሲስ ዮሐንስ ተዉ በማለት እስክ ሶስት ቀንም ጊዜን እንዲሰጡት ለመነና በአመቢታችን ሥዕል ፊት ቆሞ ጸለየ ከሶስት ቀን በኋላም በጥቁር ቀለም የተጻፈች ደብዳቤ መጀ ከሊፋ ደርሳለች የሚል ቃል ሰማና ተደሰተ። ይህን መልክትም ያደረሰ ከእግዚአብሔር የታዘዘ ርግብ የሚባል ነጭ ወፍ ነው መስፍኑም በድንኳን አልጋው ላይ ተኝቶ ሳለ በአውታር በተቆለፈው ድንኳን ውስጥ የፋና መብራት ሲበራ አይቶ ተደነቀ ወፉም ደብዳቤውን ጣለው ደብዳቤውንም አንበቦ ተረዳ ቤተክርስቲያኒቱም በዚህ ምክንያት ሳትቃጠል ቀርታለችና ወፍ ወረቀትን ይዞ በረረ አለ።



ገፅ 95 ጽጌኪ ማርያም ገጺረተአምር አመጣጠን

ማርያም ጽጌ የተባለ ልጅሽ ታምር መሥራትን ዘጀመረ ጊዜ
በትእዛዝኪ አነኑ ማየመጎብኝት አውሃነ
ፈታድሽን በመፈጸም የጋኖችን ውሃ ወይን አድርገሃል
ምንተ ገቢረ ኃያለዚአኪ (ቃለዚአኪ) ዘከፅነ
ቃልሽ ምን ማድረግ ተስኖታል! የተሳነው ነገር አለ? የለም።
ሶበሰ ትፈቅዲ ከመታርአዩ ሥልጣነ
ፅብንኒ ሕብስተ አምነነ
ሥልጣንሽን ልታሳዩ ብትወጂስ ድንጋዩ ዳቦ በሆነ ነበር።
ታሪኩ በቀጥር ጀኛ ከአባ ሳሙኤል ታሪክ ሶባ አተዐ ሰማያ
ከሚለው ይገኛል።

## በቃና ዘገሊላ ስለተደረገው የመጀመሪያው ታምር

የገሊላ አውራጃ በምትሆን በቃና መንደር ሠርግ ተደረገ ኢየሱስ ክርስቶስና ደቀ መዛሙርቱ ድንግል ማርያምም ቤተ ዘመድ ናትና ለሠርጉ ተጠርተው ሄዱ የሠርጉ ባለቤት የሆነው የመሸራው አባት ስሙ ዮካን ሲሆን የመሸራው ስም ደግሞ ዶኪማስ ይባላል። ለሠርጉ የተጠሩት ሁሉ ምሳ እየተጋበዙ ሳለ የወይኑ ጠጅ አለቀ በዚህም አስተናጋጆች

Scanned by CamScanner

ፅዮረት ተስማቸውና ሊያዘኑ እመቤታችንም ልጅ ሆይ ሰምተ
የወደኑ ጠጅ አልቆባቸዋል አለች ይሁዳ ከደቀ መዛሙርቱ
ጋር አልነበረምና ከተአምራቱ ቢለየኝ በሞቱ ንባቡን
እንዳይል ይሁዳ አስከ መጣ ድረስ ጊዜው ገና አልደረሰም
አላት ይሁዳም ወደ ሠርጉ መጣ ከዚህ በኋላ እመቤታችን
ልጅ የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ አለቻቸውና በስድስት ጋኖች
ውሃን ሞሉ በጋን የሞላችሁትን ውሃ ሳጠጅ አሳላፊም
/አስተናጋጅ/ አለ ስጡት አለ የአስተናጋጅ አለቃም
ወይኑን ቀምሶ አደነቀ ሁሉም ዕውቀ ድንቅ ታምር ነው አለ
ክርስቶስም በአደባባይ የመጀመሪያውን ታምር ሠራ ከዚያች
ቀን ጀምሮ የአመኔታችንን አማላጅነቷ ታወቀ።

## ፍቺታ

የመጀመሪያውን ታምር አደረገ ማለት ክርስቶስ በዮርዳኖስ
ከተጠመቀ በኋላ በመጀመሪያ ጊዜ ያደረገው ታምር በቃና
ሠርግ ነውና ሠርጉም በ30 ዓ.ም የካቲት 23 ማክሰኞ
ዘመኑም ዘመነ ሉቃስ ነበር[134] የውሃ በዓል ከውሃ በዓል ጋራ
ይከበር ብለው ሊቃውንት ጥር 12 ቀን ወሰኑ እንጂ ።
ዮሐ 2÷11-12

[134] በዘመነ ሉቃስ በ30 ዓ.ም. የካቲት 23 ማክሰኞ የቃና ሠርግ ሆነ



ገጽ 96 ኅበአተቦ ለማይ በትዳሴኪ እንዘይጸሊ.
ረስዮ ሕብስተ ሳሙኤል ጽጌሃይማኖት ዘሐትለ ዋለ.
በዋልድባ በረሃ ያለ የሃይማኖት አበባ ሳሙኤል በትሩፌሽ
ውሃውን ባርኮ ሕብስት አደረገ ወይም ውሃውን በባረከው ጊዜ
ሕብስት ሆነለት
ምሕረተ ወፍጥሐ ለተአምርኪ እጎሊ.
ለታምርሽ ቸርነትንና ኀጢያትን አነግር ዘንድ
ሥረዪ ኃጢአትየ ወዕዕበየ አትልለ.
ኃጢአቴን አስተሥርዪልኝ ችግሬንም አትልዪልኝ
እስመ ኵሉ ገቢረ ማርያም ትክለ.
ማርያም አንቺ ሁሉን ማድረግ ትችያለሽና።

## ስለ ኢትዮጵያዊው ሳሙኤል ታሪክ

ከአባቱ አስጢፋኖስ ከእናቱ ዓመተማርያም ሳሙኤል
በአክሱም ምድር ተወለደ የቤተክርስቲያን ትምህርትን
እየተማረ አባትና እናቱ በሞቱ ጊዜ ወደደብረ መንኩስ ገዳም
ወደ አባ አድኃኒ ሄዶ የምንኩስናን ልብስ ለብሶ በጾምና
በጸሎት እየተጋደለ ኖረ። ምስጋናውም እንደ ሃያ አራቱ
ካህናተ ሰማይ ምስጋና ሆኖ ተቆጠረለት።

Scanned by CamScanner

ቅዳሴ ለመቀደስም በሚገባ ጊዜ ሕብስትንና ወይንን የተመላ
ጽዋ ይወርድለት ነበር። የእመቤታችንም ቅድስት ድንግል
ማርያም ውዳሴዋን ሲጸልይ ከንድ ያህል ከምድር ወደ ላይ
ከፍ ከፍ ይል ነበር። እመቤታችን ማርያም ወደ እርሱ
መጥታ የሚያበራ ዕንቍንና ንጹሕ ዕጣንን ሰጠችው
ቅዳሴማርያምንና ውዳሴማርያምን ደግሞ ውሃውን ቢባርከው
የሕይወት ሕብስት ሆናላቸው ይቀመሳሙርቱ ተመግበዋል።
ስለዚህ በቅዳሴኪ እንዘይጸሊ ረሰዮ ኅብስተ ያሰኘው ይህ ነው

ጊ፡97 ቅዳሴኪ ማርያም ጸገየ መለኮተ
ማርያም ምስጋናሽ ክብርን አስገኘ
ወፈረየ ብኪ ለቅዱሳን ቅድሳተ
በእንቺ በኩልም ለቅዱሳን ቅድስናን አፈራ
ለላዕካኒሁ እምግዘት ከመየሀቡ /ከመየሀቦሙ/ ፍትሐተ
ለእንልጋዮቹ መፍታትን (ኃጢአት ማስተሥረይን) ይሰጣቸው
ዘንድ እንልጋዮቹ የተባሉ ሐዋርያት ናቸው
እርአዮሙ ለመምህራን ዐበይተ ኃይላተ
ለመምህራን ታላላቅ ታምራትን አሳያቸው ማለት ለሐዋርያት
አምስት ሕብስትን ሁለት ዓሣን ባርኮ ብዙዎችን መመገብ፣
ባሕርን ነፋሳትን መገሠጽ፣ ድውያንን መፈወስ።



እንዘይገብር ተአምረ ወመንክረ በነበ ኵሉ ተአኵተ
ታምራትና ድንቅ ሥራን እየሠራ
በሁሉ ዘንድ ተመሰገነ።
ወለማይኒ ረሰዮ ሕብስተ
ውሃውንም እንጀራ አደረገ ማለት የጻድቁ የአባ ሳሙኤልን
ታሪክ ያመለክታል ዝርዝሩ በተራ ሥርር ፶፭ ይኖራል።

ጀ፡98 አሐዱ ነዳይ ዘክሕደ ሃይማኖቱ
ኪያኪ ክሒደ ሶበ ዐየየ በቅድመ ሰይጣን ዘአስሐቶ
አሚነዚአኪ ድንግል ሰአድኅነነፍሰ በሥዑቶ
ሃይማኖቱን የካደ አንድ ደሃ በአሳተው በሰይጣን ፊት አንችን
መካድ እንቢ ባለ ጊዜ አንችን ማመኑ ነፍሱን ለማዳን
ጠቀመችው ረዳችው
እንዘ ይሴብሕ ተአምረኪ ወለጽጌኪ ምሕረቶ
ታምርሽንና የልጅሽ ቸርነቱን እየነገረ እያመሰገነ
ተንሥአ እምንዋሙ ወአተወ ቤቶ
ከእንቅልፉ ነቅቶ /ከሞት/ ተነሥቶ ወደቤቱ ገባ።

**ስለሠይጣን ወርቅ ሃይማኖቱን ስለካደ ሰው ልዩ ስምና ታሪክ**

ቅፍጥ በሚባል አገር በወንድና በሴት አገልጋይ በወርቅና
በብር በላሞችና በግመሎች ሁሉ እጅግ የከበረ በሆነና
በባሕር የሚነግድ ስሙ ጥብርያዶስ የሚባል አንድ ነጋዴ

ነበር ከብሮ ገኖ ብዙ ዘመን ከኖረ በኋላ በሱ ላይ ዘመን ተለወጠበትና ገዝቡ ሁሉ አለቀ አኗኗሩ ጎሰቆለ ረዳቶቹ ተበተኑ ሠራተኞቹም ሁሉ በችግር አለቁ።

ከዚህ በኋላ ወደሌላ አገር ሄጀ እየነገድኩ እኖራለሁ ብሎ እያዘነ ሲሄድ ሰይጣን በመንገድ አገኘውና ወንድሜ ሆይ ለምን ታዝናለህ? ለምንስ ታለቅሳለህ አለው። ጥበርያዶስም ያገኘኝን እነግርህ ዘንድ አንተ ማነህ? አለው እኔ ሰይጣን ነኝ አለው። ጥበርያዶስም አንተ ሰይጣን ስትሆን ልትረዳኝ ይቻልሃልን? አለው። ሰይጣንም አምን አለውና ለጥበርያዶስ ሁለት ዕንቊዎችን ሰጠው ሰይጣንም ክርስትናህን ትተህ፣ ክርስቶስን ካደው፣ ሱራፌልንና ኪሩቤልን አምላክን የወለደች ድንግል ማርያምንም ካድ አለው ጥበርያዶስም

የነገሩን ፍጻሜ በሰማ ጊዜ የሰማይ የምድር ንግሥት ናትና እመቤቴ ማርያምን አልክድም እንጂ ሁሉንም አክዳለሁ አለው።

ሰይጣንም ማርያምን ካልካድካት የምትሠራው ሁሉ አይረባህም ብሎ ክሱ ተሠውሮ ትቶት ሄደ።

ሠይጣንም የሰጠውን ዕንቊ ቢያይ ተለውጦ የድንጋይ ጠጠር ሆነበት ገዝቤን አጥፍቼ ሃይማኖቴን ለውጬ ፈጣሪዬን ክጀ ወዮታ አለብኝ ብሎ እያዘነ ሲሄድ የእመቤታችንን



ቤተክርስቲያን አግኝቶ በሥዕሏ ፊት እያለቀሰ ከልጅነ አማልጅኝ አለ በአንቅልፍ ላይም እያለ እመቤታችን ጥበርያዶስን ልጅዋ አንዲምርላት ተማፀነችው ስለ አንተ ምሬዋለሁ አላት እመቤታችንም ሁለተኛ አትበድል አለችውና እሱም ወደ ገዳም ሄዶ በጾም በጸሎት ተጸምዶ ኖረ።

በተመሳሳይ በቅዳሴ ማርያም ትርጉም እንደተጻፈ አንድ ደሃ በሠይጣን ምክር እመቤታችንን አልክድም ብሎ ነፍሱ ከሥጋው ከተለየች በኋላ በእመቤታችን ቃል ኪዳን መሠረት ከልጇ አማልዳ ነፍሱ ከሥጋው ተዋሕዳ በሳ ሥራን እየሠራ ኖረ የሚል ታሪክም አለ። ሙሉ ታሪኩን በቅዳሴ ማርያም ትርጉም ይመልከቱ።

ቁ 99 ለብእሲት ብዙኃ ዘአፍቀረቶ ውቀበዮ ዕፍረተ በእዴሃ

ከመኃጢአታ ጎደገ በከመ ጽጌኪ ፈትሐ

ጎድጊ ሊተ ማርያም ኃጢአትየ ብዙኃ

እጅግ ለወደደችውና በእጅዋ ሽቱን ለቀባችው ሴት ልጅሽ ፈርዶ ኃጢአቷን ይቅር እንዳላት ድንግል ማርያም ለኔም ብዙ ኃጢአቴን ይቅር በዪ።

ወረተአምርኪሰ እመኒ ነስሐ

እምኃጢአቱ ኢይረክብ ንጽሐ

የታምርሽ ጠላትስ ግን ንስሓ ቢገባም ሥርየትን አያገኝም።

**ሐተታ** ንስሓ ቢገባም ሥርየትን አያገኝም ማለቱ እንደአርየስ ንስጥሮስ እና መቅዶንዮስ ያሉትን መናፍቃን ሁሉ መናገር ሲሆን የታምርሽ ጠላት ነውና አይማርም አለ።

አርዮስና ንስጥሮስ አግዚአብሔር ወልድ ከድንግል ማርያም በድንግልና መወለዱን ክደዋል መቅዶንዮስም የመንፈስ ቅዱስ አምላክነትን ክዷልና። ክርስቶስ በወንጌሉ የካደኝን በአባቱ ፊት አክደዋለሁ መንፈስ ቅዱስንም የሰደበ ኃጢአቱ አይሠረይለትም ብሎ ተናግሯል። ስለዚህ በድንግልና መውለድሽን ክዷልና ከኃጢአቱ ሥርየትን አያገኝም ሲል ነው

ማቴ.10÷32-34 ሉቃ 12 ÷8-11

## ስለ በደለኛዋ ሴት ሥርየት ማግኘት

ስሟ ማርያም የምትባል የአልዓዛር እህት ነበረች ብዙ ጊዜዋን በገዘሙት ያላሰፈች ነበረች ከዕለታት አንድ ቀን መልኳን በመሥተዋት አይታ ይህ መልክ እንደ ጧት ጤዛ ጠፊ ረጋፊ መሆኑን ተገንዝባ ወደ ንስሓ መመለስ አለበች አስባም አልቀረች ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወዳለበት ሄዳ በብዙ ገንዘብ የተገዛ ሽቱን ወስዳ እግሩን እየቀባች ስታለቅስ አንቺ ሴት ኃጢአትሽ ተሠርዮልሻል እምነትሽ



አድኗሽ ብሎ ከበደሏ ነጽታ ያደረጎትው በኀ ሥራ በአራቱ መዓዝን /በዓለም አቅጣጫ/ ሁሉ እንዲነገርላት ክርስቶስ አዘዘ

ማቴ 26÷6-14 ማር 14÷3-10 ሉቃ 7÷36-50 ዮሐ 12÷3-9።

## ስለ ዮሴፍ ልጅ ዮሳ የሞት ፍርድ ታሪክ

የገሊላ ንጉሥ ሄሮድስ በሁለት ዓመተ ምሕረት ሕፃናትን ለመግደል ባሰበ ጊዜ እመቤታችን ወደ ግብፅ በስደት ስትሸሽ እነ ዮሴፍ በጊጋር ቤት ሰንበቱ የዮሴፍ ልጅ ዮሳ ታሞ ከጊጋር ቤት ነበር የጊጋር ቤተሰቦች በሄሮድስ ሠራዊት ሲፈለጉ ዮሳ ሰምቶ ወደነዮሴፍ ሄደ የሄሮድስ ሠራዊት

Scanned by CamScanner

ወደነሱ እየገሠገሡ መሆኑን ሲገልፅላቸው እመቤታች
ደንግጣ ምርር ብላ ብታለቅስ ጌታ አመጣጥህ ዋጋ የሚያስ
መልካም ነው ነገር ግን እናቴን ስለ አስደነገጥካት በምጽአ
ጊዜ /በትንሣኤ ዘጉበኤ/ መጥቼ መልካም ዋጋህን እሰክሰጥህ
ድረስ ይችን ደንጊያ ተንተርሰህ ተኛ ብሎት
ከዚያው አርፏልና እንዲህ አለ።

## ክፍል ሁለት ተፈጸመ።

ቁ፩-101 ዘያስተሐቅር ተአምረኪ ወኢይፈርህ መርገመ
ሰይጣነ ወልዶ መስተቃርኒ አቀመ
ታምርሽን የሚያቃልል ርግማንንም የማይፈራ ተቃራኒ
አድርጎ ልጁ ሠይጣንን አቆመ፤
ጸግዮ አሥዋከ ከመኢይፍረይ ዳግመ
አሾህን አብቦ ዳግመኛ እንዳያፈራ
ፈንዊ ድንግል ሳዕሌሁ ጕድበሞት ግሩመ
ምስለአዕፅቂሁ ዘይገዝም ፀላዔኪ ያመ
ድንግል ሆይ ከቅርንጫፎቹ ጋራ ጠላትሽ ዛፍን የሚቆርጥ
የሚያስፈራ ገጀሞ /መጥረቢያ/ ሞትን በላዩ ላይ ላኪ እገሠ



## ሐተታ

መጥረቢያ ከሥጋ ሕይወት የሚለይ ሲሆን ሞት ደግሞ
ከርስተ መንግሥተ ሰማያት ተለይቶ በገሃነም ዘላለማዊ ሞት
መቀጣት ነው። እሾህ ጥርጥር ከሀዲት፣ ቅርንጫፎች
የአርዮስ የንስጥሮስ ተከታዮች መናፍቃን።

## ክፍል ሦስት

ቁ፩-102 ኦ ሬዳኢተድኩማን ዘይረድአኪ ኢተንሥሚ
እመንበረላዕክኪ በምዕር ከመገፍታዕኪየ ለወራሲ
የሚረዳሽ የማትፈልጊ የድኩማን ረድኤት ማርያም
ከአገልጋዪሽ /ደገኛው ደቅስዮስ/ ወንበር ላይ የተቀመጠ
ወራሹን /ትዕቢተኛው ደቅስዮስን/ በአንድ ጊዜ
እንደገለበጥሽው
ለገፍትዖ ፀርየ ድንግል ኃይለ ዚአኪ ልበሲ
ጠላቴን ለመገልበጥ ኃይልሽን ልበሺ
ዘይሳለቅ ተአምረኪ እንዘሐሱተ ይራሲ
መፍትውኑ ከመይሕየው ከይሲ
ታምርሽን ውሸት ነው ብሎ በታምርሽ የሚዘባበት እባብ
ሰው በሕይወት ሊኖር ይገባዋልን? እንደ ደቂቀ እስጢፋ
ያሉትን። ታሪኩን በተራ ቁጥር ፻፬ ይመልከቱ።

Scanned by CamScanner

ፍ፡- 103 ለተአምርኪ ማርያም ዐብድ ውእቱ ዘገደፍዎ
ማርያም ታምርሽን የናቀው ሰነፍ አላዋቂ ነው
እስመ ገደፍኪዮ ሎቱ ወጽጌደመና ኀለፎ
አንቺ ጥለሽዋልና የደመና አበባም (ተድላ ደስታ) አልፎታልና
ንዑ ንትፈጋዕ ወኢይኅልፈነ ጽጌ ደመና
ኑ ተድላ ደስታን እናድርግ ተድላ ደስታም
አይለፈን እንዳለ ጠቢቡ ሰሎሞን ጥበ 2፡6-8
ጠቢብሰ (ጠቢብኬ) ለተአምርኪ ዘጸሐፎ
እንዘ እምኅቤኪ ነሢአ ዕሤት ይሴፎ
ተዘኪሮ ለደቅስዮስ አጽፎ
ብልህስ ከአንቺ ዋጋ አገኛለሁ ብሎ፡- የደቅስዮስን ሽልማት
አሰቦ ታምርሽን የጻፈ ነው። (ታምርሽን የጻፈ ብልህ) ነው።

፻፬- 104 ሶበ ጸሐፈ ደቅስዮስ ተአምረኪ ቅዱሰ
መንበረ ወአዕፈ ዕሤተግማሁ ወረሰ
ደቅስዮስ ልዩ የሆነ ታምርሽን በጻፈ ጊዜ የድካሙን ዋጋ
ልብስንና ወንበርን አገኘ
ማርያም ድንግል ዘታብዕሊ ጽኑሰ
ዐስበማኅሌትየ አቅመልብየ ኀሠሠ
ጸግውኒ አትሮንሰ ወጽጉየ ልብሰ



ደሃውን ባዕለጸጋ የምታደርጊ ድንግል ማርያም
ልቡናዬ በፊለገ መጠን የምስጋናዬን ደመወዝ
ወንበርንና የክብር ልብስን ስጪኝ (ንጉስ መንግሥተ
ሰማያትን) አድዪኝ የያዝ. የያ. የያ፬ ታሪኮች የአንድ ታምር
ታሪክ ስለሆኑ በዚህ ያ፬ ቁጥር ይገኛሉ።

## ስለ ደገኛው ደቅስዮስና ትቢተኛው ደቅስዮስ ታሪክ

ስሙ ደቅስዮስ የሚባል ኤጲስቆጶስ ጥልክልያ በምትባል አገር
በተሠራች ቤተ ክርስቲያን አመቤታችንን በትንሽነት ያገለግል
ነበር አመቤታችንን ከመውደዱ የተነሣ ታምሯን የሚናገር
መጽሐፍን ሁሉ ሰበሰበ አመቤታችንም ተገልላ በአይዋ
መጽሐፍን ይዛ አያትና ደስ አሰው እኔም የአገልግሎትህን
ዋጋ አሰጥሃለሁ ብላ ማንም ያልለበሳት ልብስና ማንም
ያልተቀመጠባት መንበርን ሰጠችው ማንም ሊለብሳትና
ሊቀመጥባትም አይችልም አለችውና ከእሱ ተሠወረች ከዚህ
በኋላ ይህ ደቅስዮስ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ
ሌላ ደቅስዮስ ተሾመ በተቢት ተነሣሰቶ እኔም እንደ አርሱ
ኤጲስቆጶስ ነኝ ልብሷንም ልልበስ በወንበሯም ልቀመጥ ብሎ
አሰበ አስቦም አልቀረ ልብሷን ሰብሶ በወንበሯ ተቀመጠ

Scanned by CamScanner

ወዲያውኑ ከወንበሯ ላይ ወደቤተክርስቲያን በመጣ
ምእመናን ፊት ፈጥኖ ወደቀ
እመንበረላዕክኪ በምዕር ከመገፍታዕኪዮ ለወራሲ
ለተአምርኪ ማርያም አብድ ውእቱ ዘገደፍ
የሚለው ቃል ሁሉ ለትቢተኛው ደቅስዮስ ሲሆን
መንበረ ወአፅፈ ዕሤተ ፃማሁ ወረሰ
የሚለው ደግሞ ለደጉ ደቅስዮስ የተነገረ ቃል ነው
ኖ፡-105 ለተአምርኪ ማርያም ኃጥእ ውእቱ ዘአስተዮ
ከመስብሐቲሁ ኢይርአይ እስመጽጌኪ አእተዮ
ማርያም ታምርሽን ያቃለለ ኃጥእ ነው እንደ ይሁዳ ክብሩን
እንዳያይ ልጅሽ አስወግዶታልና አርዮስን ንስጥሮስን፣
ያስተርካል ኢሳ 26÷10-11::
የእመቤታችንን ታምር ያቃለለ ሁሉ በረከትን ያጣል ሲል
ነው::
ለተአምርኪሰ እንዘይነግር ረድኤቶ
ግን የታምርሽን ረድኤት /አጋዥነት/ እየነገረ
ቦ ዘፈለሰ ጎዲጎ ብእሲቶ
ሚስቱን ትቶ የመነነ አለ
ወቦ ገዳመ ዘወፈረ (ዘተግህሠ) መኒኖ መንግሥቶ
መንግሥቱን ንቆ ወደ ገዳም የሄደ አለ::



ገጽ
ቦ ዘፈለሰ ሚስቱን ትቶ የመነነ አለ ለሚለው ታሪክ፡-

## ስለ ንጉሡ ልጅ ገብረ ክርስቶስ ምነና

የሮስጥንጥንያ ንጉሥ ቴዎዶስዮስ ሚስቱ ማርኬላ ትባላለች
ሁለቱም እግዚአብሔርን የሚፈሩ ናቸው ነገር ግን ልጅ
አልነበራቸውም ኢየሩሳሌም ሄደው ተስለው ልጅ ወለዱ
ስሙም አብዲል መሲህ ብለው ጠሩት የክርስቶስ አገልጋይ
ማለት ነው የቤተክርስቲያንን ትምርት አስተማሩት በተወለደ
በሃያ ዓመቱ የሮሜ ንጉሥን ልጅ እንደ ሥርዓቱ አጋቡት
መንፈቀ ሌሊት በሆነ ጊዜ የሚስቱን እጅ ይዞ በአንድ አምላክ
እናምናለን የሚለውን የሃይማኖት ጸሎት እስከ መጨረሻው
ደረስ ጸለየ:: እንዲህም ብሎ ተሰናበታት እግዚአብሔር
ከአንች ጋር ይሁን ከሰይጣን ሥራ ያድንሽ ብሎ አርማንያ
ወደምትባል አገር በአመቤታችን ስም በተሠራች ቤተ
ክርስቲያን ጥግ በሰንበት ቀን ብቻ አህል እየቀመሰ በጾም
በጸሎት እየተጋደለ አስራ አምስት ዓመት ያህል ኖሮ በኋላ
በወላጆቹ ቤት ሳይታወቅ አስራ አምስት ዓመት ኖሮ
አርፏልና እንዲህ አለ መላ ዘመኑ አምሳ ዓመት ነው::
ወቦ ገዳመ መንግሥቱን ንቆ የሄደ አለ ለሚለው ታሪክ፡-

Scanned by CamScanner

**መንግሥቱን ንቆ ወደ ገዳም ሰለሄደው ድንግል ንጉሥ**

ስሙ ማርቆስ የሚባል እግዚአብሔርን የሚፈራ ቸር ንጉሥ
ነበር። ያለ ኃጢአት በድንግልና ዐንቶ በርግ አገር ላ
የሚያስተዳድር ነው በዚህ በመልካም ሥነ ምግባር
በሃይማኖት ዐንቶ አሥር ዓመትን ከፈጸመ በኋላ የርዮ
መኳንንት ሴት እንዲያገባ ለመኑት ለእመቤታችን
እስከነግራት ድረስ ለሰባት ቀን ያህል ታገሡኝ አላቸው
በእመቤታችን ሥዕል ፊት ቁሞ ጸለየ።

ጸሎቱንም ከጨረሰ በኋላ ከሥዕሏ ብርሃንን ባየ ጊዜ እያደነ
ሳለ ይህ ዓለም ለእንተ አይደለም ሰማያዊ መንግሥትን
መርምር እንጂ አለችው ከዚህ የተነሣ ማንም ሰው ሳያየው
ምድራዊ መንግሥቱን ንቆ ቱርማት ወደ ሚባል ገዳም ሄደ
በጾም በጸሎት ተወስኖ ኖሯልና እንዲህ እ
የኢትዮጵያዊው ንጉሥ ካሌብን ታሪክም ያስተርካል

ፍ፡-106 ተአምርኪ መጽሐፈጽጌ በንቤየ ክቡር
ከመ ወንጌሉ ቅዱስ ለሐዋንኪ ፍቁር
የተወደደ የልጅሽ ቅዱስ ወንጌልን ያህል የአበባ መጽሐፍ
ታምርሽ በእኔ ዘንድ የከበረ ነው
ጽላተአራት ማርያም ጸዋሪተ ትእዛዝ (ቃላት) አሥር



አሥሩ ቃላት የተጻፉበሽ የአራት ጽላት ማርያም ዘጸ 31÷18
እምይደቅ እምቃልኪ አሐዱ ነገር
ይቀልል ኅልፈቶሙ ለሰማይ ወምድር
ከቃልሽ አንዱ ነገር ከሚወድቅ ይልቅ የሰማይና የምድር
ማለፍ ይቀላል ወይም ቃል የተባለ ልጅሽ ከተናገረው አንዱ
ቃል ከሚያልፍ የሰማይና የምድር ማለፍ ይቀላል
ማቴ 5÷18-20 ሉቃ 16÷17።

ሙሴ 3844 ዓመተዓለም የቃልኪዳን ጽላትን ተቀበለ[115]

ፍ፡-107 ተአምርኪ መጽሐፈባሕርይ ዘአፀወ ቀዳሚ
አፈጸጥሥታር አርዊ መምህረአይሁድ ወአረማዊ
አንደበቱ እንደ እሬት መራራ የሆነ የአይሁድና የአረማውያን
አውሬ መምህርን አፍ በቀድሞ ዘመን የዘጋ የዕንቊ መጽሐፍ
ታምርሽ ነው፡- ማለት እንደ ዕንቊ የከበረ ነው።
የንስጥሮስን ታሪክ ያስተርካል።
መዓዛ ጽጌያት ጥዕምት እምፂናልብሱ ለአባ ብንያሚ።
ከአባ ብንያሚን የልብስ መዓዛ ይልቅ የሚበልጥ መዓዛ ያለሽ
የአበባዎች መዓዛ ማርያም።
ለዐርኪ መሪረአፍ ወምሉዓ መርገም ሳሚ።

[115] ሙሴ 3844 ዓመተ ዓለም ከእግዚአብሔር የቃልኪዳን ጽላትን ተቀበለ

እንደበቱ መራራ የሆነ እንደ ሳሚም አርግማን የተሞላ
የታምርሽን ጠላት
በተአምርኪ ማርያም ልሳኖ አብሕሚ።
በታምርሽ እንደበቱን ዝጊ
2ኛ ሳሙ 16 ፥5-15።

## ስለ አባ ብንያሚን ልብስ መልካም መዓዛና ታሪክ

በግብጽ ደብብ በቱምጻ አውራጃ ተና ርሚባል አገር ብንያሚን ተመለደ ንጹሕ ካህን ነበር ማለት ከህነቱን ጠብቆ ሥርዓቱን አውቆ ሥርዓቱን የሚፈጽም ነው ከሰለታት አንድ ቀን ልብስተክህኖ ለብሶ ቤተ መቅደስ ከገባ በኋላ አባትህ ታሞ ለሞት ቀርቧል አርሱንም አምጠልኝ ብሏል ብሰው መልክተኞች ቢነግሩት ቀሲስ ብንያሚን ግን የቱርባኑን ሥርዓት ሳልፈጽም ልብሰ ተክህኖውን አሳወልቅም እግዚአብሔር ከፈቀደ ከሞቱ በፊት ይቀየኛል ካልፈቀደ እግዚአብሔር እንደ ወደደ ይሁን ብሎ ለእግዚአብሔር ሥርዓት መፈጸም ስለአደላ የአባ ብንያሚን ክህነት የተባረከ በመሆኑ ልብሱ እጅግ መልካም መልካም ሽታን ይሸት ነበርና እንዲህ አለ።



ክፍ፡ 108 ተአምርኪ መጽሐፈ ሕይወት እሞት ዳግም
ምዕዐወሲኦል ወሞት ዘውእቱ ዝኮነም
ከዳግመኛ ሞት የሲኦልና የሞት መሻገሪያ ታምርሽ ነው
ሞት የተባለም ግሃነም ነው
ታሕዜውኒ ቡቱ ሕይወተኮሉ ዓለም
ተማሕጸንኩ ለጽጌክርሥኪ በዘረከቦ (ጊዜ ረከበ) ሕማም
መበዘአንቱኪ ሲቶታው ወአንበሰ መስየም
በዓለም ሁሉ (በሰማይም በምድርም) ታድኒኝ ዘንድ ልጅሽን
ባገኘው መከራ፣ አንቺንም በከበበኝና ዐይንን በሚያጠፉ
ልቅሶና ዕንባ ተማጽኜ አለምንሻለሁ

**ምሥጢሩ**፦- ጊዜ በሰለተዓርብ በተሰቀለ ጊዜ ያኖነውን
ፀዋትወ መከራ መናገር ሲሆን ያን ጊዜ እመቤታችን መራራ
አዘን ደርሶባታልና እንዲህ አለ።

ክፍ፡ 109 መልዐ ተአምርኪ ኮሉ መክነ
አድባረኒ በሥነጽጌሁ ከደነ።
ታምርሽ ቦታውን ሁሉ ሞላ ተራራዎችንም በክብሩ ሸፈነ
ማርያም ፍሥሐ ዘትስዕሪ (ዘታረሥኝ) ኀዘነ
አዘንን የምትሽረ የምታስረሺ ደስታ ማርያም
በከመአወጸእኪ እምከርሠ እመ ምኔት ሕማነ
ከገዳም አስተዳዳሪዋ ማሕፀን ዕንስን አንደወጣሽ

Scanned by CamScanner

እሞተ፟ኃጢአት ነፍስየ አውጽኢ ፍጡን
ነፍሴን ከኃጢአት ሞት ፈጥነሽ አውጪኒ።

## ስለ እመምኔቷ ልዩ ስምና የፅንስ ታሪክ

በቀርሜሎስ ጀብር ጠባይዋ ያማረ እግዚአብሔርን የምትፈራ እመቤታችንን የምትወድ ሶፍያ የምትባል የሴቶች ገዳም አስተዳዳሪ ነበረች። በገዳሙ ውስጥ በድንግልና የሚኖሩ ብዙ መነኮሳት አሉ የቀናናን ሥርዓት ስታስተምራቸውና በአሉት ጊዜ ሰንፍና አንዳያዛቸው ትመክራቸዋለች ስለዚህ ነገር ያጠፋ፡ል ከሹመቷ የምትሻረበትን ከዜተክርስቲያን የምትባረርበትን ምክንያት ያፈልጉባት ነበር። በዚች እመምኔት ርኩሰ መንፈስ አያረፋትና ለገዳሙ ከሚያገለግሉ ጎልማሳ ወሰች ደናግል እንቶች በኢጲስቆጶሱ /በአባ ሳዊሮስ/ እንደከሰሷት ተረዳች ወደ ቤተክርስቲያን ሂዳ በእመቤታችን ሥዕል ፊት ቁማ ትሰግድ ጀመር በማሕሌቱ ያለውን የዓመፃ ጽንሰ ሻራልኝ አያለች ጸለየች እመቤታችንም ከማሕፀኗ ያለውን ሕፃን አውጥታው ፈለጎክስ ሰጣባል ልው ያሳድገው ዘንድ ለዘጉት አሉ የወተት ላሞች አሉትና ብላ ሁለት የብዝሃን መላእክትን አዘዘች መላእክትም የታዘዙትን ፈጸሙ እመምኔቷም ከእንቅልፋ ብትነቃ የእርግዝና ምልክት ፈጽሞ



የሌለባት መሆኑን ተረዳች በዚያ ጊዜ ተደስተች ከሳሾቿም በተጠሩው ቀን ቢመረምሯት የእርግዝና ምልክትን አላገኙም ነገር ግን እመምኔቷ እመቤታችን ያደረገችላትን ታምር ለአባ ሳዊሮስ ነገረችውና ተደንቆ ሕዝቡም ወደገዳም መጥቶ የቤተክርስቲያን ትምርትን ተምሮ ኤጲስቆጶሱ ከአረፈ በኋላ በእርሱ ፈንታ ሾሙት ባለ ዘመኑ ሁሉ ቤተክርስቲያንን ሲያገለግል ኖረ።

፤፡110 ምንተ ያሠልጥ ደመዚአየ አመወረድኩ ውስተ-ሙስና
ሞቼ ወደመቃብር ብወርድ የኔ ደም ምን ማዳጅን ይፈጽማል
መሬትኑ ይነግር ዘተአምርኪ ዜና
መሬት የታምርሽን ዜና ይናገራልን? /ያመሰግናልን?/
መዝ 29፥9።
ወስክኒ ሊተ ዓመተሕይወት ወጥዓና
መዓዛፍቅርኪ ዘይመሥጥ ጎሊና
እግዝእትየ ጽጌሃ ሰሐና።
የፍቅርሽ መዓዛ ጎሊናን የሚመሥጥ
የሐና አበባዋ እመቤቴ ማርያም የሕይወትና የጤና ዕድሜን
ጨምሪልኝ

፤፡፩-111 መኑ በመቃብር ዘይሴብሖ ለልዑል
ዐቢየትምህርት ሲራክ ከመይነግር ወይብል

Scanned by CamScanner

ዕውቀቱ ከፍ ያለ ሲራክ ልዑል እግዚአብሔርን በመቃብር
ውስጥ የሚያመሰግነው ማነው? ብሎ እንደተናገረ ግን
ያመሰግነዋል።

## ሐተታ

ያልሞቱ ሰዎች ዛሬ ንስሓ ገብተው እንዲያመሰግኑት ሰው
ከሞተ በኋላ ንስሓ ገብቶ እግዚአብሔርን በመቃብር
የሚያመሰግነው ማነው? የለምና በሕያውት ሳለን
እግዚአብሔርን ደስ እያሰኘን እናመሰግነው ሲል ነው ።

መዝ 113፡25-26 ሲራ 17፡27፡29።

ጸጋውኒ ድንግል ኮነመዋዕል
ድንግል ብዙ ዕድሜን ስጪኝ
ከመእስባሕ ተአምረክ በማኅሌተጽጌ ዘኩል
እንደ ፅዝኦ ደስ በሚያሰኝ በማኅሌተጽጌ ታምርሽን አመሰግን
ዘንድ።

እሸሙትነደናቱ ለፍትርክ ቤዘው ስዘኩል
በተሳለ በፍትርሽ ጦር ተወግቻለሁና መኃ 5፡8 ።

## ሐተታ

ዓቢያትምህርት ያሰኘው ምንድን ነው? ቢሉ ከነቢያት በኋላ
ተነሥቶ ከነቢያት ትንቢትና ማረግ ደርሷልና ዳግመኛም



የተናገረው ቃል እንደ ጠቢቡ ሰሎሞን ልብን በምክር
የሚያስደስት ነውና።

ያያፍ 112 ዘያሠምረክ ማርያም ፍሬጽድቅ አፍረይ አዘደ
መሕየው ለክ እንዘእንብር ዘዚአክ ፈቃደ
ማርያም ደስ የሚያሰኝሽ አንድ የእውነት ፍሬን /ንስሓን/
አፈራ ዘንድ ያንችንም ፈቃድ እየፈጸምክ በሕያውት እናር
ዘንድ።

ለመላእክተሞት ዘማዕረር (ጸዋጋን) አለይወሩ ማዕፀደ
የመከር ማሥድን የሚያስ ክፉምች የሞት መልክተኞችን
በሊኦሙ እምስብሐትየ አስክ ይጸኒ ውዑደ
ወይነተአምርየ ዘንተ ጎድን ጉሚደ
ከምስጋናዬ ጥቂት አስኪያፈራ ድረስ እንኳ ይህን የታምራቱን
ወይን ተዉ አትቁረጡ ቢያቸው።

ያያፍ 113 ውስተአፀደወይን ዘበጋዲ ከመይጸኒ አስክል
የወይን ቦታ በሆነው ቢጋዲ አገር ወይን እንደሚያብብ
ተአምረፍቅርክ ይጸኒ በላዕሌየ ድንግል
ድንግል የፍቅርሽ ታምር በኔ ላይ ያብብ ዘንድ
ኢትመንንኒ ለጎጥአ ሚጠደመወልድክ ቃል

Scanned by CamScanner

እካላዊ ቃል ልጅሽ ከንኑ በፈሰሰ ደሙ የገዛኝ እኔ ኃጢአተኛን
አትናቂኝ ቸልም አትበዪኝ
ስብእኒ መንኖንሞዩ ኢይክል
ዘተሣየጦ በወርቱ ዝሑል
ስሙ እንኳ በሚዝግና በሚበላሽ በወርቱ በገንዘቡ የገዛውን
ዕቃ አይንቅም።

## ከጌታው ጋር የተቀበረ ወርቅ ጌታውን ስለ ሚቃጠሉ

በዓለመቅዱት /ባለድስት/ የሚባል ፍጹም ገንዘብ ወዳጅ ሰው
ነበር ሙሉ ወርቅ ከራስጌው ዝልቅ አድርጎ ቆፍሮ ቀብሮ
ስሞት በዚች ላይ ራሴን አድርጋችሁ ትበሩኝ ብሏቸው ከዚያ
ቀበሩት በሦስተኛው ቀን አሳት ከመቃብሩ እየጨሰና እየነደደ
ታየ ቆፍረው ቢያዩት ሌላ አካሉን ጨርሶ ራሱን
(ሞንቅሳቱን) ተያይዞት አዩ ማሰት ወርቱ አሳት ሆኖ
ሊያቃጥለው ተገኘ ይህም ቃል እውነት ተፈጻሚ ለመሆኑ
መጽሐፍ አስቀድሞ ተናግሯል፡ እንዲህ ሊል እናንተ
ባለጠጎች ስለሚደርስባችሁ ጭንቅ ዋይ ዋይ እያላችሁ
አልቅሱ ሀብታችሁ ተበላሽቷል ልብሳችሁም በብል ተበልቷል
ወርቃችሁና ብራችሁም ዝንል ዝገቱም ምስክር
ይሆንባቸዋል።



ሥጋችሁንም እንደ አሳት ይበላል ብሎ ሐዋርያው ያዕቆብ
የተናገረው በዚህ ተፈጸመ። ያዕ 5÷ 2-4። በዚህ ወርቅ ነዳያን
ሊረዱበት ቤተ ክርስቲያን ሊታነጽበት አይገባም ብለው
ክህሐር ጥለውታል ታምርሽንም ማታለል በገሃነም
ያቃጥላልና። በገሃነም እንዳልሠቃይ በደለኛ እኔን አድኚኝ።

ቁ፲፬፡ 114 ለመኑ እንገዘኖ እመጠፋሕኩ በክንቱ
በደመገቦሁ ጽጌኪ ዘተየጠኒ ሰሙ
ልጅሽ ከንኑ ባፈሰሰው ደሙ የገዛኝ እኔ በክንቱ ብሶሩ ማንን
አሳዝናለሁ?
መሐርኒ ድንግል ለመፍቀራስበእ (ምሕረት) ወላዲቱ
ስውን የሚወድ የምሕረት ባለቤት የክርስቶስ እናቱ ድንግል
ማሪኝ ይቅር በዪኝ
ምሕረትስ ሕገወልድኪ (ልብኪ) ውእቱ
ምሕረትስ የልጅሽ (የልብሽ) ሕግ ሥርዓት ነው
ተአምርኪ ስምዕየ በዝንቱ
በዚህም ታምርሽ ምስክሬ ናት

ቁ፲፭፡ 115 ኢታሕምምኒ ማርያም የአክለኒ ዘቀዲሙ
ለጽጌ ክርሥኪ ንጹሕ ዘዲበ መስቀል ሕማሙ
እመቤቴ አታሳዝኚኝ አታስለቅሺኝ ልጅሽ ቀድሞ በመስቀል
ላይ የተቀበለው መከራ ይበቃኛል።

Scanned by CamScanner

እመአተከዘኩኪ እንሰ በገቢረ ርስሐት ሰላጌሠመ.
እኒ ኃጢአትን በመሥራት በየቀኑ ባሳዘንሽ
ተአምረ ማሕሪት (ወናትሐ) ግበሪ ዳሰመ.
እስመበደምየ (ለዘበደምየ)ተዋስሐ ሰወልድኪ ደመ.
የቸርነትና የይቅርታ ፍርድ ታምርን አድርጊልኝ እንጂ
የልጅሽ ደሙ በደሜ ተተሳትፏልና። ወያም የልጅሽ ደሙ
ከደሜ ለተቀላቀለ ለኔ የቸርነትና የይቅርታ ፍርድ ታምርን
አድርጊልኝ እንጂ። (ሐተታ)፦ እመቤታችን የተገኘች
ከአዳም ዘር ነው እግዚአብሔርም አዳምን ለማዳን አስቀድሞ
ቃል ሲገባለት ከልጅ ልጅህ ተወልጄ በመስቀል ተሰቅዬ ደሜን
እፍሰሻ ብሎ እኛን ለማዳን ከነፍሷ ነፍስን ከሥጋዋ ሥጋን
ነስቶ አድኖናልና እንዲህ አለ።

ዮሐኔ 116 ኀልዮ ዓዕረ ሞት ጸዋግ ያደነገጸ ለልብየ
ክፉ የሆነ የሞት ዓሰርን ማሰብ ልቤን ያስደነገጠኸል
ያስፈራዋል
ከመይነግር ባሕቱ ተአምርኪ ተስፋየ
በጺሐኪ ድንግል ጊዜዕረፍትየ
ነገር ግን ታምርሽ ተስፋዬን አለኝታዬን እንዲነግር
ድንግል በዕረፍቴ ጊዜ ደርሰሽ
ጽጌዕፀ ግኑት ገሬ (ውግሬ) ላዕለየ



የነት የዛፍ አበባን በኔ ላይ ጣህ ሰጠኸ
በመዓዛሁ ትጉመሠጥ ነፍስየ
በመዓዛው ነፍሴ ከሥጋዬ ትለያ ዘንድ።
ኪ 117 ዕዐ (ጽጌ) ድንግላ ዘቦላ ወሰኮ ዘደናክ
ዘጸገይክ ጽጌ በማሰነለአይሁድ አሥሞክ
ተአምረድንን ማርያም ዘልማድክ ምሐክ
በእሾሆች አይሁድ መካከል የደን ያደለ የቆላ የሰኳ አበባን
ያበበሽና፣ ልማድሽ ምሕረት የሆነ የመዳን ምልክት
ማርያም መጌ 2+1-2።
መሐክኪ ለምእመንክኒ እምዓዕረዘኮንኒ ድናክ
ዘርቱ ክሆነ ከሞትን የትጣት ፍርድ ታሞገኝሽን ያትር ዘንን
እድኚኝ
ተአምሮትየ ብክ አደይኩን በክክ
በእንች መታመኔ ክንቱ ሆኖ እንዳይቀር።

## ሐተታ

በሾሆች መካከል አበባን ያበበሽ ማለቱ አይሁድን በንግሥናው
እሾሆች ይሉቸዋል ሃያሕዘ ዝጽ 239 ምዕ 66-23 እሾሆች
ከተባሉ ከአይሁድ ቤት ጌታ ተወልዶ ልና ግን የአይሁድ
ግብር የክርስቶስን ግብር አይመስልምና እንዲህ አለ።

Scanned by CamScanner

የሃጽ 118 ማርያም በሊኖ ለጽጊክርሪሚክ በሐሩረፀሐይ ዘመጽሰጠ
ተዘኪረክ ወልድየ ትእምርተንግድትየ በድወ
ለዓቁርየ ጸግም እሞተሲኦል ሐዩወ /ሐይወ/
ማርያም በፀሐይ ሐሩር የተቃጠለ የማሕጸን አበባ ልጅን
ልጂ ሆይ ወደ በረሃ መሰደዴን አስበክ ለወዳጂ ከሲኦል ሞት
ሕይወትን ስጠው በሊው።
እመሰ ለሕያወት ኢኮነ ድልወ
እንበፅየ ቦኑ በክንቱ (ለክንቱ) ተክፅወ
እንዲህ ያለው ሰው ለሕያወት የማይበቃ ከሆነ ዕንባዪ በክንቱ
ፈሰስን (ለክንቱ)ሆነንን? በሊው

የሃዘ 119 አድኅንኒ በተአምርክ ዳንመ ኢያየኩቱ
ሰቆቃወዚአክ ድንግል ያብሥየኒ በሕቱ
ድንግል ያንች ልቅሶ በእጅጉ ይብቃኛል፡ ሁለተኛ እንዳላሰቅስ
በታምርሽ አድኚኝ
እስመአንቲ ውትረ መድኃኒተአዳም ወያቲቱ
አንች ሁልጊዜም የአዳምና የልጅቺ መድኃኒት ነሽና
ኅልዊ ኃጥአነ አስክአድኅነ በጽድቁ
ከመጽጊክ ንጉሥ ተሰቅለ ዕራቁ
ኃጥአንን በቸርነቱ እስክአዳነ ድረስ ንጉሥ ልጅሽ ራቁቱን
እንደተሰቀለ አስቢ።



ፊሃ 120 እንበያንአውሊጊስ ለዳንኤል አመአርአሎ ስትለት
ከመአገረሁ ስሪሚክ ወሰአልክኒ ምሕረተ
ለተአምረክዝለ ወልድክ በእንተዓትረሰብእ ዘሞተ
እንዚተዘክረኒ ድንግል ይምሐረኒ ሊተ
ከናፍረው ጽጊ አንኒ ስዕመተ
በአውሊጊስ ምክንያት በዳንኤል ስትለትን በፈረደበት ጊዜ
ድንግል ሆይ ሥላልሽ እንሩን ስመሽ ምሕረትን
እንደለመንሽው ሁሉ ስለሱው ፍትረ የሞተ የያትረኑ ባለቤት
ልጅሽን አኔን ይምረኝ ዘንድ አዘላ ክንፈሩን መላልሽ
አየሳምሽ ለምኚው።

## በአውሊጊስ ምክንያት ከመሰተል ስለ ዳንየው ዳንኤል

ይህ አላ ዳንኤል ኃላት ገድሰኮ ነው ከትጠለ በቀር ሌላ
አያመገብም ነበር በዚህ ሁኔታ አረላ ኅሙት ከስድስት መር
